ወደ ዕብራውያን

መግቢያ

የዕብራውያን መልእክትን ማን እንደጻፈው አይታወቅም። ይህ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፣ ጳውሎስ በየመልእክቶቹ መጀመሪያ ስሙን እንደሚገልጸው፣ በየትኛውም ስፍራ ስሙን ሲጠቅስ አንመለከትም። በዕብራውያን 2፥3 መሠረት የዚህ መልእክት ጸሐፊ ስለ ምሥራቹ ቃል ያወቀው ከእርሱ ቀድመው ከሰሙት ሰዎች፣ ማለትም ከሐዋርያት ነበር። ጳውሎስ የምሥራቹን ቃል የተቀበለው በቀጥታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው (የሐዋ. 9፥4–6)። ስለሆነም ይህን መልእክት የጻፈው እርሱ ቢሆን ኖሮ በፍጹም እንደዚያ አይልም ነበር።

መልእክቱ የተጻፈው በ60 እና በ70 ዓ.ም. መካከል እንደሆነ ይታሰባል። መልእክቱ የተጻፈላቸው «ዕብራውያን»[1] እነማን እንደሆኑም በትክክል የሚታወቅ ነገር የለም። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደሚስማሙበት ግን አረማይክ ቋንቋ ተናጋሪ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ናቸው። ይሁን እንጂ፣ የየትኛው ከተማ ነዋሪዎች እንደሆኑ ምንም የምናውቀው የለም።

የመልእክቱ ጸሐፊ ማን መሆኑን፣ የተጻፈውም ለእነማን እንደሆነ አለማወቃችን ግን በፍጹም ሊያሳስበን አይገባም። አንድ ነገር ግን በእርግጠኝነት እናውቃለን፤ ይኸውም፣ የመልእክቱ ጸሐፊ እግዚአብሔር እንደሆነና የተጻፈውም ለእኛ መሆኑን ነው።

ለመሆኑ ጸሐፊው ይህንን መልእክት ለእነዚህ ዕብራውያን፣ ማለትም ለአይሁድ ክርስቲያኖች የጻፈላቸው ለምንድነው? እነዚህ ክርስቲያኖች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያየ ዓይነት ፈተናዎች እየወደቁ ነው፤ ስለዚህም ጸሐፊው በእነዚህ ፈተናዎች መውደቅ እንደሌለባቸው ሊያሳስባቸውና ሊያበረታታቸው ይህን መልእክት ጻፈላቸው። ፈተናዎቹስ ምንድናቸው? እነዚህ ዕብራውያን ዳተኞች እየሆኑ ነው (ዕብ. 6፥12)። ችላ ማለትና ተስፋ መቁረጥ ጀምረዋል (ዕብ. 12፥3)። መጀመሪያ የነበራቸው የእምነት ሁኔታና ቅንዓት እየቀዘቀዘ ነበር (ዕብ. 3፥14፤ 10፥23፤ 35)። በእምነታቸውም አላደጉም (ዕብ. 5፥12–14)። አንዳንዶቹም መሰብሰባቸውንና እርስ በርስ መገናኘታቸውን አቁመዋል (ዕብ. 10፥25)። ክርስቲያን መሪዎቻቸውንም እየተቃወሙ ነበር (ዕብ. 13፥17)። እንዲያውም አንዳንዶቹ ጭራሽኑ እምነታቸውን የመተው አዝማሚያ እየታየባቸው ነበር (ዕብ. 3፥12፤ 10፥26)።

የእነዚህን ዕብራውያን ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሁኔታ ስንመለከት፣ ራሳችንንም መመርመር ይኖርብናል። በተለያየ ሁኔታ እነርሱን እየመሰልን ይሆን? እንደዚያ ከሆነ እንግዲያውስ መልእክቱ የተጻፈው ለእኛም ጭምር ነው ማለት ነው!

በአጭር አነጋገር እነዚህ ዕብራውያን ክርስቲያኖች፣ በጣም ከባድ በሆነ ፈተና ለመውደቅ ተቃርበዋል። አዲሱ የክርስቲያን እምነታቸውን ትተው ወደ ቀድሞው የአይሁድ ሃይማኖታቸው ሊመለሱ ነው።

ስለዚህም ጸሐፊው ይህን መልእክት የሚጽፈው አራት ዓላማዎችን በአእምሮው ይዞ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ በክርስቶስ ብቻ ስለሚገኘው ደኅንነትና የዘላለም ሕይወት ሊያሳስባቸው ይጽፍላቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ በክርስቶስ በማመን ስለሚገኘው ተቀጥር ስለማያልቅ በረከት ሊያሳስባቸው ይጽፍላቸዋል። በሶስተኛ ደረጃ፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመድረስ ከተፈለገ፣ ክርስቶስ ራሱ መከራን እንደተቀበለ ሁሉ፣ አማኞችም መከራን ለመቀበል መዘጋጀት እንዳለባቸው ሊነግራቸው ይጽፍላቸዋል። በአራተኛ ደረጃ ደግሞ፣ በክርስቶስ ያላቸውን እምነት በመተው ወደ ኋላ ከተመለሱ፣ የእግዚአብሔር ፅኑ ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ለማስጠንቀቅ ነው መልእክቱን የጻፈላቸው።

[1] ዕብራውያን አረማይክ ቋንቋ ወይም ዕብራይስጥ ተናጋሪ አይሁዳውያን ናቸው (በአብዛኛው ዕብራይስጥና አረማይክ ቋንቋ ተመሳሳይ ናቸው)። አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን አረማይክ ቋንቋ በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ በስፋት ይነገር ነበር።

አስተዋጽኦ

ሀ. የክርስቶስ በላጭነት (1፥1–7፥28)

1. መግቢያ (1፥1–4)
2. ክርስቶስ ከመላእክት ይበልጣል (1፥5–14)
3. መደመጥ ያለበት ማስጠንቀቂያ (2፥1–4)
4. ክርስቶስ ፍጹም ሰው ስለመሆኑ (2፥5–18)
5. ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል (3፥1–6)
6. ክርስቶስ የእርሱ ለሆኑት ተስፋ የገባው እረፍት (3፥7–4፥11)
7. ክርስቶስ ታላቁ ሊቀ ካህን (4፥12–5፥10)
8. ስለ ክህደት ወይም ሐሰት ትምህርት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (5፥11–6፥20)
9. የክርስቶስ ክህነት ከመልከጼዴቅ ክህነት ይበልጣል። (7፥1–28)

ለ. አዲስ እና የተሻለ ኪዳን (8፥1–10፥18)

1. አዲሱ ኪዳን (8፥1–13)
2. አዲሱ መቅደስና የክርስቶስ ደም (9፥1–28)
3. ለአንዴ እና ለዘላለም የሆነ ክርስቶስ መሥዋዕት (10፥1–18)

ሐ. የእምነት ሕይወት (10፥19–13፥25)

1. ስለ እምነት ሕይወት ገለጻ (10፥19–25)
2. የሚያፈገፍጉ ሰዎች ዕጣ-ፈንታ (10፥26–39)
3. የእምነት ሰዎች (11፥1–40)
4. ክርስቶስ ምሳሌያችን (12፥1–3)
5. የእግዚአብሔር ተግሳጽ (ቅጣት) (12፥4–13)
6. የአዲሱ ኪዳን ክርስቲያናዊ አኗኗር (12፥14–29)
7. የየዕለቱ ክርስቲያናዊ ኑሮ (13፥1–17)
8. መደምደሚያ (13፥18–25)

ምዕራፍ 1

የእግዚአብሔር ልጅ በላጭነት (1፥1–4)

1 *በቀድሞ ዘመናት* ማለትም ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ በፊት፣ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ነቢያት አማካይነት *ለአባቶቻችን* (አይሁድ) ተናግሮ ነበር።

2 *አሁን ግን በእነዚህ በመጨረሻ ቀኖች . . . በልጁ በክርስቶስ አማካይነት ለእኛ ተናገረን*። በእነዚህ የመጨረሻ ቀኖች ሲል፣ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ከመጣበት ጊዜ ወዲህ ያለውን ማለቱ ነው።

ጸሐፊው ይህን ሲል፣ የነቢያቱ ቃል ከክርስቶስ ቃል እውነተኛነቱ ያነሰ ነው፣ ወይም ደግሞ አስፈላጊነታቸውም ይህን ያህል አይደለም ማለቱ አይደለም። ጉልህ ልዩነቱ ግን ይህ ነው፤ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ወደ ክርስቶስ የሚያደርሰውን መንገድ አመለከቱ፤ ስለ ክርስቶስ መንግሥት መምጣት ትንቢት ተናገሩ። ክርስቶስ ራሱ ግን የእነዚህ ትንቢቶች ፍጻሜ ነው። አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ተስፋዎችና ትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜ ነው (2ቆሮ. 1፥20 ይመለከቷል)።

የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ምን ዓይነት ሰው ነው? በመጀመሪያ *የሁሉ ነገር ወራሽ ነው*። ሥልጣንና ኃይል ሁሉ የክርስቶስ ነው (ማቴ. 28፥18)። እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ የፈጠረው *በእርሱ* ነው (ዮሐ. 1፥3፤ ቆላ. 1፥16 ይመለከቷል)። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እንኳ፣ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር። እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረው በክርስቶስ አማካይነት ነው።

3 ክርስቶስ *የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ነው*። የፀሐይ ብርሃን በምድር ላይ እንደሚንፀባረቅ ሁሉ፣ የክርስቶስም ብርሃን በሰዎች ልብ ይንጸባረቃል።

ክርስቶስ *በባሕርዩ ከእግዚአብሄር ጋር ፍጹም ትክክል ነው*። ክርስቶስ የእግዚአብሄር *መልክ* ነው (2ቆሮ. 4፥4፤ ቆላ. 1፥15)። የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። በእምነት አማካይነት በመንፈሳዊ ዓይኖቻችን፣ ክርስቶስን ስናየውና ስናውቀው እግዚአብሔርን አይተነዋል፣ አውቀነዋል ማለት ነው (ዮሐ. 1፥18፣ 14፥7–9 ይመለከቷል)። *ምክንያቱም የመለኮት ፍጹም ሙላት በሰውነት ተገልጦ የሚኖረው በክርስቶስ ስለሚኖር ነው*። (ቆላ. 2፥9)።

ሁሉም ነገር ተያይዞ የቆመው በክርስቶስ ነው። (ቆላ. 1፥17)። ክርስቶስ የዓለማት ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን፣ ያጸናቸውም እርሱ ነው። ዓለማትን በሙሉ ደግፎ ያቆማቸው፣ ከዋክብትና ፕላኔቶች መንገዳቸውን ጠብቀው የሚሽከረከሩት በእርሱ ነው። ይህን ሁሉ ያደረገው ደግሞ *ሥልጣን ባለው ቃሉ* ነው። ክርስቶስ የሚናገረው ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፣ የእግዚአብሔር ቃል ማለት የቃልና ድርጊት ጥምረት ማለት ነው። እግዚአብሔር ተናጋሪ ብቻ አይደለም፤ እርሱ ቃል ሲናገር ድርጊትም ይከናወናል። የተናገረውን ይፈጽማል። *እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ* (ዘፍ. 1፥3)።

ክርስቶስ *ሰዎችን ከኃጢአት ያነጻል*። የኃጢአታችንን ይቅርታ እንድናገኝና እንድንነጻ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ራሱን መሥዋዕት አደረገ። በእኛ ምትክ ሆኖ የኃጢአታችንን ቅጣት ተቀበለ (ማር. 10፥45 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። ክርስቶስ *የኃጢአታችን መሥዋዕት ሆነ* (ሮም 3፥25)። በክርስቶስ፣ በደሙ፣ በመሥዋዕትነቱ፣ አማኞች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ እና ጻድቃን ሆነው ይታያሉ (ሮም 3፥24፤ 5፥1፤ 9 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)።

ክርስቶስ ከሞተ ከሶስት ቀን በኋላ ተነሣ፤ አሁን በሰማይ *በጎያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል* (መዝ. 110፥1፤ ሉቃ. 22፥69፤ ኤፌ. 1፥20–21 ይመለከቷል)።

ከእነዚህ የመጀመሪያዎቹ የዕብራውያን መልእክት ሦስት ቁጥሮች፣ ክርስቶስ እግዚአብሔር የመጨረሻውንና የመደምደሚያውን ቃል የተናገረበት ከሁሉም የሚበልጥ «ነቢይ» መሆኑን መመልከት ይቻላል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ክርስቶስ በራሱ መሥዋዕትነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማለትም፣ እኛን አማኞችን ያነጻና በእግዚአብሔርም ፊት ጻድቃን እንድንሆን ያደረገ ከሁሉም የሚበልጥ «ካህን» ነው። ክርስቶስ ነቢይና ካህን ብቻም አይደለም፤ በእግዚአብሔር ቀኝ በዙፋኑ የተቀመጠ የነገስታት ንጉሥም ነው። በእነዚህ የመልእክቱ መክፈቻ ቁጥሮች፣ ጸሐፊው የሚናገረውም ስለዚሁ ክርስቶስ ነው። እነዚህ ዕብራውያን ክርስቲያኖች ያመኑትም በዚሁ ክርስቶስ ነበር።[2]

4 ክርስቶስ *ከመላእክት በላይ ነው*። የክርስቶስ *ስም* ከስሞች ሁሉ በላይ ነው (ፊል. 2፥9–11 ይመለከቷል)።

ክርስቶስ ከመላእክት ይበልጣል (1፥5–14)

5 ክርስቶስ ከመላእክት ሁሉ በላይ መሆኑን ለአንባቢዎች ለማሳየት የዚህ መልእክት ጸሐፊ፣ ከብሉይ ኪዳን ሰባት የተለያዩ ክፍሎችን ይጠቅሳል። እነዚህን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች በሙሉ የተናገረው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን ያስተውሏል። መላው ብሉይ ኪዳን (እንደ አዲስ ኪዳን ሁሉ) የራሱ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን መዘንጋት የለብንም (ቁ. 1)። በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት፣ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ይናገራል።

ለየትኛውም መልአክ እግዚአብሔር *«አንተ ልጄ ነህ»* አላለም። እግዚአብሔር ያለው አንድ ልጅ ብቻ ነው፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ምንጊዜም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር (ዮሐ. 1፥1–2፣ 14 ይመለከቷል)።

በዚህ ቁጥር ላይ ጸሐፊው ከመዝሙር 2፥7 እና ከ2 ሳሙ. 7፥14 ይጠቅሳል። እነዚህ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ስለ ክርስቶስ የተጻፉ ትንቢቶች ናቸው።

6 ክርስቶስ የእግዚአብሔር *በኩር ልጅ* ነው። ብኩርናውም በሁለት መንገድ ነው። በመጀመሪያ *አንድ እና ብቸኛ* የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዮሐ. 1፥14)። በሁለተኛ ከሞት ለመነሳት የመጀመሪያው ነው፤ ስለዚህም በትንሳኤ ከሞት ለሚነሱት ሁሉ በኩር ሆኖአል (ሮሜ 8፥29፤ 1ቆሮ. 15፥20 ይመለከቷል)

በዚህ ቁጥር ጸሐፊው ከዘዳ. 32፥43 እና ከመዝ. 97፥7 ሲጠቅስ፣ *የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይስገዱለት* (ለክርስቶስ) ይላል። መላእክት ለክርስቶስ ሰግደውለታል፤ ስለዚህም ከመላእክት በላይ እንደሆነ እናውቃለን።

7 እዚህ ላይ ጸሐፊው ከመዝ. 104፥4 ጠቅሶአል። መላእክት በነፋስ እና በእሳት ነበልባል ተመስለው እግዚአብሔርን ያገለግሉታል። እንዲህም ሲባል ነፋስና የእሳት ነበልባል በአንድ ወቅት ታይተው እንደሚጠፉ ሁሉ፣ መላእክትም እግዚአብሔር ያዛቸውን ለመፈጸም ይገለገሉ፤ የታዘዙትን ከፈጸሙ በኋላም ይሰወራሉ ማለት ነው። መላእክት *አገልጋዮች እንጂ ጌቶች አይደሉም*።

8–9 ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔ ልጅ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱ እግዚአብሔር ነው። እንደመላእክት ሁሉ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ተገልጾ አይሰወርም። የክርስቶስ *ዙፋን* ማለትም፤ መንግሥት *ከዘላለም* እስከዘላለም ይጸናል (ቁ. 8)። እዚህ ላይ ክርስቶስ *አምላክ ሆይ!* ተብሎ መጠራቱን ያስተውሏል። በጽድቅም ይገዛል። ከነገሥታት መካከል ክርስቶስ ብቻ በፍጹም ጽድቅ ይገዛል። በእነዚህ ቁጥሮች ማለት ከ8–9 ጸሐፊው የጠቀሰው ከመዝ. 45፥6–7 ነው።

እግዚአብሔር ክርስቶስን *በደስታ ዘይት ቀባው* (ቁ. 9)፤ ስለዚህም *ከጓደኞቹ* ማለትም ከአማኞቹ ሁሉ በላይ አድርጎታል። *የደስታ ዘይት* ማለት የመንፈስ ቅዱስ ደስታ ነው (ዕብ. 12፥2 ይመለከቷል)። ይህም፤ እግዚአብሔር መንፈሱን በሙላት ለክርስቶስ ሰጥቶታል ማለት ነው (ዮሐ. 3፥34፤ የሐዋ. 10፥38)። ለእኛ ለአማኞች ግን የእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠን በተወሰነ ወይም በተመጠነ ደረጃ ነው (ሮሜ 12፥3፤ ኤፌ. 4፥7)።

10–12 በእነዚህ ቁጥሮች ጸሐፊው የሚጠቅሰው ከመዝ. 102፥25–27 ነው ። እግዚአብሔር ራሱ ክርስቶስን *አምላክ ሆይ!* እንዳለው ያስተውሏል። ክርስቶስ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ነው። ሰማይና ምድር *ይጠፋሉ፤* ክርስቶስ ግን *ለዘላለም ይኖራል* (ቁ. 11)፤ እርሱ *ሁልጊዜ የማይለወጥ ነው* (ቁ. 12)።

---

[2] ስፋ ላለ ማብራሪያ ከአስተምህሮ ዳሰሳው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ይመለከቷል።

13 ይህ ቁጥር የተጠቀሰው ከመዝ. 110፥1 ነው (1ቆሮ. 15፥25፤ ኤፌ. 1፥20–22፤ ዕብ. 10፥12–13 ይመለከቷል)። ለየትኛውም መልአክ ቢሆን፣ እግዚአብሔር፤ «በቀኜ ተቀመጥ» አላለም። ያ ስፍራ ለክርስቶስ ብቻ የተጠበቀ ነው። አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ባለው ዙፋኑ ላይ ሆኖ፣ ክርስቶስ በኃይልና በሥልጣኑ ይገዛል።

14 የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ በዙፋኑ ላይ ሆኖ ይገዛል። መላእክት ግን *የእግዚአብሔር አገልጋዮች* ናቸው። እነዚህ መላእክት *የሚድኑትን* ማለትም በክርስቶስ የሚያምኑትን *ለማገልገል* ተልከዋል። መላእክት በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ፤ ሆኖም የክርስቶስ አገልጋዮች ብቻ ናቸው (ሉቃ. 1፥19 ይመለከቷል)። ክርስቶስ የበላይ ነው።

አማኞች የሚድኑት ናቸው። እኛ በክርስቶስ *ያመንን* ድነናል፤ ይሁን እንጂ፣ በዓለም መጨረሻ ክርስቶስ ሲመለስ ብቻ ነው የተሟላ ርስታችንን፣ የተሟላ ደኅንነታችንን የምንቀበለው (ከአስተምህሮ ዳሰሳው የደኅንነት መንገድ የሚለውን ይመለከቷል)።

ምዕራፍ 2

መደመጥ ያለበት ማስጠንቀቂያ (2፥1–4)

1 ለምንድነው መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት የሚኖርብን? የሰባኪዎችንና የመጋቢዎችን ቃል ለማድመጥስ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ለምንድነው? ምክንያቱም *ለሰማነው ነገር* ማለትም ለእግዚአብሔር ቃል ጥንቃቄ የማናደርግ ከሆነ ከእውነት *እንሸራተታለን*። ከክርስቶስ *እንሸራተታለን*፤ በእርሱ ላይ ካለን እውነተኛ እምነትም እንሳሳታለን። ክርስቶስን ከመከተል ወደ ኋላ የምንመለስ ከሆነ፣ *እንዲህ ያለውን ታላቅ ደኅንነት ቸላ የምንል ከሆንን*፣ ከእግዚአብሔር ቁጣ እና ፍርድ አናመልጥም (ቁ. 3)። ከወንጌል ውጪ፣ በክርስቶስ በማመን ከሚገኘው ደኅንነት ውጪ እንሆናለን። በክርስቶስ በሚያምኑት ላይ እግዚአብሔር ከሚያደርገው *ተገቢ ቅጣት* ማምለጥ አንችልም። ስለዚህም *ስለሰማነው ነገር በጣም መጠንቀቅ አለብን!*

2 *የሰማነው* የክርስቶስን ወንጌል ነው። እንግዲህ *በመላእክት አማካይነት የተናገረው ቃል*፣ ማለትም ብሉይ ኪዳን ወይም የአይሁድ ሕግ *እርግጠኛ ከሆነ*፣ የክርስቶስ ወንጌል፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ ይበልጥ እርግጠኛ ነው። ለምን? ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ሕግ *የተነገረው* በመላእክት አማካይነት ነበር (የሐዋ. 7፥53)፤ አዲስ ኪዳን የተነገረው ግን በክርስቶስ አማካይነት ነው (ዕብ. 1፥2)። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊም በምእራፍ 1 ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ አመልክቶአል። በዚህም ምክንያት አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን ይልቃል ማለት ነው። የብሉይ ኪዳንን ሕግ *በመተላለፋቸው* አይሁዳውያን *ተገቢውን ቅጣት* ተቀብለዋል። እንግዲህ ሰዎች በጣም ጥቃቅን የሆኑትን የብሉይ ኪዳን ሕግና ደንቦችን በመተላለፋቸው ከተቀጡ፣ በራሱ በእግዚአብሔር ልጅ የተነገረውን የክርስቶስን ወንጌል ቸላ ብንል፣ በእርግጥ የእግዚአብሔር ቅጣት በእኛ ላይ ይሆናል።

3 አስቀድሞ *ይህን ደኅንነት* ያበሰረው *ጌታ* ራሱ፣ ማለትም ክርስቶስ ነው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ክርስቶስ እንደሚመጣ ትንቢት ተናግረዋል፤ ትንቢታቸው መፈጸሙን ያወጀው ግን ራሱ ክርስቶስ ነበር (ማር. 1፥14–15፤ ሉቃ. 4፥17–21 ይመለከቷል)። ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መፈጸማቸውን ከማወጁም ባሻገር እርሱ ራሱ የትንቢቶቹ ፍጻሜ ነበር!

ክርስቶስ ያበሰረውን *ይህን ደኅንነት* ከእርሱ የሰሙት ሐዋርያት *አረጋግጠውልናል*። የደኅንነት ወንጌል ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ መሠረት የለሽ ወሬ ወይም የሰዎች ፈጠራ ተረት አይደለም። ጸሐፊውም ሆነ የዚህ መልእክት አንባቢዎች፣ ወንጌልን የሰሙት በገዛ ዓይኖቻቸው፤ ክርስቶስን ካዩትና በገዛ ጆሮዎቻቸውም ከሰሙት ሰዎች፣ ከሐዋርያት ነበር።

4 በስብከታቸው ወንጌልን የመሰከሩ ሐዋርያቱ ብቻ አልነበሩም፤ እንደ ፈቃዱ በሚያድላቸው (የሐዋ. 2፥22፤ 43፤ 1ቆሮ. 12፥7–11 ይመለከቷል) *ምልክቶች፣ ድንቅ ነገሮች፣ ልዩ ልዩ ትአምራትንም* በማድረግ እግዚአብሔር ራሱ ምስክርነታቸውን *አጽንቶአል*። *ታዲያ፣ እንዲህ ያለውን ታላቅ ደኅንነት እንዴት ቸላ ማለት ይቻላል?*

በሐዋርያት ዘመን የነበሩ ሁሉ ስለ እነዚህ ድንቅና ተአምራት *ያውቃሉ*። ብዙዎቹም የእግዚአሔርን ታላላቅ *ሥራዎች* በዓይኖቻቸው አይተዋል። እዚህ ላይ ግን አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በዚህ ዛሬ ባለንበት ዘመንስ እንደቀድሞው ሁሉ እግዚአብሔር እነዚህን ታላላቅ *ሥራዎች* ያደርጋልን? እንደቀድሞ ሁሉ ዛሬስ የመንፈስን ስጦታዎች ለሰዎች ያድላልን?

ለጥያቄው የምንሰጠው መልስ አዎን የሚል ነው። ዛሬም እግዚአብሔር ለአማኞች ጸሎት ምላሽ በመስጠት በመላው ዓለም ታላላቅ ተዓምራትን ያደርጋል፤ ሕሙማንን ይፈውሳል፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነትም፣ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት እየሰጠ ነው። እንደቀድሞው ሁሉ ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል እየሰራ እንደሆነ በፍጹም መጠራጠር የለብንም። ከዚህ ይልቅ በእምነት እንደግ። ጸሐፊው መልእክቱን የጻፈው ለእነዚህ ዕብራውያን ብቻ ሳይሆን፣ ለእኛም ጭምር ነው። ስለዚህም *ከሰማነው ነገር ተንሸራትተን እንዳንወድቅ፣ ስለሰማነው ነገር በጣም መጠንቀቅ አለብን* (ቁ. 1)።

ክርስቶስ ወንድሞቹን መሰለ (2፥5–18)

5 ይህ አሁን የምንኖርበት ዓለም በመላእክት *አገዛዝ* ወይም *ቁጥጥር ሥር* ነው። ከእነዚህ መላእክት አንዳንዶቹ መልካም መላእክት ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን ክፉ ወይም ርኩስ መላእክት ናቸው (ዳን. 10፥20–21፤ 12፥1፤ ዮሐ. 16፥11፤ ኤፌ. 6፥12 ይመለከቷል)። *የሚመጣው ዓለም* ግን በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ እንጂ፣ በመላእክት አይገዛም። የሚመጣው ዓለም ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ሆኖ የሚገዛው የእግዚአብሔር *መንግሥት* ነው። በአንድ በኩል ክርስቶስ *መጀመሪያ* ወደዚህ ምድር በመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔር *መንግሥት* ተጀምሮአል (ማቴ. 12፥28፤ ሉቃ. 17፥20–21 ይመለከቷል)። ይሁን እንጂ፣ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር *መንግሥት* የሚመሠረተው በዓለም መጨረሻ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ነው።

6–8 *ምንም* እንኳ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ መጠን ከመላእክት የበለጠ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር *ለጥቂት ጊዜ ከመላእክት አሳንሶት* ነበር (ቁ. 7)። ክርስቶስ በ*መጀመሪያ* ወደዚህ ዓለም የመጣው ሰው ሆኖ ማለትም፤ ከመላእክት አንሶ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን እግዚአብሔር *የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫነለት* ማለትም፤ ከሞት አስነሳው። *ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር አደረገለት* (ኤፌ. 1፥20–22፤ ዕብ. 1፥13 ይመለከቷል)።

እዚህ ላይ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ከመዝ. 8፥4–6 ይጠቅሳል። ይህ ከመዝሙር መጽሐፍ የተጠቀሰው ምንባብ፣ መጀመሪያ የተጻፈው ስለተራ ሰው ማለትም፤ ስለ ሰው ልጅ ነበር። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ግን በአዲስ መልኩ በመተርጎም፣ ለተራ ሰው የተነገረ ሳይሆን፣ ፍጹም ሰው ለሆነው ለክርስቶስ የተነገረ እንደሆነ ያቀርባል። በተጨማሪም ይህ ምንባብ በክርስቶስ ያመንነው ሁላችንንም የሚመለከት ሊሆን ይችላል። በእምነታችን ምክንያት *የክብርና የምስጋና ዘውድ እንጭናለን*።

ቁጥር 8 በጣም ልናስተውለው የሚገባንን አስፈላጊ እውነት ይዞአል። ሁሉም ኃይልና ሥልጣን በክርስቶስ እጅ ነው። ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል። ሁሉም ነገር ተገዝቶለታል። ይሁን እንጂ፣ ሰይጣንና ክፉ መናፍስቱ ዛሬም ቢሆን በዚህ ዓለም ውስጥ ሲሰሩ እንመለከታለን። በራሳችን ሕይወትም ኃጢአትን እንመለከታለን። እርግጥ ነው ክርስቶስ ሰይጣንን አሸንፎታል፤ ይሁን እንጂ፣ ዛሬም ቢሆን በዚህ ዓለም ክፉ *ሥራውን* በመ*ሥራት* እንዲቀጥል ፈቅዶለታል። ሰይጣን ፈጽሞ የሚጠፋው ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ ብቻ ነው። ምንም እንኳ ሰይጣን በክፉ *ሥራው* ቢቀጥልም፣ አሁንም ቢሆን ዓለምን በበላይነት የሚገዛው ክርስቶስ ነው። *ጠላቶቹን ሁሉ በሥልጣኑ ሥር እስኪያደርግለት ድረስ ክርስቶስ መንገሥ ይገባዋል* (1ቆሮ.

15፥25)። ጠላቶቹ ሁሉ ከእግሩ በታች ሲሆኑ ክርስቶስ ብቻ ነው መንግሥቱን ለእግዚአብሔር የሚያስረክበው፥ (1ቆሮ. 15፥24)።

9 እዚህ ላይ ጸሐፊው በቁጥር 7 አንስቶት በነበረው አሳብ ላይ ሌላ ተጨማሪ አሳብ ያክልበታል። ክርስቶስ የክብርና የምስጋናን ዘውድ የተቀዳጀው *የሞትን መከራ በመቀበሉ* ምክንያት ነው (ፊል. 2፥8–9 እና ገለፃውን ይመለከቷል)። በኃጢአታችን ምክንያት እኛ ልንቀበለው የሚገባንን ቅጣት ለመቀበል ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጣ። ክርስቶስ በእኛ ምትክ ሞተ፣ ለእኛ ሞተ። ስለዚህም ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ራሱን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎአልና እግዚአብሔር ከሞት አስነሳው። *የክብርና የምስጋና ዘውድ ሜነለት* (ቁ. 7)።

10 ኢየሱስ ደህንነታችንን *ያበሰረ* (ቁ. 3) ብቻ ሳይሆን፥ እርሱ ራሱ የደኅንነታችን *ፈጻሚ* ነው። በተቀበለው መከራ ደኅንነትን አስገኘልን። በመከራው *ብዙ ልጆችን* (አማኞችን) ወደ ክብር (ደኅንነት) አመጣ። ክርስቶስ መንገዱን መራን፣ የደኅንነትን መንገድ አሳየን። ክርስቶስ ስለ እኛ መከራን ተቀብሎአልና በእርሱ *ያመንነው* እኛ የክብሩ ተካፋዮች እንሆናለን። ክርስቶስ ክብርን *ያገኘው* መከራን ከተቀበለ በኋላ እንደሆነ ሁሉ፥ እኛም ክብርን የምናገኘው እንደ እርሱ መከራን ከተቀበልን በኋላ ነው።

ለምንድነው እግዚአብሔር ኢየሱስን በመከራ ፍጹም *ሊያደርገው* የፈለገው? ከዚያ አስቀድሞም ቢሆን ክርስቶስ «ፍጹም» ነበር። እዚህ ላይ ግን ትርጉሙ ለየት ያለ ነው፥ የሰው ልጆች አዳኝ እንዲሆን እግዚአብሔር ኢየሱስን ፍጹም ወይም ዝግጁ ማድረግ አስፈለገው ማለት ነው። እርሱ መከራን ባይቀበል ኖሮ ሰዎችን ማዳንና ወደ ክብር ማምጣት ባልሆነለትም ነበር። ይህን በመሰለ መንገድ እግዚአብሔር ኢየሱስን በመከራ *ፍጹም አዳኝ* አደረገው።

11 *ሰዎችን ቅዱሳን የሚያደርጋቸው* ኢየሱስ ነው። በሞቱና በመሥዋዕትነቱ ቅዱሳን አድርጎናል (ዕብ. 10፥10)። በእርሱ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን (ዮሐ. 1፥12)። በዚህ ሁኔታ የክርስቶስ *ወንድሞች* እንሆናለን፣ ከእርሱ *ጋር የአንድ አባት ልጆች ነን*። ለዚህ ነው ኢየሱስ ወንድሞቼ ብሎ ሊጠራን ያላፈረብን (ሮሜ 8፥29 ይመለከቷል)። እኛ በክርስቶስ ካላፈርን እርሱም በእኛ አያፍርም። በእርሱ ካፈርንበት ግን እንዲሁ እርሱም ያፍርብናል (ማቴ. 10፥32–33፣ ማር. 8፥38 ይመለከቷል)።

12 ይህ ቁጥር የተጠቀሰው ከመዝ. 22፥22 ነው። እዚህ ላይ ክርስቶስ የሚናገረው በመዝሙር ጸሐፊው ቃሎች ነው። «*ስምህን ለወንድሞቼ አበስራለሁ*» ይላል። እንግዲህ *ወንድሞቼ* በማለት ጠርቶናል ማለት ነው።

13 እዚህ ላይ ደግሞ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የሚጠቅሰው ኢሳ. 8፥17–18 ነው። በዚህም ቁጥር ቢሆን፥ ክርስቶስ የሚናገረው በነቢዩ ኢሳይያስ አንደበት ነው። «*እምነቴን በእርሱ ላይ በእግዚአብሔር እጥላለሁ*» ይላል። በመስቀል ላይ በሚሞትበት ጊዜ እንኳ፥ ክርስቶስ *እምነቱን* በእግዚአብሔር ላይ ጥሏል። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ሰማይ ከፍ አደረገው። ስለዚህም አሁን «*እነሆኝ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች*» ማለት ይችላል። እኛ አማኞች እግዚአብሔር ለክርስቶስ የሰጠን ልጆች ነን። ኢየሱስ *ወደ ክብር ያመጣን ልጆች* ነን (ቁ. 10)።

14–15 እኛ *ልጆቹ* ማለትም አማኞች *ሥጋና ደም* ያለን ነን፣ እኛን ለማዳንም እኛን መምሰል ተገባው። ሰውን ለማዳን *ሰው መሆንን መካፈል ተገባው* (ቁ. 14)። እንግዲህ ሰው በመሆንና በመሞት ከዚያም በኋላ በመነሳት ብቻ ነው ክርስቶስ *በሞት ላይ ሥልጣን* ያለውን (2ጢሞ. 1፥10፣ ራእ. 1፥18 ይመለከቷል) ዲያብሎስን ማስወገድ የሚችለው። የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው (ሮሜ 6፥23)፣ ሰዎችን ወደ ኃጢአት የሚመራው እርሱ ስለሆነም ዲያብሎስ *በሞት ላይ ሥልጣን* አለው።

ስለዚህም ክርስቶስ ሰው ሆኖ እንደ እኛ ሲሞትና እንደገና ሲነሳ ስናየው፥ በእምነት አማካይነት እኛም ከሞት እንደምንነሳ እናውቃለን (2ቆሮ. 4፥14)። ሞት በእኛ ላይ ሥልጣን አይኖረውም (1ቆሮ. 15፥55፣ 57)፣ ከሞት *ተዋጅተናል*፣ ነፃ ወጥተናል (ቁ. 15)።

ለምንድነው ከእንግዲህ ወዲህ ሞትን መፍራት የሌለብን? ምክንያቱም በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ሞት ወደ ነፃነት፥ ወደ ክብርና ወደ ዘላለም ሕይወት ከዚያም በላይ በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ለመኖር የምንሄድበት መንገድ ነው። ለማያምኑ ግን ሞት ወደ ዘላለማዊ የገሃነም ቅጣት መንገድ ነው።

16 ክርስቶስ ሰው የሆነውና ወደዚህ ዓለም የመጣው መላእክትን ለመርዳት ሳይሆን ሰውን ለመርዳት ማለትም፣ ሰውን ለማዳን ነው። ምን ዓይነት ሰዎችን? *የአብርሃም ዘር* የሆኑትን። እዚህ ላይ ጸሐፊው የሚናገረው ስለ መንፈሳዊ የአብርሃም «ዘር» እንጂ፥ በሥጋ ከአብርሃም ስለተወለዱት ሰዎች (አይሁዳውያን) አይደለም። በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ እውነተኛ የአብርሃም ዘር ናቸው (ገላ. 3፥7፣ 9፣ 29 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

17 የሰዎችን ኃጢአት *ለመደምሰስ* እንደ እኛ ኃጢአትን ካለማድረጉ ውጪ፥ ኢየሱስ በሁሉ ነገር እኛን መምሰል ተገባው (ዕብ. 4፥15)።

ይህን እንደሚገባ ለመረዳት፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን ስለነበረው *ሊቀ ካህን* ማወቅ ይኖርብናል። ለሕዝቡ ኃጢአት ስርየት፥ የአይሁድ ሊቀ ካህን በየዓመቱ ለእግዚአብሔር የእንስሳት መሥዋዕትን ያቀርባል። ሊቀ ካህኑ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ሕዝቡን ወክሎ ነበር። ሕዝቡን ለመወከል ደግሞ ሊቀ ካህኑ ራሱ ሰው መሆን አለበት። በተመሳሳይ መንገድም *ሊቀ ካህንና* አዳኛችን ለመሆን ክርስቶስም ደግሞ ሰው መሆን ተገባው። ለእኛ ኃጢአት ቤዛ እንዲሆን ወደ እኛ መምጣት አስፈለገው። ለሰው ኃጢአት ቤዛ መሆን ያለበት፥ ራሱ ሰው ነው ።

እርሱ ራሱ ምንም ኃጢአት የለበትምና ኢየሱስ ትክክለኛና ፍጹም ሊቀ ካህን ነው። ስለዚህም በቀጥታ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ይችላል። ሰው ስለሆነ *በድካማችን ሊራራልን* የሚችል (ዕብ. 4፥15) *መሃሪ* ሊቀ ካህን ነው።

ኢየሱስ ያቀረበው መሥዋዕት በግ ወይም ፍየል ሳይሆን፥ የገዛ ራሱን አካል ነው። ምንም ዓይነት የኃጢአት ነውር ወይም እድፍ የሌለው ፍጹምና ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ያገኘ መስዋእት ነው። በፍጹም መሥዋዕትነቱ ክርስቶስ የተሟላ የኃጢአት ይቅርታን አስገኘልን (ሮሜ 3፥24–25 እና ማብራሪያውን ይመለከቷል)።

18 በመከራ ውስጥ ያሉትን በተሻለ ሁኔታ መርዳት የሚችሉት ራሳቸው መከራን፣ የተቀበሉት ናቸው። ዛሬ ስለ ክርስቶስ መከራን በመቀበል ላይ ያለን ከሆንን፥ እርሱ ራሱ ስለ እኛ መከራን መቀበሉን አንዘንጋ። አሁንም ቢሆን አብሮን ነው። ሊያቆመን፥ ሊያፀናን፥ ሊያበረታንም ይችላል። ውስጣዊ ሰላምንና ደስታን ይሰጠናል (2ቆሮ. 1፥3–5)።

ስለዚህም በየትኛውም መንገድ ቢሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሊቀ ካህንና ፍጹም አዳኝ ነው። በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ሰላምን አድርጎአል (ሮሜ 5፥1)። ለኃጢአታችን ቤዛነትን አድርጎአል፣ ስለዚህም አሁን በእግዚአብሔር ፊት ጸድቀናል (ሮሜ 3፥24)። ይህም ብቻ አይደለም፣ ኢየሱስ መከራን ተቀብሎአል፥ ተፈትኖአል፣ ስለዚህም በመከራና በፈተና ውስጥ ያሉትን ማጽናናትና ማበርታት ይችላል። ታዲያ እንዲህ ያለውን አዳኝ እንዴት አንወደውም፣ እናመሰግነውም፣ እንዴትስ እናመልከውም!

[3] አብርሃም የመጀመሪያው አይሁዳዊ ነው፤ ስለዚህም በሥጋ አይሁዳውያን ለሆኑት 'የመጀመሪያው አባታቸው ነው። ራሱ ክርስቶስም አይሁዳዊ ስለ ነበር የአብርሃም ዘር ነው (ማቴ. 1፥1)።

ምዕራፍ 3

ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል (3፥1–6)

1 *ስለዚህ . . . ኢየሱስን አስቡ* በየዕለቱ ስለ ኢየሱስ እናስብ፤ ስለ እርሱም እናሰላስል (ዕብ. 12፥2–3 ይመለከቷል)። እዚህ ላይ ኢየሱስ *ሐዋርያና ሊቀ ካህናት* ተብሎአል። እንደ *ሐዋርያነቱ* በሰዎች መካከል የእግዚአብሔር ተወካይ ነው። እንደ *ሊቀ ካህንነቱ* ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት የሰዎች ተወካይ ነው። እንደ ሐዋርያነቱ ለሰዎች እግዚአብሔርን ለመግለጽ ተልኮአል። እንደ ሊቀ ካህንነቱ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆአል።

2 ኢየሱስ ሐዋርያና ሊቀ ካህን አድርጎ *ለሾመው* ለእግዚአብሔር *ታማኝ* ነው። እዚህ ላይ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ኢየሱስን *በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ታማኝ* (ዘኁ. 12፥7) ከነበረው ከሙሴ ጋር ያወዳድረዋል። ሙሴ አይሁዳውያንን ከግብጽ ባርነት ወደ አዲስ ምድር መርቶ ያወጣ ታላቅ አይሁዳዊ መሪ ነበር። ሙሴ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለአይሁዳውያን ሰጠ። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ የእግዚአብሔርና የሰው መካከለኛ እንደሆነ ሁሉ፣ ሙሴም የእግዚአብሔርና የአይሁዳውያን መካከለኛ ነበር።

ለምንድነው የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ኢየሱስን ከሙሴ ጋር የሚያወዳድረው? ምክንያቱም እነዚያ መልእክቱን የሚጽፍላቸው ዕብራውያን ከክርስቶስ እየተመለሱ ነበር። ቀድሞውኑም አይሁዳውያን ነበሩ፤ አሁን ደግሞ ወደ ቀድሞው የአይሁድ ሃይማኖታቸው እየተመለሱ ነው። ስለዚህም ኢየሱስ ከድሮው መሪያቸው ከሙሴ አብዝቶ የሚበልጥ መሆኑን ያሳስባቸዋል። ለመሆኑ፣ ከሚበልጠው ይልቅ ወደሚያንሰው መመለሱ የሚያስገኘው ጥቅም ምንድነው? በማለት እነዚህን አይሁዳውያን የሚጠይቃቸው ይመስላል።

3–4 ሙሴ *በእግዚአብሔር ቤት* ማለትም፤ በአይሁድ ሕዝብ መካከል የእግዚአብሔር ባለ አደራ ነበር። ኢየሱስ ግን ራሱ እግዚአብሔር ነውና *የቤቱ ሰሪ* እና ባለቤትም ነው። ስለዚህም የቤቱ ሰሪ እና ባለቤት የሆነው ኢየሱስ፣ በቤቱ ውስጥ አገልጋይ ከነበረው ከሙሴ ይበልጣል ማለት ነው። አገልጋዮች ቤቱን አይሠሩም። ሁሉን ነገር የሠራ እግዚአብሔር ማለትም፤ ኢየሱስ ነው (ቁ. 4)።

5–6 ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት ታማኝ *አገልጋይ* እንደነበረ ሁሉ፣ ኢየሱስ ደግሞ *እንደ ልጅ ሆኖ በቤቱ* ማለትም በእግዚአብሔር መንግስት ታማኝ ነው። በታማኝ ምስክርነቱና የሕይወት ምሳሌነቱ ሙሴ ስለ ክርስቶስ መስክሮአል። *ወደ ፊት መባል ለሚገባው* ነገር መስክሮአል።

እኛ ቤቱ (የእግዚአብሔር) *ነን* (ቁ. 6)። እኛ አማኞች የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነን (1ቆሮ. 3፥9፤ ኤፌ. 2፥19፤ 22፤ 1ጴጥ. 2፥5)።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ የምንሆነውም *የምንተማመንበትን ነገርና የምንመካበትን ተስፋ አጽንተን ብንይዝ ነው*። ከሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች በብዛት እንደምንመለከተው ሁሉ (ቁጥር 14 ይመለከቷል) እዚህም ላይ የእግዚአብሔር ቤት የምንሆነው በእምነት ጸንተን ከቆመን ብቻ እንደሆነ ተጽፎአል (ከአስተምህሮ ዳሰሳው፣ ደህንነታችንን ማጣት እንችላለንን? የሚለውን ይመለከቷል)። እምነቱን የተወ ሁሉን ነገር አጥቶአል (ማር. 4፥5–6፤ 16–17 ይመለከቷል)።

ስለ አለማመን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (3፥7–19)

7–11 እነዚህ ቁጥሮች የተጠቀሱት ከመዝ. 95፥7–11 ነው። *መንፈስ ቅዱስ እንደሚለው . . .* (ቁ. 7) እነዚህ ቃላት በመጽሐፍ የሰፈሩ ተራ ቃላት ሳይሆኑ፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተነገሩ የራሱ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው።

ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ አውጥቶ በግብጽና በእስራኤል መካከል ወዳለው ሲና በረሃ ወስዷቸዋል። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮች (ለአይሁዳውያን) ተስፋ ወደ ሰጣቸው የእስራኤል ድንበር አድርሶአቸዋል። ይሁን እንጂ፣ በሲና በረሃ በነበሩበት አርባ ዓመት እስራኤላውያን ዘወትር በእግዚአብሔርና በመሪያቸው በሙሴ ላይ ያምጹ ነበር። ይህን በማድረጋቸውም እግዚአብሔርን ተፈታትነዋል፤ ተገዳድረዋል (ቁ. 9)። እንዲህም ሲባል ትዕግሥቱ ምን ያህል እንደሆነ፣ በቁጣ የሚነሳባቸውስ ምን ያህል ኃጢአት ቢሰሩ እንደሆነ ለማወቅ ተፈታተኑት ማለት ነው (ዘጸ. 17፥1–4፤ 7)። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ብዙ ተፈታተኑት፤ በመጨረሻም ቁጣውን አነሳሱ። ስለዚህም እግዚአብሔር እነዚያ አመፀኛና አጉረምራሚ አይሁዳውያን *«ወደምሰጣቸው የዕረፍት ቦታ* ማለትም፤ ለአብርሃም ዘሮች እንደሚሰጥ ተስፋ ወደ ገባላቸው (እስራኤል) ከቶ አይገቡም» (ቁ. 11) በማለት ማለ (ዘኁ. 14፥21–23)።

12 እነዚያ በበረሃ የነበሩት ዓመፀኛ አይሁዳውያን በፈተና እንደ ወደቁ ሁሉ፣ እነዚህ መልእክቱ የተጻፈላቸው ዕብራውያንም በፈተና ለመውደቅ ተቃርበዋል። ስለዚህም ጸሐፊው፤ በበረሃ በኃጢአት የወደቁትን፣ በእግዚአብሔር ላይ ያመፁትን፣ በእርሱ *መታመናቸውንም* የተውትን አይሁዳውያን በፍጹም አትምሰሉ እያለ ያስጠነቅቃቸዋል (1ቆሮ. 10፥1–5)።

እነዚያ ሙሴን የተቃወሙና፣ በእግዚአብሔር *መታመናቸውን* የተው የጥንት አይሁዳውያን፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮች ተስፋ ወደ ሰጣቸው የዕረፍት ምድር ከቶውንም አልገቡም። ይህ የእኛም እጣ ሊሆን ይችላል። በአንድ ወቅት «ካመንን» በኋላ እምነታችንን ከተውንና ክርስቶስን ከተቃወምን *የዕረፍት* ስፍራ ወደ ሆነው መንግሥተ ሰማይ አንገባም።

13 በእምነት ጸንተን እንድንቆም ከተፈለገ፣ በየቀኑ *መመካከርና መረዳዳት* ይኖርብናል። በግላችን ብቻ ክርስቶስን ለመከተል ከሞከርን በፈተና ልንወድቅ፣ ተስፋ ልንቆርጥና እንዲያውም እምነታችንን እንኳ ልንተው እንችላለን። የምንመካከርና እርስ በርስ የምንረዳዳ ከሆንን ግን በእምነት ወደ ፊት እንገሰግሳለን (ዕብ. 10፥25 ይመለከቷል)።

ስለዚህም *«ዛሬ» የተባለው ጊዜ እስካለ ድረስ፣* እርስ በርሳችን እንመካከር፤ እንረዳዳ። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ እየተናገረን ነው። ነገ ድምጹን የምንሰማበት ዕድል ሊኖረን አይችልምና *ዛሬ* እንስማ። ዛሬ ሰይጣን ወደ ፈተና ሊያገባን እንደሚሞክርም በፍጹም መዘንጋት የለብንም። ዛሬ በኃጢአት መታለል ሰይጣን ልባችንን እልከኛ ሊያደርገው ይሞክራል። ዛሬ በመንፈስና በሥጋ መካከል ትግል ላይ ነን (ገላ. 5፥17)። ዛሬ *ዕረፍት* የለንም፤ ጸንተን ከቆምን ግን «ነገ» የዕረፍት ቀናችን ይሆናል።

በኃጢአት መታለል ምንድነው? ራሱን ሸፋፍኖ የሚቀርብ ኃጢአት ነው። አንድን ኃጢአት ለማድረግ ሰይጣን የሚፈትነን «ይህ እኮ በፍጹም ኃጢአት አይደለም» በማለት ነው። አታላይ ነውና ያታልለናል። ያንን ኃጢአት ማድረግ ስንጀምር ደግሞ ይበልጥ እንታለላለን፤ ይበልጥ እንታወራለን። በዚያው ኃጢአት ከቀጠልን ልባችን *እልኸኛ* ይሆናል። ስለዚህም *በኃጢአት ማታለል* ልባችን እልኸኛ እንዳይሆን በየቀኑ እርስ በርሳችን እንመካከር፤ እንረዳዳ (2ጢሞ. 4፥2 ይመለከቷል)።

14 እዚህም ላይ ጸሐፊው *በመጀመሪያ የነበረንን የእምነት ሁኔታ አጽንተን* እንድንይዝ በድጋሚ ያስጠነቅቃል። *እስከ መጨረሻው* ጸንተን እንድንቆም ያስጠነቅቃል (ማር. 13፥13 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። በእምነት ጸንተን ከቆምንና ወደ ኋላም ካልተመለስን፣ *ከክርስቶስ ጋር ወራሾች* ማለትም፤ የክብሩና የርስቱ ተካፋዮች እንሆናለን (ሮሜ 8፥17)።

15–16 እንደገና ጸሐፊው ከመዝ. 95፥7–8 ይጠቅሳል። እነዚያ *ድምፁን ሰምተው* በእግዚአብሔር ላይ *ያመፁ* የጥንት አይሁዳውያን፣ የእግዚአብሔርን ታላላቅ *ሥራዎችና* ተአምራት አይተው ነበር። በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር በተአምራዊ መንገድ አይሁዳውያንን እየመራ *ከግብጽ* አወጣቸው። ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ላይ አምፀዋል፤ በእርሱ *መታመናቸውንም* ትተዋል።

17 ለእርሱ አልታዘዙምና እግዚአብሔር እነዚያን አይሁዳውያን ተቆጣቸው። የተቃወሙትም ሁሉ በበረሃ ወድቀው ቀሩ (ሞቱ) (ዘኁ. 14፥27፤ 29–30)።

18–19 አይሁዳውያን ባለማመናቸ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር እረፍት ማለትም፣ እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ገባላቸው ምድረ እስራኤል ሊገቡ አልቻሉም (ዕብ. 4፥6 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። አለማመን የሰው ልጅ ኃጢአት ሁሉ ምክንያት መሆኑን ከዚህ መመልከት ይቻላል።[4] ምክንያቱም አለማመን እንዳያድነንና እንዳይቀድሰን ከእግዚአብሔር ኃይል ይለየናል። ያለ እምነት ኃጢአትን የምናሸንፍበት ኃይል ሊኖረን አይችልም።

ስለዚህም እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ቃሎች ለእኛም ማስጠንቀቂያ ይሁኑን። እነዚያ የጥንት አይሁዳውያን የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር እንዳዩ ሁሉ፥ እኛም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ክብር አይተናል። እርሱን መከተል ጀምረናል። በእነዚያ የጥንት አይሁዳውያን እንደሆነው ሁሉ ምናልባት የተለያየ ችግርና መከራ ደርሶብን እምነታችን እየተፈተነ ይሆናል። ወንድሞቼና እህቶቼ፥ እነዚያን የወደቁትንና እምነታቸውንም የተውትን የጥንት አይሁዳውያን በፍጹም አንምሰል! ወደ ዕረፍት እንዳንገባ የሚያግደን አንድ ነገር አለ፤ *ያም አለማመን ነው። ወንድሞቼ ሆይ! ከእናንተ ማንም ከሕያው እግዚአብሔር የሚያርቅ ክፉና የማያምን ልብ እንዳይኖረው ተጠንቀቁ* (ቁ. 12)።

ምዕራፍ 4

ዕረፍታችን (4፥1–11)

1–2 እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ምድር የላከው፥ ወደ ዕረፍት እየመራ ማለትም፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲያገባን ነው። በክርስቶስ ያመነን ሁሉ እግዚአብሔር *ወደሰጠን የዕረፍት ቦታ ለመግባት የተቀበልነው ተስፋ ገና የፀና ነው።* ይሁን እንጂ፥ ባለማመናችን ምክንያት እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ገባልን እረፍት ቦታ ላንገባ እንችላለን። ወንጌል ሲሰበክልን መስማት ብቻ በቂ አይደለም፤ የሰማነውን በእምነት መቀበል አለብን (ቁ. 2)። እነዚያ የጥንት አይሁዳውያን የእግዚአብሔርን *መልእክት* ሰምተዋል፤ ሆኖም *በእምነት* አልተቀበሉትም። *የሰሙትን ቃል በእምነት ስላልተቀበሉት አልጠቀማቸውም።*

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ *ከእናንተ ማንም ወደዚህ የዕረፍት ቦታ* ማለትም፣ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት *ሳይገባ እንዳይቀር እንጠንቀቅ* በማለት ያሳስባል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ሳንገባ እንቀር ይሆን? ደኅንነታችንንስ እናጣ ይሆን? በማለት መስጋት እንደሌለብን ይናገራሉ። የዕብራውያን ጸሐፊ ግን ይህ እንዳይደርስብን *እንጠንቀቅ* ነው የሚለው! ክርስቶስ በፍጹም ስለማይተወን ፍጹም መስጋት የለብንም። እኛ ግን ባለማመናችን ምክንያት ክርስቶስን ልንተወው እንችላለን፤ ለዚህ ነው *እንጠንቀቅ* የተባለው። አለማመንን ልንፈራው ይገባል (1ቆሮ. 10፥12 ይመለከቷል)።

3 እስከ መጨረሻው በእምነት የሚፀኑ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ይገባሉ። ዕረፍቱ የእኛ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ዕረፍት ነው። ይህን ዕረፍት እግዚአብሔር *«ዕረፍቴ»* ብሎ እንደተናገረለት ለማሳየት ጸሐፊው እንደገና ከመዝ. 95፥11 ይጠቅሳል (ዕብ. 3፥11)። ከዓለም መፈጠር ወዲህ እግዚአብሔር «ዐርፎአል» ታዲያ እዚህ ላይ የእግዚአብሔር «ዕረፍት» ሲል ምን ማለቱ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

4–5 በስድስት ቀን እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ፤ በሰባተኛውም ቀን ዐረፈ (ዘፍ. 2፥2)። ከዚያን ጊዜ ወዲህ እግዚአብሔር «ዐርፎአል» ጥሪ የቀረበልን የዚያ ዕረፍት ተካፋዮች እንድንሆን ነው ። ባለማመን ምክንያት ግን ያንን ዕረፍት ልናጣ ስለምንችል መጠንቀቅ አለብን።

6 ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔር ዕረፍት ለሁላችንም ተሰጥቶናል። እውነተኛ አማኞች ዛሬም ወደ ዕረፍቱ ይገባሉ። ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የሚያግዳቸው የማያምኑትና የማይታዘዙትን ብቻ ነው።

የጥንት አይሁዳውያን *ባለመታዘዛቸው ምክንያት እግዚአብሔር ወደሚሰጣቸው የዕረፍት ቦታ አልገቡም* በማለት ጸሐፊው ይናገራል። በዕብ. 3፥19 ላይ ግን *ባለማመናቸው ምክንያት* እግዚአብሔር ወደሚሰጣቸው የዕረፍት ቦታ አልገቡም ነበር ያለው። አለማመን በአንድ መልኩ አለመታዘዝ መሆኑን ከዚህ መመልከት ይቻላል (ሮሜ 14፥23 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። ስለዚህም ጸሐፊው በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች የሚያሳየን በመሠረታዊ አሳቡ አንድ ስለሆነ ነገር ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ አለማመን ማለት አለመታዘዝ ማለት ነው። እምቢ፥ አላምንም ማለት ነው። አለማመን በራሱ አለመታዘዝ ብቻ አይደለም፤ ወደ ማንኛውም ዓይነት አለመታዘዝ የሚመራንም ነው። ባለማመኑ ምክንያት የሰው ልጅ ኃጢአትን የሚያሸንፍበት ኃይል ያጣል። ባለማመኑ ምክንያት የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ይለያል። ለዚህ ነው አለማመን የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት እንዳይገባ እንቅፋት ይሆናል የተባለው (ዕብ. 3፥19 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

7 እግዚአብሔር ግን፥ «ዛሬም ቢሆን በንስሐ ለመመለስ ጊዜ አለ» በማለት ይናገራል። *ዛሬ* ወደ እግዚአብሔር እረፍት የመግባት እድል ተሰጥቶናል። *ዛሬ* ድምፁን እየሰማን ነው፤ መስማትም ይገባናል። የደኅንነት ቀን *ዛሬ* (አሁን) ነው (2ቆሮ. 6፥2) «ዛሬ» የተባለው ቀን እስካለ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የመግባትና ደኅንነትን የመቀበል ዕድላችንን አናባክነው። ልባችንን እልከኛ አናድርግ (መዝ. 95፥7–8፤ ዕብ. 3፥13፤ 15)።

8 እነዚያ ዓመፀኛ አይሁዳውያን ከሞቱ በኋላ፥ ቀጥሎ የመጣውን ትውልድ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮች ተስፋ ወደ ገባላቸው ወደ እስራኤል የወሰዳቸው ኢያሱ የሚባል መሪ ነበር (ኢያሱ 1፥1–2)። ወይም ደግሞ ኢያሱ ወደ «እግዚአብሔር ዕረፍት» አደረሳቸው ማለት ይቻላል። ኢያሱ ቀጥሎ የመጣውን ትውልድ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት እንዳገባቸው ሁሉ፥ ኢየሱስም ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ያገባናል።[5] ይሁን እንጂ፥ ለእነዚያ የጥንት እስራኤላውያን ኢያሱ የሰጣቸው «ዕረፍት» ዛሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚሰጠን ዕረፍት በፍጹም ልዩ ነው። ኢያሱ የሰጣቸው ዕረፍት ዘላቂ አይደለም፤ ምክንያቱም ከዚህ ዓለም የሚገኝ ማንኛውም ዕረፍት ዘላቂ አይደለም። ከኢያሱ በኋላ ብዙ ዘመን ቆይቶ የተነሳው ዘማሪው ዳዊትም ወደ ፊት ስለሚመጣው የእግዚአብሔር «ዕረፍት» ጽፎአል። ኢያሱ ከሰጣቸው ዕረፍት ሌላ፥ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጣቸው ወደ ፊት ሌላ ዓይነት ዕረፍት ይመጣል። ኢየሱስ የሚሰጠው ዕረፍት ዘላቂና ዘላለማዊ ነው።

9–10 *እንግዲህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሰንበት ዕረፍት የመሰለ ሌላ ዕረፍት ገና ይቀረዋል።* በእምነት እኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን። እግዚአብሔር ዓለምን በስድስት ቀን ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ወይም በሰንበት[6] ቀን አርፎአል፤ ስለዚህም እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ዕረፍት *የሰንበት ዕረፍትን የመሰለ ዕረፍት* ተብሎአል። ዓለምን ከፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር እንዳረፈ ሁሉ፥ እኛም የዚህ ምድር *ሥራችን* ከተጠናቀቀ በኋላ እናርፋለን።[7] የእግዚአብሔርን ዕረፍት እንካፈላለን። «የእግዚአብሔር ዕረፍት» መንግሥተ ሰማይ እንደሆነ ያለጥርጥር መረዳት ይቻላል። እውነተኛ ዕረፍት በሰማይ ይጠብቀናል። እዚህ ላይ ጸሐፊው የዕብራውያን 3፥12 አሳብን በድጋሚ ያቀርባል።

---

[4] ስለ ኃጢአት ስፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት የሮሜ መልእክት 3፥10–12 ገለጻውንና ግርጌ ማስታወሻውን ይመለከቷል።

[5] በግሪክ ቋንቋ ኢያሱና ኢየሱስ አንድ ትርጉም አላቸው።

[6] ሰንበት በአይሁድ ባሕል መሠረት፥ ቅዳሜ ላይ የሚውል የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን ነው። በአራተኛ ትእዛዝ መሠረት፥ አይሁዳውያን ሰንበትን እንዲያከብሩና ምንም ሥራ እንዳይሠሩ ታዝዘዋል (ዘጸ. 20፥8–11)።

[7] በአንድ በኩል ስንመለከተው እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ አርፎአል። በሌላ በኩል ስንመለከተው ግን እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ አያርፍም። ዓለምና ሁሉም ነገር ጸንተው የተደገፉት በእርሱ ነው። እርሱ ባይደግፋቸው ኖር ሁሉም ይጠፉ ነበር (ዮሐ. 5፥17 ይመለከቷል)።

ኢየሱስ ታላቁ ሊቀ ካህን (4፥12–16)

12 የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እንዳለብን ጸሐፊው አሳስቦናል (ቁ. 7)። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቻውን ግን በቂ አይደለም፤ ልንታዘዘውም ይገባል (ማቴ. 7፥24–27 ይመለከቷል)። የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነው። ቃሉን በተመለከተ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት *«ከአፌ እንደበት የሚወጣው ቃል የምሻውን ሁሉ ሳያደርግና ተልእኮውንም ሳይፈጽም በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም»* ብሎአል (ኢሳ. 55፥11)። *የእግዚአብሔር ቃል ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ ስለታም ነው።* ለሚያምኑ ደኅንነትን ያመጣላቸዋል (ሮሜ 1፥16)። ለማያምኑ ግን ፍርድን ያመጣባቸዋል (ዮሐ. 3፥18)። የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰይፍ ስለታም ነው። እንደ ሰይፍ ሁሉ የሰውን ውስጣዊ አእምሮና ኅሊና ዘልቆ ይገባል።[8] *በልብ ውስጥ የተሰወረውን አሳብና ምኞት መርምሮ የሚፈርድ ነው።* የእግዚአብሔር ቃል የክርስቶስ ቃል ነው። ከዚያም በበለጠ የእግዚአብሔር ቃል ክርስቶስ ራሱ ነው (ዮሐ. 1፥14)። ያ ደኅንነትና ፍርድን የሚያመጣ ቃል፥ ያ የልብን አሳብና ምኞት መርምሮ የሚፈርድ ቃል ክርስቶስ ራሱ ነው። (1ቆሮ. 4፥5 ይመለከቷል)።

13 ኢየሱስ ልባችንን ይመለከታል። ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ ምንም የተሰወረ የለም። አሳብና ምኞታችንን ከሰዎች ወይም ከትዳር ጓደኞችን መሰወር ይቻላል፤ በዚህም ራሳችንንም ልናሞኝ እንችላለን። ከእግዚአብሔር ግን ምንም ነገር መሰወር አንችልም፤ እግዚአብሔርን ልናሞኝ አንችልም። አንድ ቀን ሁሉም ሰው ስለ ራሱ ለእግዚአብሔር የተሟላ ምላሽ ይሰጣል፤ በዚያ ቀን *ሁሉ ነገር ግልጥና እርቃኑን* ይሆናል።

ዛሬ ክርስቶስ «ኑ ተከተሉኝ» ይለናል (ማር. 1፥17)። ምን ዓይነት ምላሽ እየሰጠነው ነው?

14 ኢየሱስ *ታላቅ ሊቀ ካህናታችን* ነው። በዕብ. 2፥17 ላይ ጸሐፊው ኢየሱስን *ታማኝና መሐሪ ሊቀ ካህናት* ብሎታል። ኢየሱስ *ወደ ሰማይ የወጣ* ሊቀ ካህናት ነው። አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል። ወደ ሰማይ የሄደው ስፍራ ሊያዘጋጅልን ነው (ዮሐ. 14፥2)። ያን ስፍራ እንዳናጣ *እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ።*

15 ደካማ መሆናችንን ኢየሱስ ያውቃል። *በሁሉ ነገር እንደ እኛ ስለተፈተነ* ፈተናችን ምን ያህል እንደሚከብድ ይረዳል። ስለዚህም *ሊራራልን የሚችል* ነው (ዕብ. 2፥18)። ያለንበትን ሁኔታ በትክክል ስለሚረዳ እንደ ቅርብ ወዳጅ ልናናግረው እንችላለን።

ኢየሱስ *በሁሉ ነገር እንደ እኛ ተፈተነ*። ኢየሱስ *በሁሉ ነገር ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው* (ዕብ. 2፥17)። ይሁን እንጂ፥ ምንም ኃጢአት አላደረገም። ደኅንነትን የምናገኝበት (ዕብ. 5፥8–9) ፍጹም ሊቀ ካህን የሆነውም ምንም ኃጢአት ባለማድረጉ ነው።

16 እንዲህ ያለ መሐሪና ፍጹም ሊቀ ካህን ስላለን ጸጋ ወደሚገኝበት ወደ *እግዚአብሔር ዙፋን . . . መቅረብ* እንችላለን። ይህም ማለት፤ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ፊት በመተማመን መቅረብ እንችላለን ማለት ነው። *ምሕረትና ጸጋ* እንደምናገኝ እናውቃለንና በእርግጠኝነት ወደ እርሱ እንቀርባለን። አሁን እንኳ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ሆኖ እየማለደልን ነው (ሮሜ 8፥34፤ ዕብ. 7፥25–26)። ስለዚህም ችግርና ፈተና ሲደርስብን፥ በችግራችን ሊረዳን ወደሚችለው ኢየሱስ እንቅረብ እንጂ፥ በፍጹም ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ወይም ለመሰወር አንሞክር።

ምዕራፍ 5

ታላቁ ሊቀ ካህናችን (5፥1–10)

1 አንድ ሰው የአይሁድ ሊቀ ካህን ለመሆን ሁለት ነገሮች ያስፈልጉት ነበር። በመጀመሪያ፥ ሊቀ ካህኑ *ከሰዎች መካከል* ይመረጣል ማለትም፤ እርሱ ራሱ ሰው መሆን አለበት። በሁለተኛ ደረጃ ሊቀ ካህኑ በእግዚአብሔር *ይሾማል*። የሊቀ ካህኑ *ሥራ* ስለ ሰዎች የኃጢአትን ስርየት የሚያስገኝ መባንና መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው። መባንና መሥዋዕትን በማቅረብ ሊቀ ካህኑ የሕዝቡን ኃጢአት ያስተሰርያል።

2 የአይሁድ ሊቀ ካህናት ሰዎች ስለሆኑ፥ እነርሱ ራሳቸው በየጊዜው በኃጢአት ይወድቁ ነበር። *ደካማ* በመሆናቸውም ደንቆሮዎችንና ስህተተኞችን በርህራኄ ሊመለከቷቸው ይችላሉ። ይሁን እንጂ፥ ሆን ብለው ኃጢአት የሚያደርጉትንና በንስሐ የማይመለሱትን ግን በር ኀራኄ አይመለከቷቸውም። በአይሁድ ሕግ መሠረት አውቀው ኃጢአት ለሚያደርጉ ምንም ይቅርታ አይደረግላቸውም (ዘኍ. 15፥27–31፤ ዕብ. 9፥7 ይመለከቷል)።

3 የአይሁድ ሊቀ ካህናት በየጊዜው ኃጢአትን ስለሚፈጽሙ፥ ለሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት ከማቅረባቸው አስቀድሞ ስለ ራሳቸው ኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ይገባቸው ነበር (ዘሌ. 16፥6)። ራሱ ከኃጢአት የነፃ ሊቀ ካህን ብቻ ነው ለሌሎች ኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ የሚችለው።

4 ምንጊዜም ቢሆን፥ ሊቀ ካህናት በእግዚአብሔር ይሾማሉ እንጂ፥ ራሳቸውን አይሾሙም። የሙሴ ወንድም *አሮን* የመጀመሪያው የአይሁድ ሊቀ ካህን ነበር (ዘጸ. 28፥1–2)።

5 በተመሳሳይ ሁኔታም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ተሾመ እንጂ፥ ራሱን ሊቀ ካህን አላደረገም። እግዚአብሔር ክርስቶስን ሊቀ ካህን ብቻ ሳይሆን ልጁም አድርጎታል። እዚህ ላይ ጸሐፊው ከመዝ. 2፥7 ይጠቅሳል።

6 እግዚአብሔር ክርስቶስን *ለዘላለም ካህን* እንዲሆን ሾመው። እዚህ ላይ ግን አንድ ችግር ያለ ይመስላል። እንደሚታወቀው የአይሁድ ሊቀ ካህናት በሙሉ የመጀመሪያው ሊቀ ካህን የአሮን ዝርያዎች ናቸው። ክርስቶስ ግን የአሮን ሳይሆን የስመ ጥሩና የአይሁድ ንጉሥ የዳዊት ዘር ነው። ታዲያ፥ ክርስቶስ እውነተኛ ሊቀ ካህን መሆን የቻለው እንዴት ነው?

እዚህ ላይ መዝ. 110፥4 በመጥቀስ ጸሐፊው መልስ ይሰጣል። ኢየሱስ ሊቀ ካህን የሆነው እንደ አሮን ክህነት ሳይሆን፥ *እንደ መልከ ጼዴቅ የክህነት ሹመት ነው።*

ለመሆኑ መልከ ጼዴቅ ማነው? ከአሮን በፊት ብዙ ዘመን የነበረ የእግዚአብሔር ካህን ነበር። የሳሌም ማለትም የኢየሩሳሌም[9] ንጉሥም ነበር (ዘፍ. 14፥18)። ስለዚህም ካህንም ንጉሥም ነበር ማለት ነው። በኋላም ንጉሥ ዳዊት «የኢየሩሳሌም ንጉሥ» ሆኖአልና ንጉሥ የሆነው *በመልከ ጼዴቅ ሹመት* መሠረት ነው ማለት ይቻላል። ኢየሱስ የተወለደውም ከዳዊት ዘር ስለሆነ እርሱም የተሾመው በመልከ ጼዴቅ ሹመት መሠረት ነው ማለት ነው። ስለዚህም በመልከ ጼዴቅ ሹመት መሠረት ኢየሱስ ንጉሥና ሊቀ ካህን ነው (ቁ. 10)።

7 ቁጥር 1 ላይ ጸሐፊው ሊቀ ካህናት ሰው መሆናቸውን ተናግሮአል። ኢየሱስም እንዲሁ በሊቀ ካህንነት ለማገልገል ሰው መሆን አለበት። በዚህ ቁጥር ላይ ጸሐፊው፥ እንደሰውነቱ አንዱን የኢየሱስን ሕይወት ገጽታ ያቀርባል (ማር. 14፥32–36 ይመለከቷል)።

---

8 ጸሐፊው የእግዚአብሔር ቃል ነፍስንና መንፈስን ጅማትንና ቅልጥምን ይለያል ብሎአል። እንዲህም ሲል ቃሉ በውስጣችን ያለውን ሁሉ ይገልጻል ይመረምራል ማለቱ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በሥጋ ሕይወታችን እንዲሁም በመንፈሳችን ውስጥ ያለውን ያሳየናል። የእግዚአብሔር ቃል ነፍሳችንን ማለትም አእምሮአችንን ውስጣዊ ምኞትና ዝንባሌአችንን ይመረምራል። አንዳንዴ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረግን ይመስለናል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የራሳችንን ስግብግብ ፈቃድ እያደረግን ነው። ነፍሳችን ለፈቃዳችን ትገዛለች፤ መንፈሳችን ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ትከተላለች፤ ብዙ ጊዜ ሁለቱን መለየት አዳጋች ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን እነዚህ ሁለት ፈቃዶችን ይለያል። ጸሐፊው የእግዚአብሔር ቃል ነፍስንና መንፈስን ጅማትንና ቅልጥምን ይለያል ሲል ይህን ማለቱ ነው።

9 ኢየሩሳሌም በጣም ወሳኝ የአይሁዳውያን ከተማ ናት። በአብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን፥ ኢየሩሳሌም ዋና ከተማ ነበረች። ንጉሥ ዳዊትና ሌሎች ብዙ የአይሁድ ነገሥታት የ[illegible]

የሚደርስብንን ፈተናና ድካማችንን ጨምሮ ኢየሱስም እንደኛ ሰው ነበር። ምንም እንኳ የራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፥ እንደ እኛው ሁሉ ማንኛውንም መከራ ተቀብሎአል። ድንጋዩን ወደ እንጀራ መለወጥና ሲርበው መመገብ ይችል ነበር፤ እርሱ ግን ያንን አላደረገም (ማቴ. 4፥2–4)። በተያዘበት ጊዜም *በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የመላእክት ሰራዊት* ደርሰው እንዲታደጉት ማድረግ ይችል ነበር፤ እርሱ ግን ያንን አላደረገም (ማቴ. 26፥53)። ተራ ሰዎች መከራና ስቃይን እንደሚቀበሉ ሁሉ፥ እርሱም መከራና ስቃይን ተቀበለ። እርሱ ራሱ የተለያየ ችግርን ተቀብሎአልና፥ ኢየሱስ በማንኛውም ሁኔታችን ሊራራልን ይችላል (ዕብ. 2፥18፤ 4፥15)።

የኢየሱስ መከራ ከእኛ መከራ ይልቅ እጅግ የከፋ እንደ ነበር እስቲ ለቅፅበት እናስብ። መከራ ሲደርስብን ኢየሱስ አብሮን እንዳለ እናውቃለን፤ በፍጹም ብቻችንን አይደለንም። ኢየሱስ መከራ በተቀበለ ጊዜ፥ በተለይ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ ብቻውን ነበር። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር እንኳ ትቶት ነበር (ማር. 15፥34)።

ጸሐፊው ስለ ኢየሱስ ሲናገር *በትህትና በመታዘዙም እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰማው* ይላል። በመስቀል ላይ ከመሞት እንዲድን ኢየሱስ ጸልዮ ነበር (ማር. 14፥35–36)። እግዚአብሔር ግን ያን ጸሎት አልተቀበለውም። እርግጥ ነው እግዚአብሔር ከሞት ሊያድነው ይችል ነበር፤ እንደዚያ ግን አላደረገም። ይሁን እንጂ፥ ከሦስት ቀን በኋላ ከሞት በማስነሳት እግዚአብሔር የኢየሱስን ጸሎት መልሶለታል።

8 ምንም እንኳ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፥ *ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ*። ምን ማለት ነው? ብዙውን ጊዜ ሰዎች ባለመታዘዛቸው ከሚደርስባቸው መከራ ነው መታዘዝን የሚማሩት። ኢየሱስ ግን አንድም ጊዜ እንኳ በእግዚአብሔር ፈቃድ አላመፀም። እንዲያውም በመታዘዙ ነበር ያ ሁሉ መከራ የደረሰበት። ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ተማረ። ለእግዚአብሔር ፈቃድ በሚታዘዙት ላይ የሚደርሰውን መከራ እርሱ ራሱ ቀመሰ።

እነዚህ መልእክቱ የተጻፈላቸው ዕብራውያን ክርስቲያኖች፥ ለክርስቶስ በመታዘዛቸው አንዳንድ መከራ ይደርስባቸው ጀምሮአል። በዚህም ምክንያት በእምነታቸው እየተዳከሙ ነው፤ ክርስቶስን ወደ መካድም ደርሰዋል። ስለዚህም እስከ መጨረሻው ድረስ በመታገስ መከራ የተቀበለውን ክርስቶስን ማሰብ አለባቸው።

9 በመታዘዙ ኢየሱስ *ፍጹም* ሆኖ ተገኘ (ዕብ. 2፥10)። በሁሉም ነገር ታዛዥ ሆነ። ምንም ኃጢአት አላደረገም። ስለዚህም ፍጹም ሊቀ ካህን ነውና *ለሚታዘዙት ሁሉ የዘላለም ደኅንነት ምክንያት ሆነላቸው*። በመታዘዙ *የዘላለም ደኅንነት ምክንያት* ሆነ። እኛም ለእርሱ በመታዘዝ[10] ነው ያንን ደኅንነት ማግኘት የምንችለው።

ለሚታዘዙት ሁሉ ማለትም ለሚቀበሉት ሁሉ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ምንጭ ነው። ከሁሉ በፊት እምነት ይቀድማል፤ ያለ እምነት ለክርስቶስ መታዘዝ አንችልም። በዚያው ሁኔታ ደግሞ ያለመታዘዝ እውነተኛ እምነት ሊኖር አይችልም (ያዕ. 2፥14–17 ይመለከቷል)። እምነትና መታዘዝ በአንድነት ለደኅንነት አስፈላጊ ናቸው።

10 ቁጥር 6 እና ገለጻውን ይመለከቷል።

ወተትና እና ጠንካራ ምግብ (5፥11–14)

11–12 ይህ መልእክት የተጻፈላቸው ዕብራውያን፥ በእምነታቸው ለማደግ ዘገምተኞች ነበሩ። ገና መንፈሳዊ ሕጻናት ናቸው (1ቆሮ. 3፥1–2)። *የእግዚአብሔርን ቃል የመጀመሪያ ትምህርት* እንኳ እንደሚገባ አልተረዱም (ቁ. 12)።

የእግዚአብሔር ቃል ሁለት ነገሮችን ያጠቃልላል፥ *ወተትና ጠንካራ ምግብን* (ማቴ. 4፥4 ይመለከቷል) «ወተት» በእምነታቸው ሕፃናት ለሆኑት ነው (1ጴጥ. 2፥2)። «ጠንካራ ምግብ» ደግሞ በእምነት ላደጉት በሳል አማኞች ነው።

13 እንግዲህ በመንፈሳዊ አነጋገር ስንመለከተው፤ እነዚህ ዕብራውያን የሚኖሩት *በወተት* ብቻ ነበር ማለት ነው። በመጠኑም ቢሆን በመጀመሪያ ማደግ ጀምረው ነበር፤ አሁን ግን እድገታቸው ባለበት ቆሟል። እንደ ሕፃን ሁሉ ወተትን መጋት ቀላል ሆኖ አግኝተውታል!

ለማደግ *ጠንካራ ምግብ* ያስፈልገናል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ *የጽድቅ ትምህርት* ያስፈልገናል። እዚህ ላይ ጸሐፊው፤ ለጽድቅ መከራን ለመቀበል የሚያዘጋጀን ትምህርት ያስፈልገናል ማለቱ ነው (ማቴ. 5፥10፤ 2ጢሞ. 3፥12)። እነዚህ ዕብራውያን ግን በዚህ መንገድ መከራን ለመቀበል ዝግጁ አይደሉም። ስለ እውነተኛ ጽድቅ የሚገባቸውን ያህል አልተረዱም።

14 እዚህ ላይ *ጠንካራ ምግብ* ሲል አስቸጋሪና ጥልቅ የክርስቶስ ትምህርቶች ማለቱ ነው። እንዲህ ያለውን «ምግብ» ስንመገብ በክርስቶስ እናድጋለን። በክርስቶስ ስናድግ ደግሞ የበለጠ *መልካሙንና ክፉውን* የመለየት ልምድ ይኖረናል። በራሳችን ሕይወት ያለውን ኃጢአትና በክርስቶስ ሕይወት ያለውን መልካምነት አጥርተን እናያለን። በእምነት ስናድግ፥ የክርስቶስን ጽድቅ ይበልጥ መረዳትና መከተል እንችላለን። በዚህ መልክ ለማደግ ግን *ጠንካራ ምግብ* ያስፈልገናል። ወተትን በመጋት ብቻ በሳል ክርስቲያኖች መሆን አይቻልም!

ምዕራፍ 6

እምነትን ስለ መተው የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (6፥1–12)

1 ምንም እንኳ እነዚህ ዕብራውያን ገና «ወተት» እየተጋቱ ቢሆንም ጸሐፊው «ጠንካራ ምግብ» ማለትም የላቀውንና አስቸጋሪውን የክርስትና ትምህርት ሊሰጣቸው ይፈልጋል። በእምነታቸው ማደግ የሚችሉት ጠንካራ ምግብንም ሲያገኙ እንደሆነ ጸሐፊው በሚገባ ያውቃል (ዕብ. 5፥14)። እንግዲህ . . . *ፍጹም ወደ ሆነው ትምህርት እንለፍ* ይላል ጸሐፊው። በክርስትና ሕይወት ወይ ወደ ፊት የመጓዝ ወይም ደግሞ ወደ ኋላ የመመለስ እንጂ፥ ባሉበት ስፍራ የመቆም ሕይወት የለም። ለረጅም ጊዜ በተወሰነ መንፈሳዊ ደረጃ መሆን አይቻልም። እንደ ዛፍ ሁሉ እናድጋለን ወይም እንሞታለን።

የክርስትና እምነታችን *መሠረት* አንዴ ተመሥርቶአልና ሌላ መሠረት አያስፈልገንም። ቁጥር 1 ላይ ጸሐፊው ደግመን መመሥረት ስለማይገባን *የመሠረቱን* ሁለት ክፍሎች ይናገራል። የመጀመሪያው *ከሞተ ሥራ ንስሐ መግባት* ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ *በእግዚአብሔር ማመን* ነው። እነዚህ ሁለት ነገሮች የክርስትና ሕይወታችን ሁለት የመጀመሪያ ደረጃዎች ናቸው (ማር. 1፥15፤ የሐዋ. 20፥21 ይመለከቷል)። ደግመን ደጋግመን ስለ እነዚህ ሁለት ነገሮች መማር የለብንም።

የሞተ ሥራ የተባሉት ኃጢአቶቻችን ናቸው። የኃጢአት ውጤት ሞት ማለትም መንፈሳዊ ሞት ነው (ሮሜ 6፥21፤ 23)። እዚህ ላይ *ንስሓ* ሲል ለእነዚህ *ሥራዎችና* ኃጢአቶች ይቅርታን መለመን ብቻ ሳይሆን፥ የኃጢአት *ሥራዎችን* እርግፍ አድርጎ መተው ማለት ነው።

ደኅንነትን ለማግኘት *በእግዚአብሔር ማመን* አስፈላጊ መሆኑን ጸሐፊው ከላይ አመልክቶአል። እዚህ ላይ

---

[10] እዚህ ላይ የመታዘዝ መጀመሪያውና መሠረቱ እምነት ራሱ እንደሆነ መረዳት አለብን። (ዕብ. 4፥6 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። እውነተኛ እምነት ካለ ያ እምነት በሌላው ነገር ሁሉ በመታዘዝ ይገለጣል። *የአንድ መቀስ ሁለት ስለቶች ስለሆኑ እምነትና ሥራን መለያየት አይቻልም*። ስለዚህም በመታዘዝ ድነናል ስንል፥ በክርስቶስ በማመን ድነናል ማለታችን ነው። ሁለቱም እውነት ናቸው። ይሁን እንጂ፥ በሥራና በመታዘዝ ብቻ ድነናል ማለት አይደለም። የዳንነው በሥራ አይደለም፤ ይልቁንም፥ እምነታችንን በመታዘዝ በመግለጣችን ነው (ገላ. 5፥16፤ ኤፌ. 2፥8–10፤ ያዕ. 2፥14፤ 17፤ 20–24 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)። በተጨማሪም እምነት ራሱ የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ ነው። ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ ደኅንነታችን የእግዚአብሔር ጸጋ ሥራ ነው። ሰፋ ላለ ማብራሪያ ከአስተምህሮ ዳሰሳው የደኅንነት መንገድ የሚለውን ይመለከቷል።

በእግዚአብሔር ማመን ሲል ደኅንነትን በምናገኝበት በክርስቶስ (ዕብ. 5፥9) ማመን ማለቱ ነው።

2 ቁጥር 1 ላይ ጸሐፊው ስለ ክርስትና እምነታችን *መሠረት* ሁለት ክፍሎች ተናግሮአል። እነርሱም *ንስሐ* እና እምነት ናቸው። አሁን ደግሞ ቁጥር 2 ላይ ስለ ሌሎች አራት *የመሠረቱ* ክፍሎች ይጽፋል። አንዴ ስለ እነዚህ *ነገሮች መመሪያ* ከተቀበልን *ደግመን ደጋግመን መመሪያ* ማግኘት የለብንም።

አራቱ ተጨማሪ የክርስትና እምነታችን *መሠረቶችም*፥ በመጀመሪያ *ጥምቀቶች*፥ ሁለተኛ *እጅ መጫን*፥ ሦስተኛ *ከሞት መነሳት*፥ አራተኛ *የዘላለም ፍርድ* ናቸው። በቁጥር 1 ላይ የተጠቀሱት ሁለቱን ጨምሮ፥ እነዚህ አራት ነገሮች የክርስትና ሕይወታችን አቢይ አስተምህሮዎችና የሕይወታችን *መሠረቶች* ናቸው። አንድ ጊዜ *መሠረቱ ተመሥርቶአልና* ሌላ *መሠረት* አያስፈልግም።

እጅ *መጫን* አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ፥ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን *ሥርዓት* ነው። እጅ *መጫን* ሰዎች *መንፈስ ቅዱስን* እንዲቀበሉ ለማድረግ፥ *ለመንፈሳዊ ሥራ ለመሾም* ወይም ሕሙማንን *ለመፈወስ* የሚደረግ *ሥርዓት* ነው (የሐዋ. 6፥6፤ 8፥17፤ 9፥12፤ 17፤ 19፥6)። እጆችን *መጫን* እምነት ያፀናል እንጂ፥ በራሱ እነዚህን ነገሮች የሚፈጽምበት አስማታዊ ኃይል የለውም።

3 ቁጥር 1 ላይ ጸሐፊው *ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን* (ከቁጥር 1–2 የተዘረዘሩትን *የመጀመሪያ* ትምህርቶች) ፍጹም ወደ ሆነው ትምህርት እንለፍ ብሎ ነበር። እንግዲህ የእምነታችን *መሠረት ተመሥርቶአልና*፤ በላዩ ላይ እንገንባበት እንጂ፥ እንደገና በመገንባት ጊዜ አናባክን። ስለዚህም ጸሐፊው *እግዚአብሔር ቢፈቅድልን ይህን እናደርጋለን* ይላል። ማንኛውንም ነገር ማድረግ የምንችለው በእግዚአብሔር ፈቃድ እና ጸጋ በመሆኑ ጸሐፊው *እግዚአብሔር ቢፈቅድልን* አለ።

4–6 እዚህ ላይ ጸሐፊው *የመጀመሪያውን* ትምህርት ድጋሚ *መመሥረት* አስፈላጊ ያልሆነበትን ምክንያት ይገልጻል። ምክንያቱም ይህ ነው፥ አንድ ሰው እነዚህን *የመጀመሪያ* ትምህርቶች በተለይም ስለ ንስሐና እምነት የተሰጡትን ትምህርቶች ከተማረ በኋላ (ቁ. 1) እንደገና *ከመንገድ* ቢወጣ ያን ሰው ወደ ንስሐ *መመለስ* አዳጋች ነው (ቁ. 6) *መሠረቱን* እንደገና *መመሥረት* አይቻልም።

ከ4–6 ባሉት ቁጥሮች ላይ በጣም ጠቃሚ አስተምርህሮዎችን እናያለን። ጸሐፊው ብርሃን የበራላቸውን (የወንጌልን *ብርሃን ያዩትን*)፥ *ሰማያዊውን ስጦታ የቀመሱትን* (የክርስቶስን በረከት)፥ *የመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች የነበሩትን* (ቁ. 4)፥ *የእግዚአብሔርን መልካም ቃልና የሚመጣውን ዓለም ኃይል ስለ ቀመሱ* (ቁ. 5) አንዳንድ ሰዎች ይናገራል። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ጸሐፊው የሚናገረው፥ ስለ እውነተኛ ክርስቲያኖች ይመስላል። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ሆን ብለውና አውቀው እምነታቸውን *መተው* እንደሚችሉ ጸሐፊው ይናገራል። ይህን ካደረጉና *ከመንገድ ከወጡ* ግን ተስፋ የላቸውም፥ *ወደ ንስሐ መመለስ* አይቻልም።

ከመንገድ የወጡ ሲል ምን ማለቱ ነው? እዚህ ላይ ጸሐፊው የሚናገረው ጥቃቅን ኃጢአቶችን ስለ ማድረግ ወይም ደግሞ አልፎ አልፎ ማንኛችንም እንደምናደርገው ለአጭር ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለመሳት አለመሆኑ ግልፅ ነው። ከዚህ ይልቅ ከሁሉም ስለሚበልጠውና አስፈሪ ስለሆነው ኃጢአት ነው። ያም ኃጢአት የእግዚአብሔርን ብርሃን ካየን በኋላ ችላ ማለት፥ የክርስቶስን ስጦታዎችና በረከቶች ከተቀበልን በኋላ ክርስቶስን ችላ የማለት ኃጢአት ነው። ይህን የሚያደርጉ *የእግዚአብሔርን ልጅ እንደገና ይሰቅሉታል* (ቁ. 6)። እንዲህ ያሉ ሰዎች ንስሐ የማድረግ ፍላጎትም የላቸውም፤ ልባቸው ደንድኖአል፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ሊነካቸው አይችልም።[11] እንዲህ ያሉ ሰዎች በማር. 3፥28–29 የተጠቀሰውን ምንም ይቅርታ የሌለውን መንፈስ ቅዱስን የመሳደብ ኃጢአት ፈጽመዋል። ይህን ኃጢአት ሐዋርያው ዮሐንስ *ለሞት የሚያደርስ ኃጢአት* ይለዋል (1ዮሐ. 5፥16)። በክርስቶስ የሚገኘውን ደኅንነት የሚንቁ ሰዎች ከየትም ቦታ ደኅንነትን አያገኙም (ዕብ. 10፥26–27፤ 2ጴጥ. 2፥20–21 ይመለከቷል)። ለወደቁት ክርስቶስ ተስፋን ይሰጣል፤ ከእርሱ ተለይተው ለወደቁት ግን ምንም አያደርግላቸውም።

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ይነሳል። አንድ እውነተኛ ክርስቲያን እምነቱን መተውና ደኅንነቱን ማጣት ይችላል? አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚሰጡት መልስ አዎን ይችላል የሚል ነው። ማስረጃ እንዲሆናቸውም በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን *የመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች* (ቁ. 4) የነበሩትን ሆኖም ከእምነት የወጡትን ሰዎች እንደምሳሌ ያቀርባሉ። የመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች መሆን የሚችሉት እውነተኛ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ደግሞ አንድ እውነተኛ ክርስቲያን በፍጹም ደኅንነቱን አያጣም፤ ብለው ያምናሉ። ለዚህ እምነታቸው ድጋፍ እንዲሆናቸውም ከቁጥር 4–6 ባሉት ላይ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ማስጠንቀቂያ እየሰጠ እንጂ፥ እውነተኛ ክርስቲያኖች ለዘለቄታው ከመንገድ ይወጣሉ፤ ለዘለቄታውም ደኅንነታቸውን ያጣሉ ማለቱ አይደለም ይላሉ። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ይህን ያለው፥ ኃጢአት ያደርጉ የነበሩትንና በእምነት የደከሙትን አማኞች፥ ከመንገድ እንዳይወጡ ለመምከርና ለማበረታታት ብቻ ነው ይላሉ።

ሆኖም አንድ ያልተመለሰ ጥያቄ ይኖራል። ለመሆኑ እውነተኛ ክርስቲያንና ሐሰተኛ ክርስቲያንን እንዴት ነው ለይተን የምናውቀው? ብዙውን ጊዜ በፍጹም መለየት አይቻልም። እስቲ፥ ለምሳሌ ያህል በክርስቶስ እናምናለን የሚሉ፥ እውነተኛ ክርስቲያን መስለው የሚታዩ ሁለት ሰዎችን እንውሰድ። ከሁለቱ አንዱ ቢወድቅ፥ ያ ሰው እንደሚወድቅ አስቀድሞ የሚያውቅ ሰው አይኖርም። ኢየሱስ ዘር ለመዝራት ስለወጣው ሰው ከተናገረው ምሳሌ እንደምንመለከተው፥ አንዳንዱ ፍሬ *በጭንጫማ* መሬት ላይ ወደቀ፤ አንዳንዱ ደግሞ *በእሾኻማ* መሬት ላይ ወደቀ። በመልካም መሬት ላይ እንደወደቀው ፍሬ ሁሉ፥ መጀመሪያ እነዚህ ፍሬዎችም በፍጥነት ፍሬ ማፍራት ጀምረው ነበር (ማር. 4፥5–7)። የፀሐይ ሙቀት ከወጣ በኋላ (ስደት)፤ እሾህ ከመጣ በኋላ (ፈተና) ነበር በመልካም መሬት የተዘራውን በመጥፎ መሬት ከተዘራው ለይቶ ለማወቅ የተቻለው። በመጀመሪያ ሁሉም ዘሮች እኩል በደህና ማደግ ጀምረው ነበር። በኋላ ነው በጭንጫማ መሬት የተዘራውና በእሾኻማ መሬት የተዘራው ዘር መሞት የጀመሩት።

በተመሳሳይ መንገድም አንድ ሰው ችግርና ፈተና ሲደርስበት ከእምነቱ ካፈገፈገና ከወደቀ ብቻ «እውነተኛ ክርስቲያን አይደለም» ማለት እንችላለን። ከዚያ በፊት ግን የማንንም እምነት መጠራጠር የለብንም። ችግርና መከራ ሲመጣ፥ ሐሰተኛው ክርስቲያን ይወድቃል። እውነተኛው ክርስቲያን ግን ፀንቶ ይቆማል። በትክክለኛው ጊዜም (በመልካም አፈር ላይ እንደተዘራው ዘር) ያድጋል፤ ፍሬም ይሰጣል (ማቴ. 7፥24–27፤ 13፥24–30 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)።

እዚህ ላይ አንድ ተጨማሪ ነገር ማከል አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ለጊዜው ጨርሶ የወደቁ መስለው ይታያሉ። በኃጢአት ይወድቃሉ። እምነታቸውም ይጠወልጋል። ይሁን እንጂ፥ ጨርሶ አልወደቁም። ውስጣዊ አእምሮአቸውና ኅሊናቸው እየወቀሳቸው ነው፤ በንስሐ ለመመለስም ይፈልጋሉ። ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ተስፋ አላቸው። ሙሉ በሙሉ ክርስቶስን ችላ አላሉትም። ይሁን እንጂ፥ ለረጅም ጊዜ በንስሐ ሳይመለሱ ከቆዩ ምናልባት ወደ ክርስቶስ የመመለስን ዕድል እንኳ ላያገኙ ይችላሉ። ስለዚህም ያሉት በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነው ማለት ነው።

«እኔ በፍጹም አልወድቅም» ብለን ጨርሶ መመካት የለብንም። የቆመ የሚመስለው ሰው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ (1ቆሮ. 10፥12) የሚለውን የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ማስታወስ አለብን። የእግዚአብሔርን ጸጋ ልንንቅና

---

[11] እርግጥ ነው እግዚአብሔር ሊነካቸው ይችላል፤ ወደ ንስሐም ሊያመጣቸው ይችላል። *ለእግዚአብሔር ሁሉ ነገር ይቻለዋል*፤ (ማር. 10፥27)፤ ይሁን እንጂ፥ እግዚአብሔር ላይነካቸውም ይችላል። በረከቱን የቀመሱትንና ሆን ብለው የካዱትን ሰዎች እግዚአብሔር ወደ ንስሐ ላያመጣቸውም ይችላል።

ክርስቶስንም ልንክድ እንችላለን። እስከ መጨረሻው ጸንቶ የሚቆመውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው።[12]

7–8 እውነተኛ ክርስቲያኖችን ከሐሰተኞቹ ለይተን የምናውቀው፣ በፍሬያቸው ነው (ማቴ. 7፥17–20 ይመለከቷል)። በዋነኛነት ደረጃ እነዚህ ፍሬዎች የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው (ገላ. 5፥22–23)። *ክርስቶስ ፍሬ እንድታፈሩ፣ ፍሬአችሁም ነዋሪ እንዲሆን መረጥኋችሁ* አለ (ዮሐ. 15፥16)። የመረጠን፣ የመጨረሻ ዕጣው *መቃጠል* የሆነውን እሾኽ ወይም አሜኬላ እንድናፈራ አይደለም (ቁ. 8)።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ፍሬ ማፍራት ማለት መስበክ፣ ትንቢት መናገር፣ ተአምራትን ማድረግ እንደሆነ ያስባሉ፤ እነዚህ ነገሮች እውነተኛ ክርስቲያኖች ለመሆናችን ማስረጃ ናቸው ይላሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሰይጣንና ርኩሳን መናፍስቱ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ (ማር. 13፥22)። አንድ እውነተኛ ፍሬ ብቻ አለ፤ ይኸውም በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የሚያፈራው ፍሬ ነው (ማቴ. 7፥22–23 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

9 ጸሐፊው ለእነዚህ ዕብራውያን ፅኑ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ፈጽሞአል። አሁን ለስለስ ደግሞ እንደማይወድቁ ያለውን ተስፋ ይገልጽላቸዋል።

10 ለእርሱ ላቀረብነው «ፍሬ» ማለትም ለፍቅርና ለታማኝነት ፍሬያችን፣ ተገቢውን ሽልማት መስጠቱን እግዚአብሔር በፍጹም አይዘነጋም።

እነዚህ ዕብራውያን ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር እንዴት ነው የገለጡት? ቅዱሳንን ማለትም አማኞችን በመርዳት ነበር። ለእግዚአብሔር ሕዝብ የምናደርገው ማንኛውም የፍቅር ሥራ ለራሱ ለእግዚአብሔር እንዳደረግነው ነው የሚቆጠረው (ማቴ. 25፥34–40)።

11–12 ጸሐፊው *ሁላችሁም በተስፋ የምትጠባበቁትን ነገር እስክትጨብጡ ድረስ ትጋታችሁን እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ ብሏቸዋል*። ማለትም በቁጥር 10 የጠቀሰውን ለእግዚአብሔር ባሳዩት ፍቅር እንዲገፉበት ያለውን ምኞት ይገልጽላቸዋል። ለምንድነው ትጋታቸውን እስከመጨረሻ ድረስ እንዲያሳዩ የሚያበረታታቸው? ምክንያቱም *ተስፋቸውን እንዲጨብጡ* ነው። *በተስፋ የሚጠብቁትን ነገር* እንደሚያገኙ ቃል ተገብቶላቸዋል (ቁ. 12)። እግዚአብሔርን መውደዳቸውን ከቀጠሉ፣ እስከ መጨረሻውም ለእርሱ ታማኝ ከሆኑ፣ በሰማይ የሚጠብቃቸውን ርስት ማግኘታቸው የተረጋገጠ ነው (ማር. 13፥13፤ ገላ. 6፥9፤ 2ጴጥ. 1፥10–11 ይመለከቷል)። *በእምነትና በትዕግሥት ብቻ ነው የምንጠብቀውን ነገር* ማለትም በሰማይ የዘላለም ሕይወትን የምናገኘው። ጳውሎስ በተናገረው ቃል ለማጠቃለል፤ *እያንዳንዳችሁ ያላችሁን እምነት ፍጹም ለማድረግ በፍርሃትና በአክብሮት ተግታችሁ ሥሩ* (ፊል. 2፥12)።

የእግዚአብሔር ተስፋ እርግጠኝነት (6፥13–20)

13–15 እግዚአብሔር ለአብርሃም «*ዘርህን አበዛዋለሁ፤ ታላቅ ሕዝብም ይሆናል፤ እባርክሃለሁ*» የሚል ተስፋ ሰጠው (ዘፍ. 12፥2)። በዚያ ጊዜ ግን አብርሃም ሰባ አምስት ዓመቱ ነበር፤ ምንም ልጅ አልነበረውም። ታዲያ፣ አንድም ልጅ እንኳ ሳይኖረው *የታላቅ* ሕዝብ አባት የሚሆነው እንዴት ነው?

ልጅ ከመውለዱ በፊት አብርሃም ሌላ ተጨማሪ ሃያ አምስት ዓመት መቆየት ነበረበት። አንድ መቶ ዓመት ሲሆነው፣ የአብርሃም ሚስት ይስሐቅን ወለደች። ስለዚህም በይስሐቅ አማካይነት እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ይፈጽማል (ዘፍ. 17፥15–17፤ 21፥1–3)። ይህን በመሰለ ሁኔታ *አብርሃም በትዕግሥት ጠብቆ ተስፋ የተደረገለትን ነገር አገኘ* (ቁ. 15)።

ከዚያ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት ፈተነ። ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋለት ነገረው። *ያም* ማለት ብዙ ዓመት ታግሶ ያገኘውን ልጁን ይስሐቅን እንዲገድል ነገረው ማለት ነው! አብርሃም በመታዘዝ ልጁን መሥዋዕት ለማድረግ ተዘጋጀ። የአብርሃምን እምነትና መታዘዝ እግዚአብሔር ከተመለከተ በኋላ በመጨረሻው ልጁን መሥዋዕት ከማድረግ አገደው (ዘፍ. 22፥1–14)። በዚያው ወቅት አስቀድሞ የሰጠውን ተስፋ በድጋሚ አጸናለት (ዘፍ. 22፥15–18)። በዚህ ጊዜ ግን «*በእርግጥ እባርክሃለሁ፤ ዘርህንም አበዛዋለሁ*» በማለት እግዚአብሔር በራሱ ምሎ ነበር ተስፋውን ያጸናለት (ቁ. 14)። እዚህ ላይ ጸሐፊው የሚጠቅሰው ከዘፍ. 22፥16–17 ነው።

16–17 የእግዚአብሔር ቃል የተረጋገጠ ነው። እዚህ ላይ ግን እግዚአብሔር ቃሉን ወይም ተስፋውን *በመሃላ አጸና* (ቁ. 17)። ስለዚህም ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ይበልጥ አረጋግጦለታል! ለምንድነው እግዚአብሔር ተስፋውን በመሃላ ያጸናው? ምክንያቱም *ውሳኔው የማይለወጥ መሆኑን ለተስፋው ወራሾች ለማስረዳት ፈልጎ ነው*። *የተስፋው ወራሾችስ* እነማን ናቸው? እኛ በክርስቶስ የምናምነው ነን። በእምነት አማካይነት እውነተኞቹ መንፈሳዊ የአብርሃም ወራሾች ነን (ገላ. 3፥7፤ 9)። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለትን ተስፋ አሁን ለእኛ ተሰጥቶናል። እኛ በክርስቶስ የምናምነው የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆነናል። ስለዚህም በሰማይ ሙሉ ርስት እንቀበላለን።

18 እኛ *የሸሸነው* ማለትም ከክፋት፣ ከሰይጣን የሸሸነው *በፊታችን ያለውን ተስፋ* እናገኛለን። መንፈሳዊ የአብርሃም ወራሾች እንደመሆናችን መጠን፣ ተስፋው በሰማይ የምንቀበለው ርስት ነው። ያንን ተስፋ በፍጹም እምነት እንይዛለን። ተስፋው *የማይነቃነቅና አስተማማኝ* ነው (ቁ. 19)። ምክንያቱም ያ ተስፋ *በሁለቱ ነገሮች አማካይነት* ማለትም በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መሃላ የጸና ነው። ስለዚህም *ብርቱ መጽናናት እናገኛለን*።

19 በችግርና በመከራ መካከል፣ ሌላው ቀርቶ ሞት ዙሪያውን ቢያንዣብብም እንኳ፣ ይህን ተስፋ ይዘን መቆም እንችላለን። ተስፋችን በእግዚአብሔር ዘንድ የመልሕቅን ያህል *የማይነቃነቅ አስተማማኝ* ነው።

እዚህ ላይ ጸሐፊው ተስፋችን *መጋረጃውን አልፎ ወደ መቅደስ* ማለትም እግዚአብሔር ወዳለበት ስፍራ *ይገባል* ይላል። መቅደስ[13] (ዕብ. 9፥1–3)። አይሁዳውያን እግዚአብሔር ይኖርበታል ብለው የሚያስቡት ስፍራ ነው። በዓመት አንድ ቀን ሊቀ ካህኑ የሕዝቡን ኃጢአት ለማስተሰረይ ወደ መቅደሱ ውስጠኛው ክፍል ይገባል (ዕብ. 9፥7)። ስለዚህም የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ተስፋችን መጋረጃውን አልፎ ወደ መቅደስ ይገባል ሲል፣ ተስፋችን የተመሠረተው በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ነው ማለቱ ነው።

20 ኢየሱስ እኛን ቀደሞ ወደ መቅደስ ማለትም ወደ ሰማይ ገብቶአል። ወደ ሰማይ ወደ እግዚአብሔር ፊት የወጣው ለኃጢአታችን መሥዋዕት ለመሆን ነው። *በመልከ ጼዴቅ የክህነት ሹመት* መሠረት ኢየሱስ እውነተኛና ዘላቂ ሊቀ ካህናችን ሆኖአል (ዕብ. 5፥6፤ 10)። ኢየሱስ ተስፋችን የጸናበት ሊቀ ካህን ነው። ኢየሱስ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ የተፈጸመበት ንጉሥ እና የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ኢየሱስ ከእኛ አስቀድሞ ወደ ሰማይ የገባ ቀዳሚ እና መሪያችን ነው። ወደ እግዚአብሔር ፊት የምንገባበትን መንገድ ከፍቶልናል (ዕብ. 10፥19–22 ይመለከቷል)።

---

12 ሰፋ ላለ ማብራሪያ ከአስተምህሮ ዳሰሳው ደኅንነታችንን ማጣት እንችላለንን? የሚለውን ይመለከቷል።

13 ቋሚ የአይሁድ ቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም ከመሠራቱ በፊት፣ አይሁዳውያን እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ድንኳን ውስጥ ነበር፤ ድንኳኑንም በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ ይዘውት ይሄዳሉ። በድንኳኑም ሆነ ኋላ በተሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ ቅድስተ ቅዱሳን የሚባል ክፍል ነበረበት (ዕብ. 9፥3)። በዚህ ቁጥር ጸሐፊው የሚናገረው ስለዚህ ክፍል ነው።

ምዕራፍ 7

ሊቀ ካህኑ መልከ ጼዴቅ (7፥1–10)

1–2 ከዚህ ከዕብራውያን መልእክት ውጪ የመልከ ጼዴቅ ስም የተጠቀሰው በዘፍ. 14፥18–20 እና በመዝ. 110፥4 ብቻ ነው። እዚህ ላይ ስለ መልከ ጼዴቅ የሚያደርገውን ገለጻ የመሠረተው በዘፍጥረት ባለው ምንባብ ነው። (ዕብ. 5፥6 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

3 ስለ መልከ ጼዴቅ አባትም ሆነ እናት ወይም ልደትና ሞት በመጽሐፍ ቅዱስ ምንም የተገለጸ ነገር የለም። እንደ ዕብራውያኑ መልእክት ጸሐፊ ከሆነ መልከ ጼዴቅ አልተወለደም፤ አልሞተም። *ይህ መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌ በመሆን ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።* ኢየሱስ ጅማሬና ፍጻሜ እንደሌለው ሁሉ መልከ ጼዴቅም ጅማሬና ፍጻሜ የለውም።

4 መልከ ጼዴቅ ከአብርሃም ይበልጣል፤ ያ ባይሆን ኖሮ፥ አብርሃም ከነገሥታቱ ጋር ተዋግቶ ካገኘው ምርኮ አንድ ዐስረኛውን ባልሰጠውም ነበር (ቁ. 1–2)።

5 *ሌዊ* የአብርሃም የልጅ ልጅ ከሆነ፥ ከያዕቆብ ልጆች አንዱ ነው። የመጀመሪያውን ሊቀ ካህን አሮንን ጨምሮ፥ የአይሁድ ሊቀ ካህናት በሙሉ የሌዊ ዘሮች ናቸው። በአይሁድ ሕግ መሠረት ሌሎች አይሁዳውያን ሁሉ ካላቸው ሃብት ወይም ምርት አንድ ዐስረኛውን የሌዊ ዘሮች ለሆኑት ካህናት ይሰጣሉ። ካህናቱ የሚኖሩት በዚህ መልክ ነበር። ካህናቱና ሌሎች አይሁዳውያን በሙሉ ደግሞ የአብርሃም ዘሮች ናቸው። ስለዚህም *ወንድማማች* ናቸው ማለት ነው።

6–7 *የልዑል እግዚአብሔር ካህን መልከ ጼዴቅ* ግን (ቁ. 1) የሌዊም ሆነ የአብርሃም ዘር አይደለም። ይሁን እንጂ፥ የአይሁዳውያን ሁሉ አባት የሆነው አብርሃም ካገኘው ሀብት ሁሉ፥ አንድ ዐስረኛውን ለመልከ ጼዴቅ ሰጥቶታል። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ አብርሃም ከመልከ ጼዴቅ በረከትን ተቀብሎአል። ከዚህም መልከ ጼዴቅ ከአብርሃም እንደሚበልጥ እንመለከታለን። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ መልከ ጼዴቅ የአብርሃምና የሌዊ ዘሮች ከሆኑት የአይሁዳውያን ካህናት ሁሉ ይበልጣል ማለት ነው።

8 ከዚህም በላይ የአይሁድ ካህናት እንደ ማንኛችንም ሰው ስለ ነበሩ፥ ሁሉም ሞተዋል። *ሕያው ሆኖ እንደሚኖር የተመሰከረለት* መልከ ጼዴቅ ግን አልሞተም።

9–10 ሌዊ እና ከሌሎች አይሁዳውያን በሙሉ አንድ ዐስረኛውን የሚሰበስቡ የእርሱ ዝርያዎች የሆኑት ካህናት፥ በአብርሃም አማካይነት የገቢያቸውን አንድ ዐስረኛ ለመልከ ጼዴቅ ሰጥተዋል ማለት ነው። ምክንያቱም አብርሃም መልከ ጼዴቅን በተገናኘው ጊዜ ሌዊ *በአባቱ ወገብ ነበር። ይህን ሁሉ በመዘርዘር የመልእክቱ ጸሐፊ መልከ ጼዴቅ ከሌዊ ከተወለዱት* አይሁዳውያን ካህናት ሁሉ የሚበልጥ መሆኑን ያመለክታል።

ኢየሱስ የመልከ ጼዴቅ ምሳሌ (7፥11–28)

11 እዚሆ ላይ በጥቂቱም ቢሆን የአይሁዳውያንን የጥንት *ታሪክ* መቃኘቱ አስፈላጊ ነው። አብርሃም የይስሐቅ አባት ነው፤ ይስሐቅ ደግሞ የያዕቆብ አባት ነው። ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ልጆች ሲኖሩት፥ እነርሱም የዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አባቶች ሆነዋል። ሌዊ ከዐስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ሶስተኛው ነው። ከሌዊ አራት መቶ ዓመት በኋላ፥ ሙሴ የአይሁዳውያን መሪ እንዲሆን በእግዚአብሔር ተሾመ። ከእግዚ አብሔርም የአይሁድን ሕግ ተቀበለ። በዚያን ወቅት ነበር የሌዊ ዘሮች የአይሁድ ሕዝብ ካህናት እንዲሆኑ እግዚአብሔር የተናገረው። ይህንንም የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የሌዊ ክህነት ሹመት ይለዋል። የአይሁድ ሕዝብ ሕግ የተመሠረተውም በዚህ በሌዊ ዘሮች ክህነት ሹመት ነው ማለት ነው። የሙሴ ታናሽ ወንድም የሆነው አሮን (እርሱም የሌዊ ዘር ነው) የመጀመሪያው ሊቀ ካህን እንዲሆን ተሾመ።

ይሁን እንጂ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፥ *የሌዊ ክህነት ሹመት* አይሁዳውያንን *ፍጹም* ሊያደርጋቸው እንዳልቻለ ይናገራል። ያም ማለት ሰዎችን ማጽደቅና ወደ ደኅንነት ማምጣት አልቻለም ማለት ነው። *የሌዊ ክህነት ፍጹም ቢሆን ኖሮ፥ የአሮን ክህነት ሹመት ሳይሆን፥ የመልከ ጼዴቅ የክህነት ሹመት ያለው ሌላ ካህን (ኢየሱስ ክርስቶስ) መምጣት ባላስፈለገም ነበር።*

12 ይህም ብቻ አይደለም፤ የሌዊ የክህነት ሹመት መለወጥ ካለበት የአይሁድ ሕግም መለወጥ ሊኖርበት ነው፤ ምክንያቱም ሕጉ የተመሠረተው በዚያ ክህነት ላይ በመሆኑ ነው።

13–14 *ይህ ሁሉ የተነገረለት ካህን* ማለትም ክርስቶስ፥ የተወለደው *ከሌላ ነገድ* ነው። ኢየሱስ የተወለደው ከይሁዳ ወገን ነው (ማቴ. 1፥2፤ ሉቃ. 3፥33)። ይሁዳ ከዐስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች አራተኛው ሲሆን፥ የሌዊ ታናሽ ነበር ማለት ነው። እግዚአብሔር ሕጉን ለሙሴ በሰጠበት ጊዜ ካህናትን *ከይሁዳ* ወገን እንዲሾሙ አልነገረውም። ከዚህም፥ የክርስቶስ ክህነት ሹመት ከብሉይ ኪዳን የሌዊ ክህነት ሹመት፥ በፍጹም የተለየ መሆኑን እንመለከታለን።

15–16 የክርስቶስ ክህነት ሹመት፥ *በሥጋዊ ሕግ መሠረት* ወይም እንደ ሌዋዊያን ክህነት በሥጋ በመወለድ ላይ የተመሠረተ አይደለም (ቁ. 16)። የክርስቶስ ክህነት የተመሠረተው *በማይሻር ሕይወት ኃይል* ላይ ነው። በአንድ ወቅት ሌዋውያን ካህናት በሕይወት ኖረዋል፤ በኋም ሞተዋል። ክርስቶስ ግን ለዘላለም በሕይወት ይኖራል። የሌዋውያን ክህነት የተመሰረተው በውጫዊ ሕግና ደንብ ላይ ነው፤ የክርስቶስ ክህነት የተመሠረተው ግን በውስጣዊው መንፈሳዊ ኃይል ላይ ነው።

17 የክርስቶስ ክህነት ዘላለማዊ መሆኑን ለማሳየት ጸሐፊው እንደገና ከመዝ. 110፥4 ይጠቅሳል።

18 የቀድሞው ትእዛዝ ደካማና የማይጠቅም ስለሆነ ተሽሮአል። የቀድሞው ትእዛዝ ሲል፥ የሌዋውያን ክህነትን አስመልክቶ ስለ መባ፥ ስለ መሥዋዕት፥ ስለ መንፃት ሥርዓት፥ እና ስለ ሃይማኖታዊ በዓላት የሚያካትተውን ልማዳዊ ሕግ ማለት ነው። ክርስቶስ ሲመጣ ግን እነዚህ ትእዛዛት ማለትም ሚዳቋ ሥርዓትን የሚያካትቱት የአይሁድ ሕጎች *ተሽረዋል* (ማቴ. 5፥17–18፤ ቆላ. 2፥13–14 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)።

19 ለምንድነው የአይሁድ ሕግ በተለይም ልማዳዊው *ሥርዓት ደካማና የማይጠቅም* የተባለው? (ቁ. 18) ምክንያቱም *በሙሴ ሕግ ምንም ነገር ፍጹም ሊሆን አልቻለም።* እርግጥ ነው ሕጉ የሰውን ውጫዊ አካል ማንፃት ችሎአል፤ ውስጣዊውን የሰው ልብ እና ኅሊና ግን በፍጹም ሊያነፃ አልቻለም። ሕጉ ሰዎችን ይኮንናል እንጂ፥ ሰዎችን ማጽደቅ አልቻለም (ሮሜ 8፥1–3 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

እዚህ ላይ *የተሻለ ተስፋ* የተባለው *ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት* ዘላለማዊና እውነተኛው ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጽድቅ የሌላቸው ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይችሉም። በእምነት አማካይነት ግን የክርስቶስን ጽድቅ እናገኛለን፤ ጽድቁን ካገኘን ደግሞ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን። ስለዚህም ከአሮጌው የአይሁድ ሕግ ወይም የሌዊ ክህነት ሹመት ይልቅ፥ ሰዎች ከክርስቶስ *የተሻለ ተስፋ* ያገኛሉ ማለት ነው።

20–21 ሊቀ ካህን እንዲሆን እግዚአብሔር ክርስቶስን የሾመው *በመሐላ* ነው። ይህንንም ለማረጋገጥ ጸሐፊው እንደገና ከመዝ. 110፥4 ይጠቅሳል።

22 *በዚህ መሐላ ምክንያት፥* ከሌዋውያን ክህነት ሹመት ይልቅ፥ የክርስቶስ ክህነት ሹመት ይበልጣል ማለት ነው። ስለዚህም፥ *ለተሻለው ኪዳን ዋስ* ነው (ዕብ. 8፥6 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

23–24 ከመጀመሪያው ሊቀ ካህን ከአሮን አንስቶ፥ ይህ መልእክት እስከ ተጻፈበት ጊዜ ድረስ፥ ሰማንያ ሶስት ሊቀ ካህናት ተሹመዋል። ሁሉም በተራቸው ሞተዋል። ኢየሱስ ግን በፍጹም አይሞትም፤ ስለዚህ ክህነቱ *የማይለወጥ* ነው።

25 ኢየሱስ እኛን *ለማማለድ ለዘላለም ህያው ሆኖ ይኖራል* (ሮሜ 8፥34 ይመለከቷል)። በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ኢየሱስ አማላጃችንና ጠበቃችን ነው። ፍጹም ሊቀ ካህን ነውና እግዚአብሔር ይሰማዋል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ኢየሱስ የኃጢአታችንን ዋጋ ከፍሎልናል (ዕብ. 2፥17) ከእንግዲህ እግዚአብሔር አይፈርድብንም። ከዚህም በተጨማሪ

ምሕረትንና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ ይሰጠናል (ዕብ. 4፥16)። የኢየሱስ ክህነት ፍጻሜ የሌለው በመሆኑ፣ ይህን ግድረጉን በፍጹም አያቋርጥም። ለዘላለም በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል፤ ወደ እግዚአብሔር ፊት ሊያቀርበንም ምንጊዜም ዝግጁ ነው። ከእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የተነሳ ኢየሱስ *በፍጹም* ሊያድነን ይችላል። ስለ እንደዚህ ዓይነቱ አዳኝ እና ሊቀ ካህን እግዚአብሔርን ማመስገናችንን በፍጹም አናቋርጥ!

26 ጸሐፊው ስለዚህ አስደናቂ ሊቀ ካህን ስለ ኢየሱስ የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን መዘርዘሩን ይቀጥላል። ኢየሱስ *ቅዱስ፣ ያለነቀፋ የሆነ፣ ንጹሕ፣ ከኃጢአተኞች የተለየ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ያለ ነው*። ኢየሱስ ራሱ ፍጹም ነውና ክህነቱም ፍጹም ነው (ዕብ. 1፥3፤ 4፥15–16 ይመለከቷል)።

27 የአይሁድ ካህናት ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ ኢየሱስ ለራሱ ኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም (ዘሌ. 4፥3፤ 16፥6፤ ዕብ. 5፥1፤ 3)። በተጨማሪም የአይሁድ ካህናት ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ (ዘሌ. 16፥34) ደግሞ ደጋግሞ ለኃጢአታችን መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈ ልገውም። ኢየሱስ ያቀረበው መሥዋዕት ማለትም ሕይወቱን መሠዋቱ በእግዚአብሔር ፊት ብቁ ሆኖ ተገኝቶአል። ኢየሱስ ራሱን የኃጢአት መሥዋዕት አደረገ። ያቀረበው መሥዋዕት ፍጹም ስለነበር መደጋገም አያስፈልገውም።

ምንኛ የከበረ መሥዋዕት ነው! ለሰዎች ሁሉ ደኅንነትን ለመስጠት ኢየሱስ ሕይወቱን መሥዋዕት አደረገ። ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው *ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት* ነው (ማር. 10፥45)። በመጨረሻም ከመሞቱ በፊት በነበረው ምሽት «ይህ ስለብዙዎች የሚፈስስ የቃል ኪዳን ደሜ ነው» አለ (ማር. 14፥24)። ለዚህ ነው በኢየሱስ ሞት፣ ባፈሰሰውም ክቡር ደም ድነናል ብለን የምንመሰክረው።

28 እዚህ ላይ ጸሐፊው ስለ ኢየሱስ አንድ የመጨረሻ ነገር ያክላል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይላል። በሕጉ መሠረት የአይሁድ ካህናት በሙሉ ሰው መሆን ነበረባቸው፤ ሰው ደግሞ ደካማና ኃጢአተኛ ነው። በእግዚአብሔር *መሐላ* ሊቀ ካህን እንዲሆን የተሾመው የእግዚአብሔር ልጅ ግን *ለዘላለም ፍጹም ሆኖአል*።

ምዕራፍ 8

የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህን (8፥1–13)

1–2 የአሁድ ካህናት ያገለግሉ የነበረው በሰው እጅ በተሠራ መቅደስ ነው። ኢየሱስ የሚያገለግለው ግን በሰው እጅ ሳይሆን *በእግዚአብሔር በተተከለችው* በሰማይ በእግዚ አብሔር ቀኝ ባለችው መቅደስ ነው። የአይሁድ ክህነት በዚህ ዓለም ነበር፤ የኢየሱስ ክህነት ግን በሰማይ ነው። መንፈሳዊ ክህነት ነው።

3 የዚህ ዓለም ካህናት የሚሾሙት *መባንና መሥዋዕትን ለማቅረብ* ነው። ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ የአይሁድ ካህናት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርባሉ። ኢየሱስም አንድ ነገር ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። ስለዚህም የገዛ አካሉን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ።

4 በአይሁድ ሕግ መሠረት ወይም ደግሞ በዘር ሐረጉ ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ የአይሁድ ሊቀ ካህን መሆን አይችልም ነበር። የአይሁድ ካህናት በሙሉ የሌዊ ዘሮች ሲሆኑ፣ እርሱ ግን የሌዊ ዘር አልነበረም። የኢየሱስ ክህነት ከዚህ ዓለም ሳይሆን ከሰማይ ነው።

5 የአይሁድ ካህን ያገለገሉት የነበረው በሰው እጅ በተሠራ *መቅደስ*[14] ነበር። ያ መቅደስ ግን በሰማይ ያለው መቅደስ ምሳሌና ጥላ እንጂ እውነተኛው መቅደስ አልነበረም።

[14] የመጀመሪያው የአይሁድ መቅደስ ድንኳን ነበር፤ አይሁዳውያን ወደሚሄዱበት ሁሉ ይህን ድንኳን ይዘው ይሄዱ ነበር። ወደ ተስፋይቱ አገር ወደ እስራኤል ከገቡ በኋላ ነበር ቋሚ ቤተ መቅደስ የሠሩት፤ ይህም በኢየሩሳሌም የነበረው ታላቁ ቤተ መቅደስ ነው።

የጥንት አይሁዳውያን የመጀመሪያውን መቅደስ በሲና በረሃ በሚሠሩበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር *«በተራራው ላይ እንደታገለጠልህ ዓይነት ሁሉን ነገር በጥንቃቄ አድርግ»* በማለት መሪያቸው ሙሴን አዝዞት ነበር። ያም ማለት በሰማያዊው መቅደስ ምሳሌ ዓይነት ማለት ነው። ጸሐፊው ይህን የጠቀሰው ከዘጸ. 25፥40 ነው።

የዚህ ዓለም ሰዎች የሚያዩዋቸውና የሚዳስሷቸው ነገሮች ብቻ እውነተኛ እንደሆኑ ያስባሉ። ሰማያዊ ነገሮች እንደሌሉና የሰዎች ምናብ ፈጠራ ብቻ ይመስላቸዋል። መንፈሳዊ ሰው ግን ይህ ዓለም እንደሚያልፍ ያውቃል። ሰማያዊና መንፈሳዊ ነገሮች ብቻ እውነተኛና ዘላለማዊ መሆናቸውን ይረዳል። ጸሐፊው በአይሁዳውያን የተሠራው መቅደስ በኢየሱስ የተሠራው ሰማያዊ መቅደስ *ምሳሌና ጥላ* ነው በማለት የሚናገረውም ለዚህ ነው።

6 በምዕራፍ 7 እና በዚህ ምእራፍ የመጀመሪያዎቹ አምስት ቁጥሮች፣ ጸሐፊው የኢየሱስ ክህነት ከአይሁድ ክህነት እንደሚበልጥ ገልጾአል። አሁን ደግሞ ከላይ ባቀረባቸው አሳቦች ላይ ሌላ አዲስ አሳብ ያክልበታል። ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ማለትም *በበለጠና በተሻለ ተስፋ ላይ የተመሠረተው* ኪዳን መካከለኛ መሆኑን ያመለክታል። ከአይሁዳውያን ካህናት አገልግሎት ይልቅ፣ የኢየሱስ ክህነት አገልግሎት እንደሚበልጥ ሁሉ፣ አዲሱ ኪዳንም ከአሮጌው ኪዳን ይበልጣል።

ለመሆኑ አሮጌው ኪዳን ምንድነው? ኪዳን ማለት በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው። በአሮጌው ኪዳን መሠረት እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘሮች (አይሁዳውያን)፣ የእርሱ የተለየ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸውና እንደሚባርካቸው ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር (ዘፍ. 12፥1–3)። ይህ በእግዚአብሔር በኩል ያለው ውል ነው። በአይሁዳውያን በኩል ያለው ውል ደግሞ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ መታዘዝ ነበር (ዘጸ. 19፥5፤ ኤር. 7፥23)። አይሁዳውያን ካልታዘዙ ቃል ኪዳኑ ይፈርሳል።

አይሁዳውያን ለእግዚአብሔር አልታዘዙምና አሮጌው ኪዳን ተገቢውን ውጤት አላስገኘም (ኤር. 7፥24–26)። አይሁዳውያን ለገቡት ውል ታማኝ አልሆኑም፤ ስለዚህም እግዚአብሔር *እኔም ቸላ አልኩአቸው* አለ (ቁ. 9)። ለአሮጌው ኪዳን ለመታዘዝ ብርታቱም ሆነ ፈቃደኛነቱ አልነበራቸውምና ከኃጢአት ባርነት ነፃ አልሆኑም። ምንም እንኳ ካህናቱ ለሕዝቡ ኃጢአት በየዓመቱ መሥዋዕት ቢያቀርቡም፣ የሕዝቡ ልብ ግን አልነፃም፤ አልተቀደሰም። ስለዚህም ቅድስናና ጽድቅ የጎደላቸው በመሆናቸው ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይችሉም።

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረገው አዲስ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስ ኪዳን ነው። ጸሐፊው ኢየሱስን የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ ይለዋል። ኢየሱስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ይቆማል። እግዚአብሔር በአዲሱ ኪዳን የሰጠውን ተስፋ የምንቀበለውም በኢየሱስ አማካይነት ነው። እግዚአብሔር «በኢየሱስ ብታምኑ ደኅንነትንና የዘላለም ሕይወትን እሰጣችኋለሁ» ይለናል (ዮሐ. 3፥16 ይመለከቷል)። ደኅንነትን፣ የዘላለም ሕይወትን፣ መንፈስ ቅዱስን፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የመሆንን መብት እንደሚሰጠን እግዚአብሔር ቃል ገብቶአል፤ ይህ የእርሱ ድርሻ ነው። የእኛ ድርሻ ግን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው።

እዚህ ላይ ጸሐፊው አዲሱ ኪዳን *ከአሮጌው ኪዳን የበለጠና በተሻለ ተስፋ* ማለትም፤ በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ ላይ *የተመሠረተ* መሆኑን ይናገራል። ከነቢዩ ኤርምያስ መጽሐፍ በመጥቀስም ከተሰጡት የተሻሉ ተስፋዎች ሶስቱን ያቀርባል። የመጀመሪያው ተስፋ «እኔ ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ፤ በአእምሮአቸውም እጽፈዋለሁ» ይላል (ቁ. 10)። ሁለተኛው ተስፋ «ከትንሹ ጀምሮ እስከ ትልቁ ድረስ ሁሉም ያውቀኛል» ይላል (ቁ. 11)። ሦስተኛው ተስፋ «በደላቸውን ይቅር እላቸዋለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስታውስባቸውም» ይላል (ቁ. 12)። የእነዚህን ሶስት ተስፋዎች አሳብ በአጭሩ ስናጠቃልለው፣ በኢየሱስ የሚያምነውን ሁሉ እግዚአብሔር *አዲስ ፍጥረት* ያደርገዋል ማለት ነው (2ቆሮ. 5፥17)። በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ እንዲኖር መንፈስ ቅዱሱን ይልካል። እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ «*አዲስ ልብና አዲስ*

ለእምሮ እሰጣቸዋለሁ፤ አልሸኛ የሆነውን የድንጋይ ልብ ከእነርሱ አውጥቼ የሚታዘዝ ልብ እሰጣቸዋለሁ። በዚያን ጊዜ ሕጌን ይፈጽማሉ፤ ትእዛዛቴንም ሁሉ ያከብራሉ፤ እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም አምላካቸው እሆናለሁ» (ሕዝ. 11፥19–20)።

ስለዚህም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረገው «አዲስ ኪዳን» እንደሚከተለው ነው ማለት ነው። በመንግሥተ ሰማይ የዘላለምን ሕይወት ተስፋ እግዚአብሔር ሰጥቶናል። ከዚህም ጋር አብሮ ኃጢአትን የምናሸንፍበትን፣ እርሱን የምናውቅበትን፣ እርሱን የምንወድበትና የምንታዘዝበትን አዲስ መንፈስ ይሰጠናል። ኪዳኑ እንዲፈጸም ከተፈለገ አንድ ነገር ብቻ አስፈላጊ ነው፤ ይኸውም በክርስቶስ ማመን ነው። በእርግጥም አዲሱ ኪዳን ከአሮጌው ኪዳን እጅግ ይበልጣል!

7 የመጀመሪያው ኪዳን (አሮጌው ኪዳን) *ነቀፋ ባይኖረው ኖሮ* አዲሱ ኪዳን ባላስፈለገም ነበር።

8 የመጀመሪያው ኪዳን ግን «ነቀፋ» ተገኘበት፤[15] አይሁዳውያን ታማኝ ሆነው አልተገኙም፤ ኪዳኑን ለመጠበቅ የግላቸውን ድርሻ አልተወጡም።

ከ8–12 ባሉት ቁጥሮች፣ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ከትንቢተ ኤርምያስ 31፥31–34 የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል ይጠቅሳል። *«እነሆ ከእስራኤል ሕዝብና ከይሁዳ ሕዝብ ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ጊዜ ይመጣል»* ይላል ጌታ። በነቢዩ ኤርምያስ ዘመን የእስራኤል መንግሥት ለሁለት መንግሥታት ተከፋፍሎ ነበር። ሰሜናዊው መንግሥት የእስራኤል ሲሆን፣ ደቡባዊው መንግሥት ደግሞ የይሁዳ መንግሥት ሆነ። ስለዚህም ከዚህ ቁጥር አዲሱ ኪዳን «ለሁለቱም መንግሥታት» ማለትም በእምነት አማካይነት እውነተኛ የአብርሃም ልጆች ለሆኑት ሁሉ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ ናቸው (ገላ. 3፥7–9 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

9–10 አዲሱ ኪዳን እንደ አሮጌው ኪዳን አይደለም። አሮጌው ኪዳን የተጻፈው በሁለት የድንጋይ ፅላቶች ላይ ነበር (ዘፀ. 31፥18)። አዲሱ ኪዳን ግን በሰዎች ልብ ነው የሚጻፈው። ሰዎች ለአሮጌው ኪዳን መታዘዝና ታማኝ መሆን አልቻሉም። በአዲሱ ኪዳን ግን ሰዎች ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ኃይልና ፍላጎት የሚሰጣቸውን መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ። ስለዚህም ከዘማሪው ከዳዊት ጋር *«አምላኬ ሆይ! ፈቃድህን ለማድረግ በጣም እወዳለሁ፤ ሕግህንም በልቤ አኖራለሁ»* (መዝ. 40፥8) ማለት እንችላለን።

11 አይሁዳውያን በብሉይ ኪዳን የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል አንዳቸው ለሌላው ያስተምሩ ነበር። በአዲሱ ኪዳን ግን በውስጡ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እያንዳንዱ አማኝ በግሉ እግዚአብሔርን ያውቀዋል። ልጆች አባቶቻቸውን እንደሚያውቁ ሁሉ፣ እኛ አማኞችም የሰማዩ አባታችንን እናውቀዋለን። ኢየሱስ ራሱ ይህን በመሰለ ሁኔታ እግዚአብሔርን ማወቅ የዘላለምን ሕይወት ማግኘት እንደሆነ ተናግሮአል (ዮሐ. 17፥3)።

12 በአዲሱ ኪዳን ኃጢአታችን በሙሉ ይቅር ተብሎአል፤ ብፍጹም ተደምስሶአል። ክርስቶስ አካሉን፤ ፍጹም መሥዋዕት አድርጎ ስላቀረበ ነጽተናል። ስለዚህም ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ እንችላለን። ሰው ቅዱስ የሚሆነውና በእግዚአብሔርም ፊት ተቀባይነትን የሚያገኘው በክርስቶስ ብቻ ነው። ይህን በሚመስል ሁኔታ ክርስቶስ የአዲሱ ኪዳን *መካከለኛ* ሆኖአል (ዕብ. 9፥15)።

13 ስለዚህም ከ8–12 ከተፃፉት ቁጥሮች ይህ አዲሱ ኪዳን ምን እንደሚመስል መመልከት እንችላለን። በሰዎች ልብ ላይ የተጻፈ የመንፈስ ቅዱስ ኪዳን ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ *ፊደልን ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ያለበትን አዲስ ኪዳንን እንድናገለግል* ተጠርተናል (2ቆሮ. 3፥6) በማለት ስለ ራሱና ስለ ሌሎች ሐዋርያት የሚናገረው። እንግዲህ አዲስ ኪዳን ከመጣ የድሮው ኪዳን *አሮጌ* ሆኖአል፤ የሚጠፋበት ጊዜ ተቃርቦአል። አሮጌው ኪዳን እንደሻማ ብርሃን ነው፤ ፀሐይ ወጥቶአልና ከእንግዲህ አስፈላጊ አይደለም።

አሮጌው ኪዳን የጸናው ደም በማፍሰስ ነበር (ዘጸ. 24፥8)። በተመሳሳይ መንገድም አዲሱ ኪዳን የጸናው በኢየሱስ ደም መፍሰስ ነው። ለዚህ ነበር በመጨረሻው ራት ጊዜ ኢየሱስ ጽዋውን አንስቶ፣ *«ይህ ስለብዙዎች የሚፈስስ የቃል ኪዳን ደሜ ነው . . . ይህ ስለእናንተ በሚፈስሰው ደሜ የሚፈጸም አዲስ ኪዳን ነው።»* በማለት ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው (ማር. 14፥24፤ ሉቃ. 22፥20)።

ምዕራፍ 9

አምልኮ በምድራዊው ድንኳን (9፥1–10)

1–3 እግዚአብሔር አይሁዳውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ ካወጣ በኋላ፣ ከእነርሱ ጋር የመጀመሪያውን ኪዳን አደረገ (ዘጸ. 24፥፡7–8)። ከዚያም በኋላ *መቅደስ ወይም ድንኳን* እንዲሠሩ አዘዘ (ዘጸ. 25፥8–9)። ድንኳኑ ትልቅ ሲሆን፣ በመጋረጃ የተከፈሉ ሁለት ክፍሎች ነበሩት። አንደኛው ክፍል *ቅድስት* ሲባል ሁለተኛው ክፍል ደግሞ *ቅድስተ ቅዱሳን* ይባል ነበር (ዘጸ. 26፥33)። በቅድስት ውስጥ መቅረዙ (ዘጸ. 25፥31) ጠረጴዛው (ዘጸ. 25፥23) እና የመሥዋዕቱ ኅብስት (ዘጸ. 25፥30) ነበሩ።

4–5 በእነዚህ ቁጥሮች ጸሐፊው ስለ ሁለተኛው ክፍል ማለትም ስለ *ቅድስተ ቅዱሳን* ይገልጻል። በዚህ ክፍል ውስጥ የወርቅ ማእጠንት (ዘጸ. 30፥1) እና የቃል ኪዳን ታቦት ነበሩበት (ዘጸ. 25፥10)። በታቦቱ ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብ (ዘጸ. 16፥31–33)፣ የለመለመችው የአሮን በትር (ዘኁ. 17፥1–5፤ 8፤ 10–11) እና እግዚአብሔር ትእዛዙን የጻፈባቸው ሁለት ጽላቶች ነበሩ (ዘጸ. 24፥12፤ 25፥16፤ 31፥18)። ከታቦቱ በላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ የሆኑት የክብር ኪሩቤል ነበሩ (ዘጸ. 25፥18)። የስርየት መክደኛ የተባለው ታቦቱን የሚሸፍን ሲሆን፣ ሊቀ ካህኑ ለሕዝቡ ኃጢአት ስርየት የሚያቀርበውን የእንስሳት ደም የሚረጨውም እዚሁ መክደኛ ላይ ነው (ዘጸ. 25፥17፤ 22)።

6–7 እግዚአብሄር በዓመት አንድ ጊዜ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ይገለጥና ከሊቀ ካህኑ ጋር ይገናኛል። ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርበው ሊቀ ካህኑ ብቻ ሲሆን፣ ይህንንም የሚያደርገው በዓመት አንድ ቀን ማለትም በኃጢአት ስርየት ቀን ብቻ ነበር (ዘሌ. 16፥2)። በዚያ ቀን ሊቀ ካህኑ *መጀመሪያ* ስለራሱ ኃጢአት መስዋዕት ያቀርባል (ዘሌ. 16፥6)። ከዚያ በኋላ ደግሞ ስለ ሕዝቡ ሁሉ ኃጢአት ሁለተኛ *መሥዋዕት* ያቀርባል (ዘሌ. 16፥9)። ስለዚህም ሊቀ ካህኑ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በሚገባበት ጊዜ ሁሉ፣ ለመሥዋዕት የቀረቡትን እንስሳት ደም መያዝ ነበረበት (ዘሌ. 16፥14–15)። ሊቀ ካህኑ የሚያቀርባቸው *መሥዋዕቶች* ዘላቂነት ስላልነበራቸው፣ በየዓመቱ *መደጋገም* ነበረባቸው።

ሊቀ ካህኑ *መሥዋዕት* የሚያቀርበው *ሕዝቡ ባለማወቅ ስላደረገው ኃጢአት* ብቻ ነው (ቁ. 7) በብሉይ ኪዳን መሠረት ሆን ተብሎ ለተሠራ ኃጢአት ምንም መሥዋዕት ወይም ይቅርታ አይደረግም (ዕብ. 10፥26 እና ገለጻውን የመለከቷል)።

8 ከላይ እንደተጻፈው ከሊቀ ካህኑ በቀር፣ ወደ ቅዱስተ ቅዱሳን ማለትም ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚያስገባው መንገድ ለሌሎች አይሁዳውያን ዝግ እንደ ነበር መመልከት ይቻላል። እንግዲህ *የመጀመሪያይቱ ድንኳን እስካለች ድረስ* ማለትም አሮጌው ኪዳን *ሥራ* ላይ እስከዋለ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚያስገባው መንገድ እንደተዘጋ ነው ማለት ነው። ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመጣበት ጊዜ ግን የራሱን አካል *መሥዋዕት* አደረገ፤ የራሱንም ደም ይዞ ወደ እግዚአብሔር ፊት ገባ (ቁ. 12)። ይህን በማድረጉም ለአማኞች ሁሉ የኃጢአት ቤዛ ሆነ፤ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚገቡበትንም መንገድ ከፈተላቸው።

---

[15] እንደ እውነቱ ከሆነ «ስሕተት» የተገኘበት ራሱ ኪዳኑ አይደለም፤ ስሕተት የተገኘው በአይሁዳውያኑ ነው። ቁ. 8 እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ *ነቀፋ አገኘባቸው* ይላል።

9–10 በአሮጌው ኪዳን የሚቀርበው *መባና መሥዋዕት የአቅራቢውን ሰው ኅሊና ፍጹም* ሊያደርጉት አይችሉም። ያለ ንጹህ ኅሊና ደግሞ ማንም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይችልም። ኅሊናችን ሊነጻ የሚችለው፥ በክርስቶስ *መሥዋዕትነትና* በውስጣችን በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነው።

ስለዚህም እነዚህ የአሮጌው ኪዳን ዓለማዊ *ሥርዓቶች ሥራ* ላይ የሚውሉት *የመታደስ ጊዜ* (ቁ. 10) ማለትም በክርስቶስ አማካይነት የሚደረገው አዲሱ ኪዳን እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ነበር ማለት ነው። አዲሱ ኪዳን ሲመጣ፥ አሮጌው ኪዳን አስፈላጊ አይሆንም (ዕብ. 8፥13 ይመለከቷል)።

የክርስቶስ ደም (9፥11–22)

11 ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው *አሁን ለሚሆኑት* መልካም ነገሮች ሊቀ ካህን ማለትም፤ የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህን ለመሆን ነበር (ዕብ. 8፥1፤ 6 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

እግዚአብሔር የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም (የሐዋ. 7፥48፤ 17፥24)። በሰማይ ባለው ትልቅና ፍጹም በሆነው ማደሪያ ውስጥ ነው የሚኖረው። ኢየሱስ በሰማይ ያለው ማደሪያ ሊቀ ካህን ነው። ኢየሱስ ወደዚህ ምድር በመጣበት ጊዜ የሰው እጅ *ሥራ* የሆነውን የብሉይ ኪዳን ድንኳን አፈረሰው፤ በምትኩም ሰዎች *በመንፈስና በእውነት* እግዚአብሔርን የሚያመ ልኩበት እውነተኛ ሰማያዊ መቅደስ አዘጋጀ ማለትም ይቻላል (ማር. 14፥58፤ ዮሐ. 4፥21፤ 23–24 ይመለከቷል)።

12 ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመግባት ለኃጢአት ስርየት መሥዋዕት የቀረቡትን እንስሳት ደም መርጨት አስፈላጊ ነበር። ስለዚህም የአይሁድ ሊቀ ካህን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው *የፍየሎችንና የኮርማዎችን ደም* ይዞ ነበር (ቁ. 7)። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ፊት የገባው ግን የገዛ ራሱን ደም ይዞ ነው። የኢየሱስ መሥዋዕት ፍጹም ነው፤ ስለዚህም መደጋገም አይኖርበትም። በእርሱ መሥዋዕት አማካይነት እኛ አማኞች *የዘላለም ደኅንነትን* አግኝተናል።

13 የእንስሳቱ ደም እና *ዐመድ* ሰዎችን ከውጫዊ ርኩሰት ብቻ ነበር የሚያነፃቸው፤ ወይም ደግሞ እንዲሁ ለሥርዓቱ ብቻ ነበር የሚያነፃቸው። እዚህ ላይ የተጠቀሰው የተቃጠለች ጊደር *ዐመድ* የሚለው በዘኁ. 19፥9 ያለውን ለመጥቀስ ነው። አይሁዶች ለውጫዊ ንጽሕና ልዩ ትኩረት ይሰጣሉ። ኢየሱስ ግን ውስጣዊ ንጽሕና ይበልጥ አስፈላጊ መሆኑን ነው የተናገረው (ማር. 7፥20–23)። የእንስሳት ደም እና *ዐመድ* የሰውን ውስጣዊ ሕይወት ማንጻት አይችሉም።

14 ይሁን እንጂ፥ የእንስሳቱ ደም ማድረግ ያልቻለውን የክርስቶስ ደም ማድረግ ችሎአል። ኅሊናችንን *ከምተ ስራ* ማለትም ከኃጢአት አንጽቶታል። ክርስቶስ ያነጻንም *ህያው እግዚአብሔርን እንድናገለግል* ነው። እግዚአብሔር ያዘዘው በአሮጌው ኪዳን ለመሥዋዕት የሚቀርበው እንስሳ *ነውር የሌለበት* እንዲሆን ነበር። በአዲሱ ኪዳን ግን ክርስቶስ ምንም ኃጢአት ወይም *ነውር የሌለበት* መሥዋዕት ሆኖአል።

15 በክርስቶስ ሞት አማኞች ከድሮው ኃጢአታቸው ነጻ ሆነዋል። ክርስቶስ ሞቶልናልና እኛ አማኞች *ዘላለማዊ ርስት እንድንወርስ* የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ሆኖአል፤ ያም «ዘላለማዊ ርስት» የኃጢአት ይቅርታ፥ ደኅንነት፥ የዘላለም ሕይወት ነው (ዕብ. 7፥27፤ 8፥6 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)። አሮጌው ኪዳን ሰዎችን ከኃጢአት ነፃ ማድረግ አልቻለም። አሁን ግን በክርስቶስ ሞት ነፃ ሆነናል (ሮሜ 8፥1–2 ይመለከቷል)።

16–17 *ኑዛዜ*[16] እንዲጸናና ዋጋ እንዲኖረው ተናዛዡ መሞት አለበት። በተመሳሳይ መንገድም አዲሱ «ኑዛዜ» ወይም ኪዳን ዋጋ የሚኖረውም ክርስቶስ ሲሞት ብቻ ነው።

18–20 አሮጌው «ኑዛዜ» ወይም ኪዳን ዋጋ ሊኖረው የቻለው በሞት ማለትም በእንስሳት ሞት ነበር (ዘጸ. 24፥8)። በቁ. 19 የተጠቀሰው *ሂሶጵና*[17] *ቀይ የበግ ጠጉር* በዘኁ. 19፥6 ተጠቅሶአል።

21–22 ደም በማፍሰስ ብቻ ነበር የአይሁድ ሊቀ ካህን የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት የሚያስተሰረየው። ስለዚህም በድንኳኑ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ ደም እንዲረጭባቸው እግዚአብሔር አዘዘ (ዘሌ. 16፥14–16፤ 18–19 ይመለከቷል)። በተመሳሳይ መንገድ በአዲስ ኪዳንም ቢሆን ሰዎች የኃጢአት ይቅርታን የሚያገኙት ደም ሲፈስ ብቻ ነው። ክርስቶስ የገዛ ደሙን ያፈሰሰውና ከኃጢአት ሊያነጻን የሞተውም በዚህ ምክንያት ነበር።

ከሁሉ የሚበልጥ የክርስቶስ መሥዋዕት (9፥23–28)

23 *የሰማያዊ ነገሮች ምሳሌ የሆኑት* ማለትም፤ ምድራዊው ድንኳን የሚነጹት በእንስሳት መሥዋዕት ነበር። ሰማያዊው ድንኳን ግን የነጻው ከዚህ በሚበልጥ መሥዋዕት ማለትም በራሱ በክርስቶስ ነው።

በአንድ መንገድ ስናየው ይህ ሰማያዊ ድንኳን እኛ አማኞች ነን (ኤፌ. 2፥22፤ 1ጴጥ. 2፥5 ይመለከቷል)። የእግዚአብሔር መኖሪያ እንደመሆናችን መጠን *በተሻለ መሥዋዕት* መንጻት ያስፈልገናል። በእርግጥም ፍጹም በሆነው የክርስቶስ መሥዋዕት ነጽተናል። ከኃጢአት ነፃ ወጥተናል፤ *በክቡር የክርስቶስ ደም* ተዋጅተናል (1ጴጥ. 18–19)።

24 እዚህ ላይ ጸሐፊው በዕብ. 8፥1–2 ያለውን አሳብ በድጋሚ ያቀርባል።

25–26 የክርስቶስ መሥዋዕት መደጋገም አያስፈልገውም። በሞቱ ክርስቶስ በማያዳግም ሁኔታ የኃጢአታችን መሥዋዕት ሆኖአል (ቁ. 26)።

27–28 አንድ ሰው አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚሞተው፤ ስለዚህም ክርስቶስ ደግሞ ደጋግሞ መሥዋዕት መሆን አይችልም። *የብዙዎችን ኃጢአት ለማስወገድ* አንዴ ያቀረበው መሥዋዕት ብቻ በቂ ነው (ዮሐ. 1፥29 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

ከሞት በኋላ *ፍርድ* ይከተላል፤ የክርስቶስ ሞት ግን እርሱን *የሚጠባበቁትን* ማለትም፤ አማኞችን በሚያድን የዘላለም ደኅንነት እንጂ፥ ፍርድን አያስከትልም። ኢየሱስ አንድ ቀን ይመጣል። በዚያው ቀን እርሱ ተስፋ የገባልንን የተሟላ ርስት በሰማይ እንቀበላለን። ስለዚህም በትዕግሥትና በእምነት እንጽና እንጂ፥ በፍጹም ተስፋ አንቁረጥ።

ምዕራፍ 10

የማያዳግም የክርስቶስ መሥዋዕት (10፥1–18)

1 *የአይሁድ ሕግ ወደ ፊት ለሚመጣው መልካም ነገር ምሳሌ* ብቻ ነበር (ዕብ. 8፥5 ይመለከቷል)። *መልካም ነገር* የተባለው የክርስቶስ መሥዋዕት፥ ሊቀ ካህንነቱ፥ ያስገኘልን ደኅንነትና የዘላለም ሕይወት ናቸው።

የአዲስ ኪዳን «ምሳሌ» የሆነው የአይሁድ ሕግ እና በየዓመቱ ዘወትር *የሚሰውት መሥዋዕቶች፤* የሚያቀርቡትን ሰዎች ማለትም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሰዎች *ፍጹሞች ሊያደርጋቸው* ወይም ሊያነጻቸው ከቶ አይችልም (ዕብ. 9፥9)።

2 ሕጉና መሥዋዕቶቹ፥ የሚያቀርቡትን ሰዎች ሊያነጻቸው ላለመቻላቸው ማስረጃው ይህ ነው፥ መሥዋዕቱን ካቀረቡ በኋላ ኅሊናቸው ይከሳቸው ነበር። ኅሊናቸው ሊነጻ አልቻለም። ስለዚህም እነዚህ መሥዋዕቶች መደገምና መደጋገም ነበረባቸው።

ንፁህ ያልሆነና በደለኛነት የሚሰማው ህሊና ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርብ እንቅፋት ይሆንበታል። ዘማሪው፥ *ኀጢአቴን ሳልናዘዝ ሰውሬ ቢሆን ኖሮ*

---

16 ግሪኩ ኑዛዜ ለሚለውና ኪዳን ለሚለው አንድ ቃል ነው የሚጠቀመው።

17 ሂሶጵ ደምን ወይም ውኃን ለመርጨት የሚጠቀሙበት ተክል ነው።

እግዚአብሔር ፀሎቴን ባልሰማም ነበር» ብሎአል (መዝ. 66፥18)።

ክርስቶስ ባቀረበው መስዋእት ግን በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ በማያዳግም ሁኔታ ህሊናቸው ነፅቶአል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ *«ሰውነቱን የታጠበ ሁለመናው ንፁህ በመሆኑ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም እናንተም ንፁሃን ናችሁ»* አላቸው (ዮሐ. 13፥10)። ጳውሎስ ደግሞ ለቆሮንቶስ ሰዎች *«በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችንም መንፈስ ከኃጢአት ታጥባችኋል»* አላቸው (1ቆሮ. 6፥11) ይህ መንጻት ወይም መታጠብ የተፈጸመው የክርስትና ሕይወታችንን በጀመርንበት ጊዜ ነው። ለዚህ መንጻት ምልክቱ ደግሞ ጥምቀታችን ነው።

3–4 የአሮጌው ኪዳን መሥዋዕት *ኃጢአትን ለማስወገድ አይችልም* (ቁ. 4)። እነዚህ መሥዋዕቶች የአይሁድን ሕዝብ የሚያስገነዝቡአቸው ኃጢአተኞች መሆናቸውን ብቻ ነበር። በአዲሱ ኪዳን ግን እግዚአብሄር «ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስታውስባቸውም» ብሎአል (ኤር. 31፥34፤ ዕብ. 8፥12)። ኃጢአታችን ከተወገደልን ደግሞ ኅሊናችን በእርግጥ ነጽቶአል ማለት ነው።

ንጉሥ ዳዊት መሥዋዕትና መባ ኅሊናን ማንጻት እንደማይችሉ ተረድቶአል። ስለዚህም *«አምላኬ ሆይ ! . . . ይቅር በለኝ . . . ኃጢአቴንም ደምስስልኝ በደሌንም ሁሉ አጥበህ አስወግድልኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ . . . አምላኬ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ . . . አንተ መሥዋዕት እንዲቀርብልህ አትፈልግም የሚቃጠል መሥዋዕትም አያስደስትህም ለእግዚአብሔር መቅረብ የሚገባው መሥዋዕት ትሕትና የተሞላበት መንፈስ ነው፤ አምላክ ሆይ! አንተ ትሑት የሆነውንና ለንስሐ የተዘጋጀውን ልብ አትንቅም»* በማለት ጸልዮአል (መዝ. 51፥1–2፤ 10፤ 16–17)።

5–7 እዚህ ላይ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ከመዝ. 40፥6–8 ይጠቅሳል። እዚህም ላይ እግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕትንና መባን እንደማይፈልግ በድጋሚ እናነባለን። እግዚአብሔር የሚፈልገው መሥዋዕት የእንስሳትን ስጋ ሳይሆን በፍጹም መታዘዝ ለእርሱ የሚቀርበውን ሰውነት ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር ለክርስቶስ ሰውነትን *አዘጋጀለት* (ቁ. 5)። በፍጹም መታዘዝ ክርስቶስ ሰውነቱን መሥዋዕት ባደረገ ጊዜ እግዚአብሔር ደስ ተሰኘ። ክርስቶስም፡– *«ፈቃድህን ለመፈጸም መጥቻለሁ»* አለ። ከሁሉም ይበልጥ እግዚአብሔር የወደደው የክርስቶስን መታዘዝ ነበር። የብሉይ ኪዳኑ ነቢይ ሳሙኤልም፥ *«እግዚአብሔር የሚወድደው የቱን ይመስልሃል? መታዘዝን ወይስ ቁርባንና መስዋእት ማቅረብን? ለእርሱ መታዘዝ ምርጥ የበግ መሥዋዕት ከማቅረብ ይበልጣል»* ብሎአል (1ሳሙ. 15፥22)።

ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሰው *መጽሐፍ*፥ ስለ ክርስቶስ ብዙ ትንቢቶችን አካትቶ የያዘው ብሉይ ኪዳን ነው። ክርስቶስ ራሱ የእነዚህ ትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜ ነው። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ተገልጾአል። በክርስቶስ ሕይወት ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹም በሆነ ሁኔታ ተፈጽሟል።

8–9 ፍጹምና የመጨረሻ መሥዋዕት አድርጎ ክርስቶስ ራሱን ለማቅረብ በመጣበት ጊዜ *ሁለተኛውን* ኪዳን በቦታው ለመተካት *የመጀመሪያውን* ኪዳን «ሽሮአል» (ቁ. 9)።

10 *በዚህም ፈቃድ* ማለትም፤ የእግዚ አብሔርን ፈቃድ በመፈጸምና ሰውነቱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ፥ ክርስቶስ በውስጥም በውጪም ቅዱሳን አደረገን። ክርስቶስ ሰውነቱን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብና በመሥዋዕትነቱም *ቅዱሳንና ንጹሐን ነቀፋም የሌለብን* አድርጎ በፊቱ እንዲያቀርበን የእግዚአሔር ፈቃድ ነበር (ቆላ. 1፥21–22)።

11–12 እዚህ ላይ ጸሐፊው በዕብ. 1፥3፤ 7፥27፤ 9፥25–26 ያነሳቸውን አሳቦች በድጋሚ ያቀርባል። የአሮጌው ኪዳን ካህናት ደግመው ደጋግመው መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር። ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብና በፊቱም ለማረፍ አይችሉም ነበር። *ሥራቸው ፈጽሞ* አልተጠናቀቀም። ክርስቶስ ግን በእግዚአብሔር ፊት ማረፍ ብቻ ሳይሆን፥ እንዲያውም በእግዚአብሔር ቀኝ በዙፋን ተቀምጦአል። እግዚአብሔር ክርስቶስን ከአሳፋሪው የመስቀል ሞት አስነሳው፤ ወደ ከፍተኛው የክብር ስፍራም ከፍ አደረገው (ፊል. 2፥8–9 ይመለከቷል)።

13 ዕብ. 1፥13 እና ገለጻውን ይመለከቷል።

14 ቁ. 10 ላይ ጸሐፊው *ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በማያዳግም ሁኔታ መሥዋዕት ሆኖ በመቅረቡ ምክንያት ተቀድሰናል ብሎ ነበር*። ጸሐፊው ለማለት የፈለገው ይህንን ነው፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸድቀናል (ሮሜ 5፥1)፤ የክርስቶስ ሥራ ተፈጽሞአል። በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ለዘላለም ተቀድሰዋል።

ታዲያ ለምንድነው ቁ. 14 ላይ ጸሐፊው ገና ሥራው ያልተጠናቀቀ ይመስል *ፍጹሞች ስለሚያደርጋቸው* የሚለው? ምክንያቱ ይህ ነው፥ ምንም እንኳ ከላይ የተጻፈው በሙሉ እውነት ቢሆንም፥ በዚህ ምድር እስካለን ድረስ ገና ሙሉ በሙሉ ቅዱሳን ወይም ፍጹማን አልሆንንም። በየጊዜው ኃጢአት እናደርጋለን። እግዚአብሔር በቅድስና እንድናድግ ይፈልጋል። በዚህ ሕይወት እያለን ቅዱሳን ሊያደርገን ይፈልጋል። ስለዚህም በአንድ መንገድ በዚህ ሕይወት እያለን ለዘላለም እንደተቀደስንና ፍጹማን መሆናችንን መረዳት ይቻላል። በሌላ መንገድ ደግሞ በዚህ ምድር እስካለን ድረስ፥ በየዕለቱ ፀባያችን በዚያው ቅድስና ማደግ ይኖርብናል (ፊል. 1፥6፤ 2፥12–13 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)።

15–18 እዚህ ላይ ጸሐፊው እንደገና ከኤር. 31፥33–34 ይጠቅሳል (ዕብ. 8፥10፤ 12–13 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)። በኤርምያስ አማካይነት የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያስተውሷል (ቁ. 15)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ቃል በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን መረዳት አለብን።

እነዚህን ቁጥሮች ከኤርምያስ በመጥቀስ የዕብራውያን ጸሐፊ አዲሱ ኪዳን ፍጹምና የመጨረሻ መሆኑን ሊያሳየን ይፈልጋል። አሁን የእግዚአብሔር ትእዛዝ በሰዎች ልብ እና አእምሮ ተጽፎአል። ከእንግዲህ ወዲህ ኃጢአታቸው አይታሰብባቸውም። ኃጢአት ከተወገደላቸው ደግሞ ሌላ መሥዋዕት አያስፈልጋቸውም (ቁ. 18)።

አዲስ እና ዘላለማዊ መንገድ (10፥19–25)

19 አሁን በዚህ መልእክት ውስጥ በጣም ጠቃሚ ወደሆነው ክፍል መጥተናል። በመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ምዕራፎች የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ስለ አሮጌውና ስለ አዲሱ ኪዳን፥ ስለ አሮጌውና አዲሱ ክህነት፥ ስለ አሮጌው የእንስሳት መሥዋዕትና ስለ አዲሱ የኢየሱስ ሰውነት መሥዋዕት ገልጾአል። ታዲያ፥ ከእነዚህ ነገሮች የምንረዳው ምንድነው?

እንግዲህ . . . ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚያስችለንን መተማመኛ አግኝተናል[18] *. . . ስለዚህ . . . ቅን ልብና እውነተኛ እምነት ይዘን ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ* (ቁ. 22)። ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እስክንሞት ድረስ መጠበቅ አያስፈልግም፤ በእምነት አማካይነት አሁኑኑ ወደ ፊቱ መቅረብ እንችላለን።

እስቲ፥ ለቅጽበት ያህል ስለዚህ ቁጥር መጀመሪያ ቃል እናስብ። ጸሐፊው *እንግዲህ* ነበር ያለው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ «እንግዲህ» የሚለውን ቃል ተከትለው ብዙ ጠቃሚ ዐረፍተ ነገሮች ይሰነዘራሉ (ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ሮሜ 5፥1 እና 8፥1 ናቸው)። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ «እንግዲህ» በኃጢአት ላይ ይፈርዳል። እግዚአብሔር መሐሪ ነው፤ «እንግዲህ» ኃጢአታችንን ይቅር ይለናል። ክርስቶስ ጽድቃችን ነው፤ «እንግዲህ» በክርስቶስ በማመናችን ጸድቀናል። ክርስቶስ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ አውጥቶናል፤ «እንግዲህ» ኩነኔ የለብንም (ሮም 8፥1)። ክርስቶስ ፍጹም ሊቀ ካህናታችን ነው፤ ራሱን ፍጹም መሥዋዕት አድርጎ ስላቀረበ ለዘላለም ፍጹማን ሆነናል፤ «እንግዲህ» *በኢየሱስ ደም አማካይነት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን* እንገባለን። የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፤ «እንግዲህ» ወደ ምድራዊ አባቶቻቸው ልጆች *በመተማመን* እንደሚቀርቡ ሁሉ፥ አማኞችም ወደ ሰማያዊ አባታቸው ፊት *በመተማመን* ይቀርባሉ (ዕብ. 4፥16 ይመለከቷል)።

---

18 አስፈላጊ አይደለም

ለመሆኑ ደካማና ኃጢአተኛ ሰዎች የሚጸድቁትና እንደ ልጆች ሁሉ በነፃ ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ የሚችሉት በየትኛው ሌላ ሃይማኖት ነው? በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ካልሆነ በቀር በየትኛውም መንገድ አይቻልም።

ቁ. 10 ላይ ጸሐፊው *ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ ብማያዳግም ሁኔታ መስዋእት ሆኖ በመቅረብ ምክንያት ተቀድሰናል* ብሏል። እዚህ ቁ. 29 ላይ ደግሞ *በኢየሱስ ደም* ተቀድሰናል ይላል። በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ ጸሐፊው በኢየሱስ ሞትና መሥዋዕትነት ተቀድሰናል፤ ጸድቀናል ማለቱ ነው። ኢየሱስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ባቀረበበት ጊዜ *ሥጋው* ተቆረሰ ደሙም ፈሰሰ። የኢየሱስ ሰውነትም ሆነ ደሙ አስፈላጊዎቻችን ናቸው። በመጨረሻው ራት ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ *«ይህ ለእናንተ የሚሰጥ ስጋዬ ነው . . . ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰሰው ደሜ የሚፈጸም አዲስ ኪዳን ነው»* ብሎአቸዋል (ሉቃ. 22፥19–20)። በሌላ ወቅት ደግሞ ኢየሱስ ለተከታዮቹ «. . . *የሰው ልጅ የሆነውን (የክርስቶስን) ሥጋ ካልበላችሁ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ የዘላለም ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላና ደሜንም የሚጠጣ ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው»* ብሎአቸዋል (ዮሐ. 6፥53–54)። እንደ አሮጌው ኪዳን ሁሉ፣ በአዲሱ ኪዳንም *ደም ካልፈሰሰ የኃጢአት ስርየት የለም* (ዕብ. 9፥2)። ስለዚህም በአዲሱ ኪዳን እኛን በደሙ ለመቀደስ ኢየሱስ መሞት ብቻ ሳይሆን፣ ደሙንም ማፍሰስ ነበረበት።

20 *ወደ ቅድስተ ቅዱሳን* የምንገባው እንዴት ነው? ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚያስገባ *አዲስና ዘላለማዊ መንገድ* ኢየሱስ ከፍቶልናል። ኢየሱስ *ዘላለማዊ* እንደሆነ ሁሉ ይህም መንገድ ዘላለማዊ ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ *«እኔ መንገድ፣ እውነት ሕይወትም ነኝ። በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ማንም ወደ አብ የሚመጣ የለም»* (ዮሐ. 14፥6)። የኢየሱስ አካል በቅድስትና በቅድስተ ቅዱሳን መካከል እንደነበረው መጋረጃ ነበር (ዕብ. 9፥3)። ኢየሱስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ቆሞአል ማለት እንችላለን፤ በሰው መካከል የቆመው ከመጋረጃው በስተውጪ ሲሆን፣ በእግዚአብሔር መካከል የቆመው ደግሞ ከመጋረጃው በስተውስጥ ነው። ስለዚህም ኢየሱስ በሞተበት ጊዜ *የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ተቀዶ ለሁለት ተከፈለ* (ማር. 15፥37–38)፤ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው መንገድ ሙሉ በሙሉ ተከፍቶአል። ወደ እግዚአብሔር ፊት የገባው ኢየሱስ ብቻ አይደለም፤ (ዕብ. 6፥19–20) እኛ በመሥዋዕትነቱ የነጻን፣ በእምነትም ጽድቁን የተቀበልን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ፊት እንገባለን።

21–22 እዚህ ላይ ሰማያዊው መቅደስ ወይም ድንኳን *የእግዚአብሔር ቤት* ተብሎአል። እኛ አማኞች የእግዚአብሔር ቤት ነን (ዕብ. 3፥6)፤ ክርስቶስ ደግሞ የዚያ ቤት ልጅ እና *ታላቅ ሊቀ ካህን* ነው።

በክርስቶስ በማመን የተሟላ የእግዚ አብሔር ልጅነትን መብት ተቀብለናል። ልጆቹና ወራሾቹ ሆነናል (ገላ. 4፥4–5፤ 7)። ስለዚህም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ልጆች ብንሆንም፣ *ቅን ልብና እውነተኛ እምነት* ይዘን ነው ወደ ፊቱ የምንቀርበው። ያለ እምነት ሌላው ቀርቶ ልጆቹ እንኳ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችሉም (ዕብ. 11፥6 ይመለከቷል)።

ንጹህ ልብ የጠራና የነጻ ልብ ነው። እግዚአብሔርን የሚያዩት *ንጹሕ ልብ ያላቸው* ብቻ ናቸው (ማቴ. 5፥8)። ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ኅሊናችንን *ከሞተ ሥራ* አንጽቶልናል (ዕብ. 9፥14 ይመለከቷል)። ልባችን ተረጭቶአል፤ (ቁ. 22) *ያም* ማለት ልባችን በኢየሱስ ደም ነጽቶአል ማለት ነው። ልባችን ብቻ ሳይሆን ሰውነታችንንም በንጹሕ ውኃ ታጥበናል (1ቆሮ. 6፥11 ይመለከቷል)። ይህ ውጫዊ ወይም የሰውነት መታጠብ የተፈጸመው ስንጠመቅ ነው።[19] ስለዚህም በክርስቶስ ሰውነታችንን (በጥምቀት ሥርዓት) ውስጣችን (በመንፈሳዊ ሁኔታ) ነጽቶአል ማለት ነው።

23 የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ *የምንመሰክረውን ተስፋ* ማለትም የምንመሰክረውን እምነት (ዕብ. 3፥14 ይመለከቷል) *ሳናወላውል አጥብቀን እንያዝ* በማለት በድጋሚ ይመክረናል። እግዚአብሔር በፍጹም አያመነታም። እኛም በፍጹም አናመንታ። የሰው ተስፋ ይናወጥ ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ተስፋ ግን ጽኑ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን ለመፈጸም *ታማኝ* ነው። *ተስፋችን* የተመሠረተው *ታማኙ* እግዚአብሔር በሰጠን ጽኑ ተስፋ ነውና ምንም የምናመነታበት ምክንያት የለንም።

24 አንድ ሰው ማመንታት ከጀመረ እናበረታታው። እርስ በርሳችን *በፍቅርና በመልካም ሥራ ነቅተን* እንኑር። ማንም ከእኛ መካከል እንዳይነጠል ጥንቃቄ እናድርግ። ስንተባበር ጠንካሮች ነን፤ ስንነጣጠል ግን ደካሞች ነን።

25 ከእነዚህ ዕብራውያን አማኞች አንዳንዶቹ *መሰብሰባቸውን ትተዋል*። እንዲህ ዓይነት ነገር በመካከላችን *መታየት የለበትም*። እርስ በርስ በሕብረት ስንገናኝ ብቻ ነው *አንዱ ሌላውን ማበረታታትና* ማፅናናት የሚችለው።

ክርስቲያኖች መሰብሰባቸውን የሚተውት በተለያዩ ምክንያቶች ነው። በአንዳንድ አገሮች ክርስቲያኖች በአንድነት የማይሰበሰቡት የመንግሥት ባለ ሥልጣናትን ስለሚፈሩ ሊሆን ይችላል። ሌሎች ደግሞ በሌሎች አማኞች ላይ ካላቸው ቅሬታ የተነሳ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች በአንድነት መሰብሰብ የማይፈልጉት በትእቢት ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ እነዚህ የሌሎች ክርስቲያኖች ኅብረትና ድጋፍ እንደማያስፈልጋቸው ያስባሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን የማንሄደው በሕይወታችን ካለው ኃጢአት የተነሳ ሊሆን ይችላል። ኃጢአት እያደረግን ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ እንደማንችል እናውቃለን፤ ስለዚህም ኃጢአን ከመተው ይልቅ ኅብረታችንን እንተዋለን። ኅሊናችን ንጹሕ አይደለም፤ በዚህም ምክንያት የሌላው ወንድማችንን ፊት ለማየት እንፈራለን። እነዚህ ሁሉ የተሳሳቱ ምክንያቶች፣ ማለትም ኃጢአተኛ ምክንያቶች ናቸው። ስለዚህም በማንኛውም ምክንያት ቢሆን መሰብሰባችንን መተው የለብንም።

ዘወትር እየተገናኘን እርስ በርሳችን እንበረታታ እንጂ. . . መሰብሰባችንን አንተው፤ ይልቁንም የጌታ መምጫ ቀን መቃረቡን እያስታወሳችሁ ይህን ነገር በይበልጥ አድርጉ። እዚህ ላይ ቀን የተባለው የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ነው። ዕብራውያኑ ያ ቀን በፍጥነት እንዲመጣ ይፈልጋሉ። የተለያየ መከራና ስደት ደርሶባቸዋል፤ ክርስቶስ በፍጥነት ሲመለስ ስደትና መከራው እንደማይቀጥል ተስፋ አድርገዋል። ስለዚህም ጸሐፊው «ከጥቂት ጊዜ በኋላ መከራችሁ ያከትማልና በፍጹም ተስፋ አትቁረጡ» ይላቸዋል።

እንዲህ ያለው አእምሮ ለእኛም ሊኖረን ይገባል። ክርስቶስ መቼ እንደሚመለስ አናውቅም፤ ይሁን እንጂ፣ በሰማይ ያለውን ርስታችንን እንዳናጣ በእምነት ጸንተን መምጣቱን እንጠብቅ (ቁ. 35–36 ይመለከቷል)።

ሆን ተብሎ የተደረገ ኃጢአት (10፥26–31)

26–27 *ሆን ብለን ኃጢአትን ብንሰራ*[20] የክርስቶስ መሥዋዕት አይጠቅመንም፤ *ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት የሚቀርብ ምንም መሥዋዕት አይኖረንም* (ቁ. 26) ምክንያቱም በቁጥር 29 መሠረት *የእግዚአብሔርን ልጅ ረግጠናል፤ የተቀደሥንበትን የቃል ኪዳን ደም* አርክሰናል። የክርስቶስን በረከት ያገኘንበትን የጸጋን መንፈስ ሰድበናል (ማር. 3፥29 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። እነዚህን ነገሮች ካደረግን ደግሞ በክርስቶስ ማመናችንን ትተናል ማለት ነው። በክርስቶስ ማመናችንን ከተውን ደግሞ ደኅንነታችንን አጥተናል። እነዚህን ሁሉ ነገሮች ያደረገ ሰው *መጀመሪያውኑም* እውነተኛ እምነት አልነበረውም ማለትም ይቻላል (1ዮሐ. 3፥6)።

እዚህ ላይ የዕብራውያኑ መልእክት ጸሐፊ የሚናገረው አልፎ አልፎ ስለምንፈጽማቸውና በንስሐ ስለምንመለስባቸው

---

[19] ጥምቀት አካልን በውኃ «መታጠብ» ብቻ አይደለም፤ የውስጣዊ ሕይወታችን መንፈሳዊ መንጻት ምልክት ነው። ሰፋ ላለ ማብራሪያ ከአስተምህሮ ዳሰሳው የውኃ ጥምቀት የሚለውን ይመለከቷል።

[20] አስፈላጊ አይደለም

ኃጢአቶች አይደለም። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቶቹን ኃጢአቶች ይቅር ማለት እግዚአብሔር ዝግጁ ነው (1ዮሐ. 1፥9 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)። ጸሐፊው ንስሐ ሳናደርግ አዘውትረን ስለምንፈጽማቸው ኃጢአቶች ነው የሚናገረው (ዕብ. 6፥4–6 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። በዚህ ሁኔታ ኃጢአት ማድረጉን የሚቀጥል ሰው በፍጹም እውነተኛ እምነት የለውም።

28 በብሉይ ኪዳን መሠረት *የሙሴን ሕግ የጣሰ* ሰው በሞት ይቀጣ ነበር (ዘዳ. 17፥2–7)።

29 *እውነትን ካወቅን በኋላ* ክርስቶስን ከናቅን ደግሞ የሚጠብቀን ቅጣት ምንኛ አስፈሪ ይሆን! (ቁ. 26) ክርስቶስን «ከተቀበልን» በኋላ እንደገና ከካድነው የሚጠብቀን የሥጋ ሞት ብቻ ሳይሆን፥ ዘላለማዊ መንፈሳዊ ሞት ጭምር ነው።

30 እዚህ ላይ ጸሐፊው ከዘዳ. 32፥35–36 ይጠቅሳል። ሆን ብለን ኀጢአት እያደረግን እናምናለን ብንል፥ «እምነታችን» አያድነንም፤ እግዚአብሔር *ይበቀለናል። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ይፈርዳል።* እውነተኞቹን አማኞች ከሐሰተኞቹ አማኞች ይለያል። በአንድ ወቅት ከሕዝቡ ጋር የተቆጠርን፥ በኋላም እምነታችንን የተውን ከሆንን በፍጹም ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አንችልም (ዕብ. 3፥12)።

31 *በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።* ይህ ቃል በዋነኛነት ደረጃ የተጻፈው ለማያምኑ ሳይሆን፥ በመጀመሪያ «አምነው»፣ በኋላ ከእምነት መንገድ ለሚወጡት ነው። ዘወትር ደስ የሚለን ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት ማውራት ነው። ይሁን እንጂ፥ ሆን ብለው ኃጢአትን ለሚያደርጉ፥ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስንም ለማይቀበሉ ግን እግዚአብሔር ፍቅሩንም ሆነ ምሕረቱን እንደማያሳያቸው በፍጹም መዘንጋት የለብንም።

በእምነት ስለ መጽናት የቀረበ ጥሪ (10፥32–39)

32 ክርስቲያን በሆንንበት የመጀመሪያ ጊዜ በንቁ ስሜት፥ በቅንአትና በድፍረት እንሞላለን። በእምነታችን ምክንያትም የሚመጣብንን ችግር በደስታ ለመቀበል ዝግጁ ነን። ከሰይጣን ጋር በሚኖረን ፍልሚያም በእምነታችን ጸንተን እንቆማለን። እነዚህ ዕብራውያንም እንደዚህ ነበሩ (ማቴ. 5፥11–12፤ የሐዋ. 5፥41 ይመለከቷል)።

33 እነዚህ ዕብራውያን *በሰው ፊት ተሰድበዋል፤ ተንገላትተዋል።* ሌሎች መከራ ሲቀበሉም፥ ጥለዋቸው ከመሸሽ ይልቅ አብረው መከራን ተቀብለዋል፤ አንድ አማኝ ስደት ሲደርስበት አብረው ለመሰደድ ዝግጁ ነበሩ (1ቆሮ. 12፥26)።

34 በአዲስ ኪዳን ዘመን እስረኞች በረሃብ እንዲሞቱ ይደረግ ነበር። በሕይወት መቆየት የሚችሉት፥ ወዳጆቻቸውና ዘመዶቻቸው በሚያደርጉላቸው ድጋፍ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፥ አንድ ክርስቲያን የታሰረውን ሌላ ክርስቲያን ለመጎብኘት ወደ እስር ቤት ሲሄድ፥ ብዙውን ጊዜ እርሱ ራሱም ይታሰር ነበርና ወደ እስር ቤት ሄዶ እስረኛ ክርስቲያንን መጠየቅ ለክርስቲያኖች በጣም አዳጋች ነበር። እነዚህ ዕብራውያን ግን በእስር ያሉ ወንድሞቻቸውን በፍጹም አልተውአቸውም። *«ታስሬ ጎብኝታችሁኛል . . . በእውነት እላችኋለሁ ከእነዚህ ከወንድሞቼ አንስተኛ ለሆነው ለአንዱ እንኳ ያደረጋችሁት ሁሉ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው»* (ማቴ. 25፥34–40) በማለት ኢየሱስ የተናገረውን ዘወትር ያስታውሳሉ።

ተቃዋሚዎቻቸው በጣም ብዙና ብርቱ ስለ ነበሩ ከእነዚህ ዕብራውያን ክርስቲያኖች አንዳንዶቹ ርስታቸውን፥ ንብረታቸውንና የቤተሰብ ቅርሶቻቸውን ተነጥቀዋል። ይሁን እንጂ፥ *የተሻለና ለዘወትር የሚኖር ሀብት* (ሮሜ 8፥18፤ 2ቆሮ. 4፥17–18 ይመለከቷል) በሰማይ እንዳላቸው ስለሚያውቁ ይህን ሁሉ የተቀበሉት በደስታ ነበር።

ታዲያ፥ አሁን እነዚህን ዕብራውያን ምን ነካቸው? የቀደመው ቅንአታቸው እየቀዘቀዘ ነው። አሁን ከመከራ መሸሽን ለምደዋል። እንደገና በሀብት ፍቅር ተጠምደዋል። ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ክርስቶስ መከራን ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም።

እንዲህ ያለው ነገር በቤተክርስቲያናችንስ እየተፈጸመ ይሆን? ለክርስቶስ የነበረን የመጀመሪያ ፍቅር ቀዝቅዞብናል? ወንድሞችና እህቶች እንደዚህ መሆን የለበትም! *«በትዕግሥት መፅናትህንና ስለ ስሜ ሳትሰለች መከራ መቀበልህን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን አንድ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ይኸውም የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃል፤ ከመውደቅህ በፊት የት እንደነበርህ አስታውስ፤ ይህን ባታደርግ ግን ወደ አንተ እመጣለሁ፤ ንስሐም ካልገባህ መቅረዝህን ከስፍራው አነሣዋለሁ»* (ራእ. 2፥3–5) በማለት ኢየሱስ የተናገረውን አንዘንጋ።

35 ጸሐፊው፥ *እነዚያን የቀድሞዎቹን ቀኖች አስታውሱ* (ቁ. 32) ይላል። በእነዚያ ቀኖች ድፍረት ነበራችሁ። ስለዚህ አሁን *ታላቅ ሽልማት የምታገኙበትን መተማመኛችሁን አትጣሉት።*

36 እግዚአብሄር እንደሚሸልመን ተስፋ ሰጥቶናል። በእኛ በኩል ደግሞ መጽናት አለብን፤ እስከ መጨረሻው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ አለብን፤ አለበለዚያ ግን ሽልማታችንን እናጣለን። *እግዚአብሔር ሊሰጠን ቃል የገባልን* ነገር ይቀርብናል።

37–38 እዚህ ላይ ጸሐፊው ከእንባቆም 2፥3–4 ይጠቅሳል። *መምጣት የሚገባው* ማለትም ክርስቶስ ይመጣል *አይዘገይም* (2ጴጥ. 3፥8–9 ይመለከቷል)። ቁ. 38 ላይ ጻድቅ የተባለው፥ በመከራው ውስጥ የሚጸና አማኝ ነው፤ ይህ ሰው *በእምነት ሕይወትን ያገኛል። ወደ ኋላው ቢያፈገፍግ ግን* እግዚአብሔር ደስ አይሰኝበትም።

39 ስለዚህ ወደ ኋላ አናፈገፍግ። የምናፈገፍግ ከሆነ፥ ሽልማታችንን ማጣት ብቻ ሳይሆን (ቁ. 36)፤ *ከሚጠፉት ሰዎች* ወገን እንሆናለን (ማር. 8፥35፤ 13፥13፤ ሉቃ. 21፥19 ይመለከቷል)።

ምዕራፍ 11

የእምነት ሰዎች–ከአቤል እስከ አብርሃም (11፥1–16)

1–2 ሰዎች በሁለት ነገሮች እምነት ሊኖራቸው ይችላል፥ *በተስፋ በምንጠብቃቸው ነገሮች* ማለትም ወደ ፊት ይሆናሉ በምንላቸው ነገሮች እና *በማናያቸው ነገሮች።* ሰዎች እምነታቸውን ከሚያኖሩባቸው የማይታዩ ነገሮች ዋናው፥ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ተስፋ ከምናደርግባቸው ነገሮች ዋናው ደግሞ የእግዚአብሔር ተስፋ ፍጻሜ ነው።

አንድን ነገር በዓይናችን ካየነው፥ በዚያ ነገር መኖር እርግጠኛ እንሆናለን። በተመሳሳይ መንገድም ምንም እንኳ በዓይናችን ባናየውም፥ የተለያዩ ነገሮች መኖራቸውን በእምነት እናረጋግጣለን። ተስፋን በመሳሰሉ የወደፊት ነገሮችም እንዲሁ ነው። እነዚህ ነገሮች በዓይን አይታዩም፤ ይሁን እንጂ፥ በእምነት አማካይነት የተሰጠን ተስፋ እንደሚፈጸም እርግጠኞች እንሆናለን።

ስለዚህም እምነት የማይታዩ ነገሮች እውነት እንደሆኑና የወደፊቱ ተስፋዎችም በትክክል እንደሚፈጸሙ የምናረጋግጥበት ዋስትና ነው።

ይህም ብቻ አይደለም። የእውነተኛ እምነት ማረጋገጫው ፍሬው፤ መልካም ሥራና መታዘዝ ናቸው። በእግዚአብሔር እናምናለን ካልን፥ የሚናገረንን ማድረግ አለብን። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የእምነት ሰዎች በሙሉ እምነታቸውን በሥራቸው አስመስክረዋል። በድርጊት የማይገለጽ እምነት ሙት እምነት፥ የሐሰት እምነት ነው (ያዕ. 2፥14፤ 17፤ 20–24 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት የእምነት ሰዎች የተቀመጡት፥ በታሪክ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት ነው። በየትኛውም መልኩ ቢሆን የእነዚህ ሰዎች እምነት በእግዚአብሔር የነበራቸው እምነት ነው። እግዚአብሔር ተስፋ ሰጣቸው፤ እነርሱም አመኑ። እግዚአብሔር አዘዛቸው እነርሱም ታዘዙ። በእነዚህ ሰዎች እምነት አማካይነት እግዚአብሔር ለእስራኤል፥ ለአይሁድ ሕዝብ የነበረውን ዓላማ ፈጸመ። ስለዚህም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ከመጀመሪያው አንስቶ ክርስቶስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ያለውን የአይሁድ ሕዝብ ታሪክ እጥር–ምጥን ባለ ሁኔታ ያቀርባል። ይህን በመሰለ ሁኔታ ጸሐፊው የብሉይ ኪዳንን ዝርዝር ያሰጠናል።

በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱትን ታማኝ ሰዎች ምሳሌ በማድረግ ጸሐፊው፣ የእግዚአብሔርን ተስፋና የእግዚአብሔርን ኃይል እንድንቀበል ከተፈለገ፥ ከሁሉም በላይ አንድ ነገር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ሊያሳየን ይፈልጋል። እርሱም እምነት ነው።

3 ይሁን እንጂ፥ ስለ እነዚህ የእምነት ሰዎች ከመዘርዘሩ በፊት ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፍጥረቱ ያስባል። በዓይናችን ማየት የማንችለውን በእምነት «ማየት» እንደምንችል ሁሉ፥ እግዚአብሔር ዓለሞችን የፈጠረውም ከማይታየው ነገር ነው። እግዚአብሔር ዓለሞችን የፈጠረው በትእዛዝ ብቻ ነበር እንጂ፥ ቀድሞ ከነበሩ ነገሮች አይደለም። እግዚአብሔር ከመናገሩ በፊት ምንም አልነበረም። ተናገረ፤ ፍጥረትም ኅልውና አገኘ (ዘፍ. 1፥3፤ 9፥11፤ 24)።

ምድርንና ሰማይን ስንመለከት በውስጣቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ጠንቅቀን መረዳት ያዳግተናል። ምድር፥ ፀሐይ፥ ከዋክብት ማን እንደሠራቸው ማወቅ አይቻለንም። በእምነት ግን እናውቃለን። በእምነት የሚታዩት ነገሮች ሁሉ በማይታየው እግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩ እናውቃለን።

4 *አቤልና ቃየል* የመጀመሪያው ሰው የአዳም ልጆች ናቸው (ዘፍ. 4፥1–2)። አቤል ጻድቅ ነበር፤ ቃየል ግን አልነበረም። ስለዚህም ከቃየል ይልቅ የአቤል *መሥዋዕት* በልጦ ተገኘ (ዘፍ. 4፥3–7፤ 1ዮሐ. 3፥12)። *እግዚአብሔር ደጋግ ሰዎች ሲጸልዩ ይሰማቸዋል፤ ኃጢአተኞች የሚያቀርቡለትን መሥዋዕት ግን ይፀየፋል* (ምሳ. 15፥8)። *አቤል በእምነቱ ጻድቅ መሆኑ ተመሰከረለት፡፡* ያም ማለት በእግዚአብሔር በማመኑ፥ እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን መሰከረለት ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እምነትና ጽድቅ ሁልጊዜ አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው፤ አይነጣጠሉም። በእምነት አቤል ጻድቅ መሆኑ ተመሰከረለት፤ ስለዚህም ያቀረበውን መሥዋዕት እግዚአብሔር ተቀበለለት፤ እግዚአ ብሔርን ደስ አሰኘ።

ከዚያ በኋላ በቁጣና በቅንዓት ተነሳስቶ ቃየል ወንድሙን አቤልን ገደለው። ይሁን እንጂ፥ አቤል ዛሬም እየተናገረ ነው። እግዚአብሔር እንዲፈርድለት *ደሙ ከምድር እየጮኸ ነው።* (ዘፍ. 4፥10) በጽድቅ ምሳሌነቱም አቤል ዛሬም እንኳ ይናገራል።

5 *ሔኖክ* ከአዳም በኋላ ሰባተኛ ትውልድ ነው (ዘፍ. 5፥21–24)። በዘፍ. 5፥24 መሠረት ሔኖክ *የኖረው የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል* ማለትም ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ ነበር። ስለዚህም የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ስለ ሔኖክ ሲናገር፥ *እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመሰከረለታል* ይላል (ቁ. 6)። በእርሱ የማናምን ከሆነ እንዴት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ይቻላል?

ሔኖክ በእምነት በሕይወት እያለ ወደ ሰማይ ተወሰደ። በእምነቱ ምክንያት እግዚአብሔር ከሞት አዳነው።

በእግዚአብሔር ላይ እውነተኛ እምነት እንዲኖረን ከተፈለገ፥ በመጀመሪያ እግዚአብሔር *መኖሩን ማመን* አለብን። በቃሉና በተስፋውም ማመን አለብን (ቁ. 1 እና ገለጻውን ይመለከቷል) እርሱን *ለሚፈልጉት* ይሸልማቸዋል። ይህም ማለት እግዚአብሔርን አጥብቀን ከፈለግነው፥ እናገኘዋለን፤ ካገኘነውም ይባርከናል ማለት ነው። እግዚአብሔር *«ትፈልጉኛላችሁ፤ የምትፈልጉኝም በሙሉ ልባችሁ ስለሆነ ታገኙኛላችሁ»* (ኤር. 29፥13) ብሏል። *ያዕቆብም ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል* አለ (ያዕ. 4፥8)። ሔኖክና በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት የእምነት ሰዎች፤ *በሙሉ ልባቸው* እግዚአብሔርን ፈለጉት፤ እንደሚሸልማቸውም የማይናወጥ ተስፋ ነበራቸው።

7 *ኖኅ* ከአዳም ጀምሮ ዘጠነኛው ትውልድ ነው። በዚያ ዘመን ከኖኅ በቀር ሰዎች ሁሉ ክፉ መንገድን መከተል ጀመሩ። ስለዚህም እግዚአብሔር (ከኖኅና ከቤተሰቡ በስተቀር) የጥፋት ውኃ በምድር ላይ እንዲመጣ በማድረግ ሰዎችንና ሕይወት ያላቸው ነገሮችን በሙሉ ለማጥፋት ወሰነ። ኖኅ ጻድቅ ሰው ነበር (ዘፍ. 6፥9) ስለዚህም እርሱና ቤተሰቡ እንዲድኑ ትልቅ መርከብ እንዲሠራ እግዚአብሔር አዘዘው።

ኖኅ መርከብ በሚሰራበት ወቅት የሚመለከቱት ሁሉ ሳያፌዙበት አልቀሩም። በእነርሱ አመለካከት ከባሕር በጣም በራቀ ስፍራ ሆኖ መርከብን መሥራት ፈጽሞ ሞኝነት ነበር። ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ቃል እምነት ነበረው። በእምነቱም *ዓለምን ኮነነ*[21] ኖኅ በእምነቱ ዳነ። ባለማመንና በዓመፅ ምክንያት ግን ዓለም ተፈረደበት፤ ተደመሰሰ (ዘፍ. 6፥13–22፤ 7፥12–24)።

8 እግዚአብሄር *አብርሃምን* የገዛ አገሩን ትቶ ጨርሶ ወደማያውቀው ሩቅ አገር እንዲሄድ አዘዘው። እንደሚባርከውና *ታላቅም ሕዝብ* እንደሚያደርገው እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ሰጠው (ዘፍ. 12፥1–2)። *አብርሃም በእምነት ታዘዘ።* መታዘዝ የእምነት ማረጋገጫ ነው። የአብርሃም እምነት የተረጋገጠውም በዚህ ምክንያት ነበር። *አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት* (ዘፍ. 15፥6)።

9 አብርሃም እግዚአብሔር በርስትነት እንደሚሰጠው ተስፋ የገባለትን ምድር በጭራሽ አላገኘም። በዚያ *ተስፋ ምድር* የኖረው መፃተኛና እንግዳ ሆኖ ነበር። ይሁን እንጂ፥ አብርሃም እግዚአብሔር ያንን ምድር ለዘሮቹ እንደሚሰጥ በእምነት ተረድቶአል። በመጨረሻ ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ፥ በኢያሱ መሪነት የአብርሃም ዘሮች ተስፋ የተገባላቸውን ምድር ወርሰዋል (ኢያሱ 1፥1–3)።

10 አብርሃም ይህን ያህል የታገሰው እንዴት ነው? የራሱን አገርና ቤት ለቅቆ ተሰዶአል። በጭራሽ ወደማያውቀውም ባዕድ አገር መጥቶአል። ይሁን እንጂ፥ ያ ምድር አልተሰጠውም። ለምንድነው አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ያላጉረመረመው? መልሱ፥ አብርሃም ከዚህ ዓለም ምንም ርስት አይፈልግም ነበር። ለዘላለም ጸንታ የምትኖረውን፥ ፈጽሞ የማትጠፋውን ጽኑ *መሠረት ያላትን ከተማ* ነበር የሚጠብቀው። ይህችም ሰማያዊት ከተማ ነች (ዕብ. 12፥22፤ 13፥14 ይመለከቷል)።

11 እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮቹን *ታላቅ ሕዝብ* እንደሚያደርጋቸው ተስፋ ሰጥቶት ነበር (ዘፍ. 12፥2)። ያ ተስፋ እንዲፈጸም ደግሞ አብርሃም ልጅ መውለድ ነበረበት (ዘፍ. 15፥2–4)። ይሁን እንጂ፥ አብርሃምም ሆነ ሚስቱ ሣራ በጣም አርጅተዋል፤ አንድም ልጅ አልነበራቸውም። አብርሃም የመቶ ዓመት፥ ሣራ ደግሞ የዘጠና ዓመት ሰዎች በነበሩበት ጊዜ ግን ይስሐቅን ወለዱ (ዘፍ. 17፥15–17፤ 19፤ 21፥1–3)።

12 የልጅ አባት ለመሆን የአብርሃም አካል *እንደሞተ ሰው* ነበር። ይሁን እንጂ፥ ልጅ ወልዶአል፤ ከዚያም ልጅ እጅግ ብዙ የሆኑ የአብርሃም ልጆች ተገኙ (ዘፍ. 15፥5፤ 22፥17፤ ሮሜ 4፥18–22)።

13 *እነዚህ ሁሉ* ማለትም አብርሃም፥ ሣራ፥ ይስሐቅና ያዕቆብ (ቁ. 8–12) *ቃል የተገባላቸውን ነገር አላገኙም።* የተስፋይቱን ምድር አልወረሱም፤ ዘሮቻቸው ታላቅ ሕዝብ ሲሆኑም አላዩም። የገባላቸውን ተስፋ በሙሉ እግዚአብሔር ወደ ፊት እንደሚፈጽመው ግን እምነት ነበራቸው። በእምነት እነዚህን ነገሮች *ከሩቅ ሆነው* ማለትም፤ በዘመናት ርቀት ተመለከቷቸው። የሞቱትም ይህን እምነታቸውን ይዘው ነበር።

በዚህ ሕይወት እስካለን ድረስ፤ ታላላቅ እምነት ያላቸው ሰዎች እንኳ ሁልጊዜ ተስፋ የተገባላቸውን ነገር እንደማያገኙ መገንዘብ በጣም ይጠቅመናል።

14–16 አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ *በምድር ላይ እንግዶችና መፃተኞች መሆናቸውን ተገነዘቡ* (ቁ. 13)። እውነተኛ መኖሪያቸው፥ እውነተኛ ዜግነታቸው በሰማይ ነበር (ፊል. 3፥20 ይመለከቷል)። ሲናፍቁ የነበረው ለዘላለም *የምትኖረውን ሰማያዊት ከተማ* ነበር።

የእግዚአብሔርን አገር፥ የእግዚአብሔርን ሰማያዊት ከተማ ፈልገዋልና እግዚአብሔርን *«አምላካችን» ብለው ቢጠሩት አያሳፍረውም* (ቁ. 16)። እግዚአብሔር *«የሚያከብሩኝን አከብራለሁ»* ብሎአል (1ሳሙ. 2፥30)። በእግዚአብሔር በማመናቸው አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ እግዚአብሔርን አከብረውታል። ራሱን *የአብርሃም፥ የይስሐቅ፥ የያዕቆብ አምላክ* ብሎ በመጥራቱም እግዚአብሔር አከበራቸው።

---

21 ዓለምን የኮነነው እግዚአብሔር ራሱ እንጂ፥ ኖኅ አይደለም። ይሁን እንጂ፥ ኖኅ ጻድቅ በመሆኑ ጻድቅ ያልሆነውን ዓለም ኮንኖአል። ብርሃን ጨለማን በሚኮንንበት መንገድ፥ ኖኅ ዓለምን ኮነነ፤ ኃጢአተኞች በጻድቃን ፊት መቆም በጣም ይከብዳቸዋል።

(ዘጸ. 3፥6)። ከዚህ የተሻለ፣ ሰው ሊያገኘው ወይም ሊቀዳጀው የሚችለው ምን የላቀ ክብር አለ?

የእምነት ሰዎች – ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ (11፥17–40)

17–19 ልጁን *ይስሐቅን* ወደ ተራራው ጫፍ ወስዶ እንዲሠዋለት እግዚአብሔር አብርሃምን እንዳዘዘው የሚናገረው ታሪክ በዘፍ. 22፥1–18 ተጽፎአል።

በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ማመን በጣም ትልቅ ነገር ነው። አንድን ተስፋ ከተቀበለ በኋላ ተስፋውን እርግፍ አድርጎ መተው ደግሞ እምነት የሚፈተንበት የበለጠ ነገር ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን ያዘዘውም ይህንኑ እንዲያደርግ ነበር። የሰጠውን ልጅ መልሶ ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ በዚህ እግዚአብሔር አብርሃምን *ፈተነው* (ቁ. 17)። በዘፍ. 21፥12 መሠረት እግዚአብሔር ለአብርሃም «*ዘር የሚወጣልህ በይስሐቅ በኩል ነው*» ብሎት ነበር። አሁን ደግሞ ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋ አዝዞታል። አብርሃም እሺ ብሎ ያንን ካደረገ ደግሞ እግዚአብሔር *ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ* በማለት እግዚአብሔር የገባለትን ተስፋ የሚፈጽመው እንዴት ነው? (ዘፍ. 12፥2)።

አብርሃም ምንም ዓይነት ጥያቄ ለእግዚአብሔር አላቀረበም። እግዚአብሔር ከሞት የማስነሳት ችሎታ እንዳለው ፍጹም እምነት ነበረው። የገባውን ተስፋ መፈጸም የእግዚአብሔር ኃላፊነት ነው። መታዘዝ ደግሞ የአብርሃም ኃላፊነት ነው።

የመጨረሻው ጊዜ ሲደርስ፣ ይስሐቅን እንዳይገድል እግዚአብሔር አብርሃምን አገደው። በአንድ መንገድ ስንመለከተው ይስሐቅ ሞቶ ነበር ማለት ይቻላል፤ ስለዚህም ጸሐፊው በተምሳሌታዊ አነጋገር *ልክ ከሞት የመነሳትን ያህል ይስሐቅን እንደገና አገኘው* ይላል (ቁ. 19)።

ከዚያ በኋላ፣ የጌታ መልአክ አብርሃምን፣ «*ልጁን አትንካ፤ ምንም ዓይነት ጉዳት አታድርስበት፤ አንተ እግዚአብሔርን የምትፈራ መሆንህን ተረድቼአለሁ፤ ምክንያቱም አንድ ልጅህን እንኳ ለእኔ ከመስጠት አልተቆጠብህም*» አለው (ዘፍ. 22፥12)። ጌታም፣ «*ብዙ በረከት እንደምሰጥህ በራሴ ስም እምላለሁ። ልጅህን ለእኔ ለመስጠት ስላልተቆጠብህ እኔም ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ. . .የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ*» አለው (ዘፍ. 22፥16–18)።

አንድ ቀን ለእያንዳንዳችንን እግዚአ ብሔር ተመሳሳይ ፈተና ያቀርብልናል። ምናልባትም ደግሞ ደጋግሞ ይፈትነን ይሆናል። የሚፈትነን በተለያየ መንገድ ነው። ይሁን እንጂ፣ መታዘዛችንን ለማየት ምን ጊዜም እምነታችን በተዳከመበትና ፅኑ ባልሆነበት አቅጣጫ ይፈትነናል። ከሁሉም አብልጠን የምንወደውን ነገር እንድናቀርብለት ይጠይቀናል። እንድና ቀርብለት የሚጠይቀንም ነገር ሀብትና ንብረታችንን፣ ችሎታችንን፣ ጊዜያችንን፣ ክብራችንን፣ ቤተሰባችንን እንዲያውም የገዛ ሕይወታችንን እንኳ ሊሆን ይችላል። አብርሃምን እንደጠራው ሁሉ እግዚአብሔር ከጠራን የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን እንኳ ለመታዘዝ ዝግጁ እንሁን (ማር. 10፥17–21፤ 29–30 ይመለከቷል)።

20 ይስሐቅ ሁለት ልጆቹን *ያዕቆብና ዔሳውን* እንደባረካቸው የሚናገር ታሪክ በዘፍ. 27፥1–40 ተጽፎአል። አባት ልጆቹን መባረኩ የአይሁዳውያን ባሕል ነበር። ብዙውን ጊዜ ከፍተኛውን በረከት የሚቀበለው ትልቁ ልጅ ነው። ይሁን እጂ፣ በእርጅና ምክንያት የይስሐቅ ዓይኖች ታውረዋል። ታናሽየው ልጅ ያዕቆብ፣ ዔሳውን ተመስሎ በመቅረብ ይስሐቅን አሳሳተው፤ ለወንድሙ ለዔሳው የሚገባውን ከፍተኛውን በረከትም ወሰደ። እንደተታለለ ካወቀም በኋላ እንኳ ይስሐቅ ለያዕቆብ የሰጠውን በረከት አልወሰደበትም። ከዚህ ይልቅ ግን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ተቀብሎ (ዘፍ. 25፥23) የያዕቆብን በረከት አጸናለት (ዘፍ. 27፥33)። ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ በማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ የሚፈጸመው በያዕቆብ በኩል እንደሆነ ይስሐቅ በእምነት አወቀ።

21 የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ (በብሉይ ኪዳን እስራኤልም ይባላል) *ዐሥራ ሁለት* ልጆች ነበሩት። ያዕቆብ ከሁሉም የሚበልጠውን በረከት የሰጠው ለዐስራ አንደኛ ልጁ *ለዮሴፍ*[22] ነበር (ዘፍ. 49፥26)። ያዕቆብ ሁለቱን የዮሴፍ ልጆችም ባርኮአል፤ ይሁን እንጂ፣ እርሱ ራሱ ከአባቱ ከይስሐቅ የበለጠውን በረከት እደተቀበለ ሁሉ፣ ሆን ብሎ የበለጠውን በረከት የሰጠው ለዮሴፍ ታናሽ ልጅ ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም ዝርያዎች የሰጠውን ተስፋ በማወቁ፣ በረከቱን የሰጠው በእምነት ነበር (ዘፍ. 48፥11–20)።

22 ዮሴፍ በወንድሞቹ ባርያ እንዲሆን ወደ *ግብጽ* ተሸጠ (ዘፍ. 37፥12–36)። በኋላም በመላው የግብጽ ምድር ባለ ሥልጣን ሆነ (ዘፍ. 41፥41–43)። ምንም እንኳ ዮሴፍ ቀሪውን ዕድሜውን ሁሉ ያሳለፈው በግብጽ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ተስፋ ለዘሮቻቸው እንደሚፈጽም ፍጹም እምነት ነበረው። በዚህም ተስፋ መሠረት አጽሙን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲወስዱትና እዚያም እንዲቀብሩት ለልጆቹ ነገራቸው (ዘፍ. 50፥24–26፤ ዘጸ. 13፥19)።

23 አይሁዳውያን ለ430 ዓመት በግብጽ ኖሩ (ዘጸ. 12፥40)። ቁጥራቸው እየበዛ በመምጣቱም ግብፃውያን ይጨቁኑዋቸው ጀመር። አይሁዳውያን በባርነት ቀንበር ነበሩ (ዘጸ. 1፥6–14)። ከዚያም በኋላ ፈርዖን [23] የሚወለዱ ወንድ የአይሁዳውያን ሕጻናት ሁሉ ወዲያውኑ እንዲገደሉ አዘዘ (ዘጸ. 1፥22)። ሙሴ ሲወለድ ግን ወላጆቹ ሸሸጉት (ዘጸ. 2፥1–3)። እግዚአብሔር አንድ የተለየ በረከት ለሙሴ እንዳዘጋጀ ወላጆቹ በእምነት ተረዱ።

24–25 የፈርዖን ልጅ ሙሴን አገኘችው፤ እንደ ልጅዋ አድርጋም አሳደገችው (ዘጸ. 2፥5–10)። ካደገም በኋላ ሙሴ የግብፅ ባለስልጣን ሆነ። ይሁን እንጂ፣ በግብጽ ከነበረው ሀብትና ሥልጣን ይልቅ ከወገኖቹ አይሁዳውያን ጋር መከራ መቀበልን መረጠ (ዘጸ. ፪፥11–12)።

26 ሙሴ *የግብጽን ሀብት* ተወ። ከጠቅላላው የግብጽ ሀብት ይልቅ *ስለ መሲህ መዋረድ* የበለጠ ሀብት መሆኑን አሰበ (ፊል. 3፥7 ይመለከቷል)። ሙሴ ስለ ክርስቶስ አያውቅም፤ ሆኖም ስለ እግዚአብሔርና ስለ ህዝቡ (አይሁድ) ሁሉንም ነገር በመተው፤ በኋላ ክርስቶስ እንዳደረገው አድርጎአል። በክርስቶስና በተከታዮቹ *ውርደት* እንዳደረሰባቸው ሁሉ፣ በሙሴም ላይ ተመሳሳይ ውርደት ደርሶበታል (መዝ. 69፥9፤ 89፥50–51፤ ሮሜ 15፥3፤ 1ጴጥ. 4፥12–14 ይመለከቷል)። ይህ ሁሉ ውርደት ቢደርስበትም እግዚአብሔር አንድ ቀን እንደሚሸልመው አውቆ እስከ መጨረሻው በእምነት ጸና።

ስለዚህም እነዚህ መልእክቱ የተጻፈላቸው ዕብራውያን የሙሴን ምሳሌነት መከተል ይገባቸዋል። ክርስቶስን የማያውቀው ሙሴ፣ ስለ እርሱ መከራ ለመቀበል ዝግጁ ነበር። እነዚህ ክርስቶስን የሚያውቁ፣ መንፈሱንም የተቀበሉ ዕብራውያን ደግሞ ስለ ክርስቶስ መከራን ለመቀበል ይበልጥ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

27 ምንም እንኳ ፈርዖን ሊገድለው ቢፈልግም ሙሴ እግዚአብሔርን እንጂ፣ ፈርዖንን አልፈራም። ስለዚህም በእምነት ግብጽን ለቆ ወጣ፤ በምድያም ምድርም አርባ ዓመት ኖረ (ዘጸ. 2፥15)። ሙሴ *በዓላማው ጸና፤* ምክንያቱም በእምነት የማይታየውን አምላክ አይቶአልና። እዚህ ላይ ሙሴ ለአማኞች ሁሉ መጽናኛ ሆኖአል፤ እኛም ብንሆን እንደ ሙሴ በዓላማችን የምንጸናው፣ በእምነት ዓይኖች የማይታየውን አምላክ ስናይ ነው።

በምድያም የሚቆይበት ጊዜ ካበቃ በኋላ ሙሴ አንድ ቀን የማይታየውን እግዚአብሔር በዓይኖቹ አየ! እግዚአብሔር ለሙሴ የተገለጠለትና ወደ ፈርዖን ተመልሶ እንዲሄድና

---

[22] እግዚአብሔር ሰዎችን የሚመርጠው በውልደት ቀዳሚነታቸው አይደለም። ከያዕቆብና ከዔሣው ታሪክ እንደምንመለከተው በመንፈሳዊ ሁኔታ የመጀመሪያ እንዲሆን በሥጋ የመጨረሻ የሆነውን ይመርጣል (ማር. 10፥31)።

[23] በዚያ ዘመን የግብጽ ንጉሦች ሁሉ ፈርዖን ይባሉ ነበር።

አይሁዳውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ እንዲያወጣ የተናገረው በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ ነው (ዘጸ. 3፥1–10)።

28 በእምነት ሙሴ አይሁዳውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ አወጣ። በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር በግብጽ ላይ የተለያዩ መቅሰፍቶችን አመጣ። ምንም እንኳ መቅሰፍቱ ጽኑ ቢሆንም በመጀመሪያ ፈርዖን አይሁዳውያንን መልቀቅ አልፈለገም ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔር የግብጽን በኩር ልጆች እንዲገድል መልአኩን ላከ (ዘጸ. 11፥1፤ 12፥29–30)። ለምልክት እንዲሆን ለመሥዋዕት የቀረበውን በግ ደም በሮቻቸውን እንዲቀቡ ሙሴ አይሁዳውያንን ያዘዛቸውም በእምነት ነበር። የሚገድለውንም መልአክ፣ ደም የተቀቡ ቤቶችን ሲያይ የአይሁዳውያንን በኩር ልጆች ሳይገድል አልፎ ይሄዳል (ዘጸ. 12፥21–23)። ከተረጨው ደም የተነሳ መልአኩ የአይሁዳውያንን ቤት አልፎ ሄደ፤ ከዚያን ጊዜ ወዲህ የአይሁድ ፋሲካ ተጀመረ (ዘጸ. 12፥24–27)።

በተመሳሳይ መንገድም በክርስቶስ ደም አማካይነት ከእግዚአብሔር ፍርድና ቁጣ እንድናለን። ክርስቶስ ራሱ የፋሲካ መሥዋዕታችን ነው፤ *የፋሲካ በግ* ነው (1ቆሮ. 5፥7)። የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ *የእግዚአብሔር በግ* ነው (ዮሐ. 1፥29)። የዳንነው በክርስቶስ ደም እንጂ በራሳችን ጽድቅ አይደለም።

29 የግብጻውያን በኩር ልጆች በአጥፊው መልአክ እንደተገደሉ ፈርዖን ሲመለከት አይሁዳውያንን ለመልቀቅ ወሰነ። ፈርዖን አይሁዳውያን ከግብጽ ጥቂት ርቀው እንደሄዱ ግን አሳቡን ለወጠና እንዲመልሱአቸው የግብጽን ሠራዊት ሰደደ (ዘጸ. 14፥5–9)። ወደ እነርሱ የሚገሰግሰውን ግዙፍ የግብጽ ሠራዊት ሲመለከቱ አይሁዳውያን በጣም ፈሩ፤ በሙሴ ላይም አጉረመረሙ። ከፊት ለፊታቸው *ቀይ ባሕር*፣ ከኋላቸው ደግሞ የግጽ ሠራዊት ነበር። የመጨረሻው እንደቀረበ አሰቡ (ዘጸ. 14፥10–12)። ሙሴ ግን በእምነት፣ *«አይዞአችሁ አትፍሩ! ባላችሁበት ጸንታችሁ ቁሙ፤ እግዚአብሔር እናንተን ለመታደግ የሚያደርገውን ዛሬ ታያላችሁ»* አላቸው (ዘጸ. 14፥13)። ከዚያም በኋላ በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር ባሕሩን ከፈለ፤ አይሁዳውያንም በእምነት *በደረቅ ምድር እንደሚሻገር ሆነው፣ ቀይ ባሕርን ተሻገሩ*። የሚያሳድዱቸው ግብጻውያን ግን ባሕሩን ለመሻገር ሲሞክሩ ሁሉም ሰጠሙ (ዘጸ. 14፥21–28)።

30 ከግብጽ ከወጡ አርባ ዓመት በኋላ አይሁዳውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር እስራኤል ገቡ። በመጀመሪያ ግን በምድሪቱ የነበሩትን ሕዝብ ተዋግተው ማሸነፍ ይገባቸው ነበር። በመጀመሪያም *የኢያሪኮን* ከተማ መያዝ ነበረባቸው። እንዴት ከተማይቱን እንደሚይዙ እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን መሪ ለኢያሱ ነገረው። ኢያሪኮ በረጅም ግንብ የታጠረች ከተማ ነበረች። አይሁዳውያን መለከታቸውን እየነፉ ለሰባት ቀን ከተማይቱን መዞር ነበረባቸው። በሰባተኛው ቀን ደግሞ ሁሉም አይሁዳዊ ድምጹን ከፍ አድርጎ በአንድነት ይጮሃል፤ የከተማይቱ ግንብም ይወድቃል። ስለዚህም ወደ ከተማይቱ ገብተው ይይዙአታል። ሁሉም ነገር እግዚአብሔር እንደ ነገራቸው ሆኖአል (ኢያሱ 6፥1–5፤ 12–16፤ 20)።

በዚህ ሁኔታ ያችን ታላቅ ከተማ መያዝ ይቻላል ብሎ ማን አሰቦአል? ኢያሱ በእግዚአብሔር የነበረው እምነትም ታላቅ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ይህን በሚመስል ያልተለመደ መንገድ ይሠራል። «*ድል የምትነሣው በመንፈሴ እንጂ በአንተ ኃይልና ብርታት አይደለም* ይላል ጌታ እግዚአብሔር» (ዘካ. 4፥6)።

የኢያሱን እምነት እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን። በእያንዳንዳችን ሕይወት መሸነፍ የሚገባቸው «ኢያሪኮዎች» አሉ። እንደ ኢያሱ ሁሉ በእምነት ልናሸንፋቸው እንችላለን። ጳውሎስ «*የጦር መሣሪያዎቻችንም ምሽግ ለማፍረስ የሚያስችል መለኮታዊ ኃይል ያላቸው ናቸው እንጂ እንደ ዓለም የጦር መሣሪያዎች አይደሉም*» ብሎአል (2ቆሮ. 10፥4)።

31 በመጀመሪያ ኢያሱ *ሰላዮችን* ወደ ኢያሪኮ ላከ፤ *ረዓብ* የምትባል አመንዝራ ሴትም በቤትዋ ደበቀቻቸው። በእስራኤል አምላክ፤ በአይሁድ አምላክ አምናለች። አይሁዳውያን ኢያሪኮን እንደሚደመስሱ በእምነት አውቃለች። በዚህም ምክንያት ኢያሱ የላካቸውን ሰላዮች ደበቀቻቸው። ይህን በማድረግዋም ሕይወትዋን አዳነች (ኢያሱ 2፥1–3፤ 6፤ 8–14፤ 6፥24–25)።

ረዓብ አረማዊ (አይሁድ ያልሆነች) ኃጢአተኛ ነበረች፤ ያም ሆኖ በእምነት እንደ ዳነች ያስተውሏል። ከዚህም በተጨማሪ የተናቀች አመንዝራ ብትሆንም፣ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም ተጠቅሞባታል።

32–34 በእነዚህ ቁጥሮች ከብሉይ ኪዳን የሌሎች አይሁዳውያን መሪዎችን ምሳሌነት ያቀርባል፤ በእምነት አማካይነት እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎችን አከናውነዋል። (መሳ. 7፥19–21፤ 15፥14–16፤ ዳን. 3፥16–28፤ 6፥16–22)።

35 ልጆቻቸው ከሞት የተነሡላቸው ሁለቱ ሴቶች በ1 ነገ. 17፥17–24 እና በ2 ነገ. 4፥32–37 ተጠቅሰዋል። ሌሎች የእምነት ሰዎች ደግሞ በሰማይ *የበለጠውን ትንሣኤ ለማግኘት አስበው ከእስራት ነጻ መሆንን እምቢ አሉ*። የዚህን ዓለም «ትንሣኤ» አልፈለጉም።

36–38 እዚህ ላይ በእምነታቸው ምክንያት ብዙ መከራ ስለ ደረሰባቸው የብሉይ ኪዳን የእምነት አርበኞች እናነባለን። ይሁን እንጂ፣ ሁሉም እስከ መጨረሻው ጸንተዋል. . . *ዓለም ለእነርሱ ተገቢ ስፍራ ሆና አልተገኘችም* (ቁ. 38)። በዓለማውያን ዓይን እነዚህ የእምነት አርበኞች ስፍራ የሚሰጣቸው አይደሉም፤ በእግዚአብሔር ፊት ግን ትልቅ ቦታ ያላቸው ናቸው። ሰማያዊት የእግዚአብሔር ከተማን ለመውረስ የሚገባቸው ሆነው ተገኝተዋል (ቁ. 10፥ 16)።

39 ከብሉይ ኪዳን የእምነት አርበኞች አንዱም እንኳ *የተሰጣቸውን ተስፋ ገና አላገኙም*። እርግጥ ነው አንዳንዶቹ ጥቂት ተስፋዎች ተፈጽመውላቸው አግኝተዋል። ይሁን እንጂ፣ የበለጠውን ተስፋ ማለትም አዳኙ እንደሚመጣ የተሰጠውን ተስፋ አልተቀበሉም ማለትም፤ አንዳቸውም እንኳ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ አላዩም። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ተስፋ ሁሉ የሚበልጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሚገኘው የደኅንነት ተስፋ ነው። በሕይወት በዚህ ምድር በነበሩበት ጊዜ እነዚህ የብሉይ ኪዳን አርበኞች ያንን ተስፋ ተፈጽሞ አላገኙትም።

40 ሆኖም አንድ ቀን፣ እነዚህ የብሉይ ኪዳን የእምነት ሰዎች፣ *ፍጹሞች ይሆናሉ*፤ ማለትም እኛ እንደምናገኘው ያለ የተሟላ ደኅንነትን ያገኛሉ። ክርስቶስ እንደገና ሲመለስ እነዚህ የብሉይ ኪዳን አርበኞች በእርሱ ካመንነው ከእኛ ጋር ከሞት ይነሣሉ፤ የዘላለምንም ሕይወት ይቀበላሉ።

ምዕራፍ 12

ኢየሱስ ከሁሉም የበለጠ የእምነት ምሳሌ (12፥1–3)

1 *እንግዲያውስ* ስለ ብዙ የእምነት አርበኞች ከምዕራፍ 11 የተማርነውን ምሳሌ በማድረግ *በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት በመጽናት እንሩጥ*። የነበራቸውን እምነት በሕይወታቸው አስመስክረዋልና እነዚህ የብሉይ ኪዳን ጀግኖች *ምስክሮች* ተባሉ።

የክርስቶስ ተከታይ ሕይወት እንደ ሩጫ ነው። በሩጫ ውድድር የሚካፈሉ ሰዎች፣ በሚቻላቸው መጠን በፍጥነት ይሮጣሉ። ሩጫው ከመጀመሩ በፊት የማያስፈልጉ ልብሶችን ሁሉ ያወልቃሉ። ማንም የከት ልብሱን ለብሶ ወይም በዕንቁዎች አጊጦ አይሮጥም። በመሠረቱ መልካም ልብሶችን መልበስ ወይም በዕንቁዎች ማጌጥ በራሱ ክፉ አይደለም፤ በሩጫ ውድድር ስንጠቀምባቸው ግን ትክክል አይሆኑም! ለሩዋጩ መሰናክል ናቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታም በክርስትና ሕይወታችን በራሳቸው ስሕተት ያልሆኑ፣ ለመንፈሳዊ ሩጫችን ግን መሰናክል የሚሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። በተቻለን መጠን በፍጥነት መሮጥ እንድንችል *እንደሸክም የሆነብንን* ነገር ሁሉ እናስወግድ። እነዚህ እንቅፋት የሚሆኑብን ነገሮች መልካም ሊሆኑ ይችላሉ፤ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የምናውለውን ጊዜ ግን ይሻሙብናል። እንደዚህ ዓይነት እንቅፋቶች በሕይወታችን መኖር አለመኖራቸውን ለማወቅ፣ እያንዳንዳችን ራሳችንን መመርመር ይኖርብናል። ይህንንም ስናደርግ በአንድ ሰው ሕይወት መሰናክል የሆኑ ነገሮች ለሌላው ሰው ሕይወት

መሰናክል ሊሆኑ እንደማይችሉ ማስታወስ አለብን። መሰናክሎች ለሁሉም አንድ ዓይነት አይደሉም።

ይሁን እንጂ፣ ምንጊዜም ቢሆን ኃጢአት ማንንም ወደ ኋላ ይይዛል። ሩጫውን እንድንፈጽም ከተፈለገ *በእኛ ላይ የተጣበቀውን ኃጢአት* ማስወገድ አለብን። ምንም ያህል ትንሽ መስሎ ቢታየንም ኃጢአትን ማስወገድ ይኖርብናል። ቶሎ ካላስወገድናቸው ጥቃቅን ኃጢአቶች ያድጉና ያጠቁናል።

በአንድ መንገድ ደግሞ የክርስትና ሕይወታችን ከሩጫ ውድድር የተለየ ነው። በሩጫ ውድድር አሸናፊ የሚሆነውና የመጀመሪያውን ሽልማት የሚያገኘው አንድ ሰው ብቻ ነው። በክርስትና ሕይወታችን «ሩጫ» ግን እስከ መጨረሻው የሚሮጡ ሁሉ አንድ ዓይነት ሽልማት ማለትም፤ የዘላለም ሕይወትን ያገኛሉ። ይህ እውነት ቢሆንም መሮጥ ያለብን አንድ ሰው ብቻ እንደሚያሸንፍ ዓይነት ሆነን ነው ። እንደዚያ የምንሮጥ ከሆነ፣ በፍጥነት እንሮጣለን! መልካሙን ሩጫ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሮጥን እርግጠኞች እንሆናለን (1ቆሮ. 9፥24–26)።

2 *ኢየሱስን በመመልከት* እንሩጥ፤ ዓይናችንን ከእርሱ ማንሳት የለብንም። የዚህን ዓለም ደስታ የሚሰጡ ነገሮች ትኩረታችንን አይሳቡት። እንደዚያ የምናደርግ ከሆነ፣ ከአንዱ ወደ ሌላው እንንከራተታለን እንጂ፣ መስመራችንን ጠብቀን መሮጥ አንችልም። ምናልባትም የመጨረሻው ግብ ላይ ሳንደርስ እንቀራለን።

ኢየሱስ *የእምነታችን ለመንጪ* (ጀማሪ) ነው። ከእኛ ቀድሞ ወደ ሰማይ ሄዶአል። ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ጀግኖች እምነት *ለመንጪም* ነው። ገና ከመጀመሪያው ኢየሱስ አብሮአቸው ነበር (1ቆሮ. 10፥3–4 ይመለከቷል)። እኛ እንደምናውቀው ኢየሱስን አላወቁትም፤ ሆኖም መሪያቸው ነበር። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ ኢየሱስ ተናግረዋል፤ ስለዚህም የእምነታቸው *ለመንጪም* ነው።

ኢየሱስ *የእምነታችን ፈጻሚ ነው*። እንዲህም ሲባል እርሱ ራሱ የእምነት ታላቅ ምሳሌ ነው ማለት ነው። የዚህ ምድር ሕይወቱ ሊፈጸም በተቃረበበት ጊዜ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ በፍጹም እምነት ራሱን ለእግዚአብሄር አስረከበ። *«ይህን የመከራ ጽዋ ከእኔ አርቅልኝ፤ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን»* አለ (ማር. 14፥36)። በዚያች ቀን እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር እንደ ነበር የሚያሳይ ምንም ምልክት አልነበረም። ማንም የሚያጽናናው አልነበረም። ሰዎች ሁሉ ትተውታል፤ ሌላው ቀርቶ ተከታዮቹ እንኳ በዚያ መጨረሻ ሰዓት ትተውታል (ማር. 15፥34)። ይሁን እንጂ፣ *በመስቀል ላይ የመሞትን ውርደት* በትዕግሥት ተቀብሎአል። በሮማውያን ዘመነ መንግሥት በጣም የተጠሉ ወንጀለኞች ብቻ ነበሩ በመስቀል ላይ እንዲሞቱ የሚፈረድባቸው። በመስቀል ላይ ከመሞት የበለጠ ውርደት አልነበረም። ስለዚህም እንዲህ ያለውን ውርደትና መከራ በመታገሡ ኢየሱስ ከሌሎች ሁሉ የሚበልጥ የእምነት ምሳሌ ሆኖልናል።

ኢየሱስ ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ፣ ብዙዎች በዙሪያው ቆመው ያፌዙበት ነበር። *«እርሱ መሲሑ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ እስቲ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም አንይና እንመን»* ይሉት ነበር (ማር. 15፥32)። በአንድ ዓይነት ልዕለ–ተፈጥሮአዊ ኃይል ከመስቀል ወርዶ ቢሆን ኖሮ፣ *የእምነታችን ፈጻሚ* መሆን ባልቻለም ነበር። ልንከተል የሚገባውን ፍጹም ምሳሌ ባልሰጠንም ነበር። በተቃራኒው ግን ኢየሱስ ከተቀበለው መከራ የተነሣ ነበር ፍጹም የሆነው (ዕብ. 2፥10)። እኛም ምሳሌነቱን በመከተል በመከራ ፍጹማን እንሆናለን።

እስከ መጨረሻው በእምነት ብንጸና እኛም ከኢየሱስ ጋር እንከብራለን (ዕብ. 3፥14)። በፊቱ የተቀመጠው *ደስታ* ተካፋዮች እንሆናለን (ዮሐ. 15፥11፤ 16፥22)። እኛም ከእርሱ ጋር እንነግሣለን። *«እኔ ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በአባቴ ዙፋን እንደተቀመጥሁ፣ እንዲሁ ድል የነሣ ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ»* (ራእ. 3፥21) እንግዲህ በዚህ መንገድ ኢየሱስ የራሱን እምነት ፍጹም ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የእኛንም እምነት ፍጹም ያደርጋል ማለት ነው። ኢየሱስ የእምነታችን አመንጪና ጀማሪ ብቻ ሳይሆን የእምነታችን ፈጻሚም ነው። ኢየሱስ በውስጣችን የጀመረውን የእምነት *ሥራ* እርሱ ራሱ ይፈጽመዋል (ፊል. 1፥6)።

3 ከእኛ መካከል ችላ የሚል፣ ተስፋ የቆረጠ አለን? ካለ ኢየሱስን ይመልከት። *ተመልከቱ*። ኢየሱስን ስንመለከት ማለትም እርሱን ስናሰላስል በሚያስፈልገን ጊዜ የሚረዳንን ብርታትና ጸጋ ከእርሱ እንቀበላለን (ዕብ. 4፥16)።

እግዚአብሔር ልጆቹን ይቀጣል (12፥4–13)

4 እዚህ ላይ ጸሐፊው፣ ዕብራውያኑ መከራ የደረሰባቸው ስለ ክርስቶስ እንደሆነና ነገር ግን ገና ደማቸውን እስከ ማፍሰስ ማለትም፤ ለክርስቶስ እስከ መሞት እንዳልደረሱ ይናገራል። አንዳንድ የብሉይ ኪዳን እምነት አርበኞች የተቀበሉትን መከራ ያህል ገና አልደረሰባቸውም። ዕብራውያኑ ፈጥነው ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም፤ መከራው ገና እየተጀመረ ነው! በትንሹ መከራ ተስፋ የሚቆርጡ ከሆነ፣ ይበልጥ የሚከፋው መከራ ሲመጣ ምን ሊሆኑ ነው?

እግዚአብሔር መሐሪ እንደሆነና ሊቋቋሙት የማይችሉት ዓይነት መከራ እንዲደርስባቸውም እንደማይፈቅድ፣ ዕብራውያኑ መገንዘብ ይኖርባቸዋል (1ቆሮ. 10፥13) ከዚህም በተጨማሪ ምንም ዓይነት መከራ ቢደርስባቸውም፣ እንደ እግዚአብሔር ተግሣጽ ነው የደረሰባቸው። ተግሣጽ የፍቅሩ ምልክት እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ምልክት አይደለም (ቁ. 6)።

5–6 እዚህ ላይ ጸሐፊው የሚጠቅሰው ከምሳ. 3፥11–12 ነው። መከራና ሀዘን ሲደርስብን፣ በእግዚአብሔር ላይ እናጉረምርም። እነዚህ መከራና ሀዘን እንዲደርሱብን እግዚአብሔር ቢፈቅድ፣ ለገዛ ራሳችን ጥቅም እንደ ልጆቹ ሊገስጸን መሆኑን እንዘንጋ። ችግርና መከራ የሚደርስብን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነው። ለክርስቶስ በመታዘዛችን ሰዎች ስደት ያስነሱብናል፤ እግዚአብሔር ግን በይበልጥ ለክርስቶስ እንድንታዘዝ ሊገስጸን በዚያ መከራ ይጠቀምበታል።

7–8 ማንኛውም ልጅ ተግሣጽ ያስፈልገዋል። ክርስቶስ ራሱ እንኳ *ከተቀበለው መከራ የተነሣ መታዘዝን ተማረ* (ዕብ. 5፥8)።

ማንም ሰው ዲቃሎችን ለመገሰጽ ደንታ የለውም። ዲቃሎች የምንም ነገር ወራሾች አይደሉም። አባት የሚቀጣው የገዛ ልጆቹን ነው። አንድ ቀን ከፍተኛ ኃላፊነትን እንደሚቀበል ያውቃልና አባት ልጁን ይቀጣል። እግዚአብሔርም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር ሲገስጸን ደስ ይበለን፤ ምክንያቱም ይህ የሚያሳየው እንደ ልጆቹ እንደሚመለከተንና ለትልቅ ኃላፊነትም እያዘጋጀን መሆኑን ነው። ምንም ዓይነት ችግር የማይደርስብን ከሆነ ግን በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጆች መሆን አለመሆናችንን መጠየቅ አለብን።

9–10 እግዚአብሔር ሲቀጣን ምንም ዓይነት ስሕተት አይፈጽምም። ምንጊዜም የእግዚአብሔር ቅጣት ፍትሕ ያለበትና ተመልሶ እኛኑ የሚጠቅም ነው። የሥጋ አባቶቻችን የሚችሉትን ያህል ሥርዓት ሊያስይዙን ቢሞክሩም፣ ስሕተት ፈጽመዋል። ያም ሆኖ ግን እናከብራቸዋለን። እንግዲህ የሥጋ አባቶቻችንን የምናከብራቸው ከሆነ *መንፈሳዊ አባታችንን* (ቁ. 9) እግዚአብሔርንማ ምንኛ ልናከብረው ይገባል።

ለምንድነው እግዚአብሔር የሚገስጸን? እግዚአብሔር የሚገስጸን *የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን* ነው (ቁ. 10)። የእግዚአብሔር ዓላማ ይህ ነው። በአንድ መንገድ በክርስቶስ *መሥዋዕትነት* ተቀድሰናል (ዕብ. 10፥10)። ይሁን እንጂ፣ ይህ የደኅንነታችን *የመጀመሪያ* እርምጃ ነው። *የመጀመሪያው* ቅድስና ገና *በመጀመሪያ* ስናምን የተቀበልነው የክርስቶስ ጽድቅ ነው፤ የጸደቅነውም በዚሁ መሠረት ላይ ነበር (ሮሜ 5፥1)። ሁለተኛ ዓይነት ቅድስና ደግሞ አለ፤ ይህም የሕይወታችን የመጨረሻው ግብ ነው። ይህን ዓይነት ቅድስና ለማግኘት ጊዜ ይወስዳል፤ ሙሉ በሙሉ የምናገኘው ግን በሰማይ ብቻ ነው (ዕብ. 10፥14 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። እስከዚያው ድረስ በተግሳጽ መልክ የተለያዩ ፈተናዎችና መከራዎች እንዲደርሱብን በማድረግ፣ በዚህ ምድር እያለን ይበልጥ እንድንቀደስ ያደርጋል። ጳውሎስ፣ *«ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ብዙ መከራ መቀበል አለብን»* አለ (የሐዋ. 14፥22)።

11 የእግዚአብሔርን ተግሳጽ በሁለት መንገድ ልንቀበለው እንችላለን። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ተግሳጽ ችላ በማለት መቆጣትና ማጉረምረም ሲሆን፤ ሁለተኛው

ደግሞ የእግዚ አብሔርን መንገድ በምስጋና መቀበልና እንዲያስለምነን ፈቃደኛ መሆን ነው። የእግዚአብሔርን ተግሳጽ ችላ የምንል ከሆነ ምንም አይጠቅመንም። ተግሳጹን የምንቀበል ከሆነ ግን ይበልጥ ሕይወታችን *በጽድቅ* (ቅድስና) እና *በሰላም ያድጋል*። ከኃጢአት ወደ ጽድቅና ወደ መታዘዝ እንመለሳለን። የጽድቅ ፍሬ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መፍጠር ነው። *አንተ እኔን ከመቅጣትህ በፊት እሳሳት ነበር . . . ሥርዓትህን እንድማር ስላደረገኝ ተግሳጽህን መቀበሌ ለእኔ መልካም ሆነልኝ* (መዝ. 119፥67፤ 71)።

12 እግዚአብሔር ሲገስጸን ተስፋ አንቁረጥ የተግሳጹ ዓላማ ሊያሳድገንና ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሊያዘጋጀን እንጂ፤ ሊያጠፋን አይደለም። ተግሳጽ ሲመጣ እንዲያስተምረንና እንዲያስለምነን በደስታ እንቀበለው እንጂ በፍጹም አንሸሽ። *ስለዚህ የዛሉትን እጆቻችሁንና የደከሙትን ጉልበቶቻችሁን አበርቱ* ይላል ጸሐፊው (ኢሳ. 35፥3)።

13 በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ተግሳጽ እየተቀበለ ያለ ሰው ካለ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ *አንካሣ* የሆነ ሰው ካለ፣ እንርዳው እናበረታታው (ገላ. 6፥1–2)። ለእግሮቹ *የቀና መንገድ* እናድርግለት (ምሳ. 4፥26)። ጭራሹኑ ተሰናክሎ እንዳይወድቅና ሩጫውንም እንዳያቋርጥ በመንገዱ ላይ ምንም ዓይነት እንቅፋት አናድርግበት።

መመሪያና ማስጠንቀቂያ (12፥14–17)

14 የሚቻላችሁ ቢሆን፣ *ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ* (ሮሜ 12፥18 ይመልከቷል)። ከማንኛውም ሰው ጋር በሰላም መኖር አዳጋች ነው፤ ምክንያቱም አንዳንዶች የሚቃወሙን በክርስቶስ ስላመንን ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን። ከማያምኑ ሰዎች ጋር እንኳ ተቻችለን በሰላም የምንኖር ከሆነ፣ ይልቁንም ከአማኝ ወገኖቻችን ጋር ምንኛ በሰላም መኖር ይገባን ይሆን! (ኤፌ. 4፥3 ይመልከቷል)።

በቅድስናም ለመኖር ትጉ። በክርስቶስ በተሰጠን ጸጋ እና በመንፈስ ቅዱስም አማካይነት በየጊዜው እግዚአብሔር ቅዱሳን ያደርገናል። ከዚያ በተጨማሪ ግን እኛ ራሳችንም ቅዱሳን ለመሆን መትጋት አለብን። የምንቀደሰውም ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ብቻ ነው (ፊል. 2፥12–13 እና ገለጻውን ይመልከቷል)።

«እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ይላል እግዚአብሔር (ዘሌ. 11፥45፤ 1ጴጥ. 1፥15–16)። *የእግዚአብሔር ፈቃድ እንድትቀደሱ ነው* (1ተሰ. 4፥3)። . . . *ያለቅድስና እግዚአብሔርን ማየት አይቻልም* (ማቴ. 5፥8 እና ገለጻውን ይመልከቷል)።

ለመሆኑ የራሳችንን ሕይወትና ቤተ ክርስቲያናችንን ስንመለከት የምናየው ምንድነው? ቅድስናን ወይስ ርኩሰትን፤ ሰላምን ወይም ጸብን። እያንዳንዳችን ራሳችንን እንመርምር።

15 *ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጎድልበት ተጠንቀቁ* (ዕብ. 4፥1 ይመልከቷል)። የእግዚአብሔር ጸጋ ምንጊዜም ቢሆን ሊረዳን ዝግጁ ነው (ዕብ. 4፥16)። አንዳንድ ጊዜ ግን እኛ ራሳችን አንቀበለውም ወይም ተግባራዊ አናደርገውም። ይልቁንም ችላ እንለዋለን። ይህንንም ስናደርግ *ከጸጋው እንርቃለን* (ገላ. 5፥4)።

ለምንድነው አዘውትረን የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል የማንፈልገው? በኃጢአት ምክንያት ነው። በኃጢአት እስከቀጠልን ድረስ የእግዚአብሔርን ጸጋ አንቀበልም። ኃጢአት ዛፉን ሁሉ የሚያመርር *መራራ ሥር* ነው። በውስጣችን ያለ ኃጢአት ጠቅላላ ሕይወታችንን ይበክለዋል። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ ኃጢአት ጠቅላላ ቤተክርስቲያንን ይበክላል፤ *ብዙዎችንም ያረክሳል*። በመካከላችን እንደዚህ ያለ «*መራራ ሥር*» እንዳይኖር ጥንቃቄ እናድርግ። *መራራ ሥር* ካለ ግን በአስቸኳይ ነቅለን እንጣለው (1ቆሮ. 5፥9–11፤ 13 ይመልከቷል)።

16 እዚህ ላይ ጸሐፊው ሁለት የኃጢአት ምሳሌዎችን ያቀርባል። *ሴሰኝነትና ነውረኝነት*። አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን ሴሰኝነት በጣም የተለመደ ኃጢአት ነበር፤ ስለዚህም አዳዲስ አማኞች በዚህ ኃጢአት እንዳይረከሱ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው (1ቆሮ. 5፥1 ይመልከቷል)።

ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ *ነውረኝነት* ነው። ለጥቂት ምድራዊ ጥቅም ብሎ እግዚአብሔር የሰጠውን *ብኩርና* ሽጦአልና የይስሐቅ ልጅ ዔሣው ነውረኛ ሆኖአል። አንድ ቀን ዔሣው በጣም ተርቦ ነበር፤ የሚበላ እንዳለውም ወንድሙን ያዕቆብን ጠየቀው። ያዕቆብም ብልጣብልጥ ነበርና የብኩርና መብቱን ከሸጠለት፣ ምግብ እንደሚሰጠው ነገረው። በጣም ርቦት ነበርና ዔሣው በዚህ ተስማማ (ዘፍ. 25፥32–33)። *ዔሣው ብኩርናውን ናቀ* (ዘፍ. 25፥34)። በዚህ ሁኔታ ዔሣው የእግዚአብሔርን በረከት አጣ (ቁ. 16)። ዋናው ኃጢአቱ ከእግዚአብሔር በረከት ይልቅ ምድራዊ ደስታ መፈለጉ ነበር ።

ዔሣው ከመቶ ብር ኖት ይልቅ፣ ጥቂት ከረሜላዎችን እንደሚፈልግ ሕፃን ዓይነት ነበር። ከእግዚአብሔር ነገሮች ይልቅ፣ ለዚህ ዓለም ነገሮች የምንጓጓ ከሆነ እኛም እንደ ዔሣው ነን። ምድራዊ ሀብትን ለማግኘት ሲሉ ሰማያዊ ርስታቸውን ያጡ ምን ያህል ናቸው? (ማቴ. 6፥19–20 እና ገለጻውን ይመልከቷል)።

ዔሣው በኩርናውን ካጣ በኋላ እንደገና ሊያገኘው ሞከረ፤ ሆኖም አልሆነለትም። በእኛም እንዲሁ ነው የሚሆነው። ሆን ብለን የእግዚአብሔርን ጸጋ ችላ የምንል ከሆነ፣ እንደ ዔሣው ሁሉ ሰማያዊ ርስታችንን እናጣለን (ዕብ. 10፥35 ይመልከቷል)።

17 ይስሐቅ ዔሣውን እንደባረከው በዘፍ. 27፥30–40 ተገልጾአል (ዕብ. 11፥20 እና ገለጻውን ይመልከቷል)። የእግዚአብሔርን በረከት ችላ በማለቱ ዔሣው ከልቡ ንስሐ አላደረገም። እርግጥ ነው ውሉ አድሮ ተጸጽቶአል፤ ስላጣው በረከትም ምርር ብሎ አልቅሶአል፤ ይሁን እንጂ፣ ስለ ኃጢአቱ አልነበረም ያለቀሰው። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ጸጋ ችላ ካለ ልቡ ይጠነከራል፤ ንስሐ የማድረግ ፈቃድም አይኖረውም (ዕብ. 3፥12–13)።

ሰማያዊት ኢየሩሳሌም (12፥18–29)

18–19 እዚህ ላይ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፣ እግዚአብሔር ሕጉን እንዴት ለአይሁዳውያን እንደሰጣቸው ይገልጻል። ከሙሴ ጋር ለመነጋገር እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ወረደ፤ ተራራው ይናጥ ነበር። ታላቅ ደመና ተራራውን ሸፈነው፤ *ጭጋግ ፣ ጨለማ ፣ ዐውሎ ነፋስ* ነበር (ቁ. 18)። ተራራው በጽኑ ተንቀጠቀጠ። እግዚአብሔር በተራራው ላይ ሲወርድ፣ *የመለከት ድምፅ* ተሰማ። እግዚአብሔርም በደመናው ውስጥ ሆኖ ተናገረ። አይሁዳውያንም ፈርተው ተንቀጠቀጡ (ዘጸ. 19፥16–19፤ 20፥18–21)።

20–21 እግዚአብሔር ተራራው ላይ በነበረበት ጊዜ፣ የሲናን ተራራ የሚነካ ሰውም ሆነ እንስሳ እንዲገደል አዘዘ። ከእግዚአብሔር መገኘት የተነሣ ተራራው ሁሉ በቅድስናው ተሸፍኖአል። ወደዚያ ቅድስና የሚቀርብ ሰውም ሆነ እንስሳ መገደል እስከሚኖርበት ድረስ ተራራው ላይ ያረፈው የእግዚአብሔር ቅድስና፣ አስፈሪና አስደንጋጭ ነበር። እንስሳው ራሱ እንኳ ከሩቅ ሆኖ በድንጋይ ይገደላል እንጂ በሰው እጅ አይነካም (ቁ. 20)። አይሁዳውያን እንዲህ ያለውን ትእዛዝ ሲሰሙና የእግዚአብሔርን መገኘት አስፈላጊነት ሲያዩ ሊቋቋሙት ከሚችሉት በላይ ሆነባቸው። ወደ እግዚአብሔር ቅድስና የሚቀርብ በሕይወት ሊኖር አይችልም (ዘጸ. 19፥12–13)። ከዘዳ. 9፥19 እንደምንመለከተው ሙሴ ራሱ እንኳ «እኔ ፈራሁ፤ ተንቀጠቀጥሁ» ብሏል (ቁ. 21)።

22 በአሮጌው ኪዳን ከእግዚአብሔር መገኘት ኃይል የተነሣ፣ ሰዎች ይፈሩ ነበር። በአዲሱ ኪዳን ግን ማንኛውም አማኝ ያለምንም ፍርሃት ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ ይችላል። የምንቀርበው አፍቃሪና መሐሪ ወደ ሆነው ሰማያዊ አባታችን ፊት ስለሆነ፣ እንደ እነዚያ አይሁዳውያን አንፈራም።

የጽዮን ተራራ፤ ንጉሥ ዳዊት የኢየሩሳሌምን ከተማ የመሠረተባት ቦታ ናት። *የጽዮን ተራራ* ማለትም ኢየሩሳሌም የአይሁድ ሃይማኖት ማዕከል ናት። የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ታላቁን የአይሁድ ቤተ መቅደስ የሠራውም እዚሁ ነበር። የአሮጌው ኪዳን ምድራዊ መቅደስ፣ የአዲሱ ኪዳን ሰማያዊ መቅደስ *ምሳሌ* እንደነበር ሁሉ (ዕብ. 9፥24)፤ ምድራዊቷ ኢየሩሳሌምም *የሰማያዊት ኢየሩሳሌም* ምሳሌ ነበረች።

«ሰማያዊት ኢየሩሳሌም» *የሕያው እግዚአብሔር ከተማ* ናት። ከመላእክቱ ጋር እግዚአብሔር የሚኖርባት ሰማያዊት መቅደስ ናት። አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ሲናፍቁ የኖሩት ይህችን *የተሻለች ከተማ* ነበር (ዕብ. 11፥16)።

23 እዚህ ላይ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም *የበኩር ልጆች ጉባዔ* ተብላለች። ኢየሱስ በኩር ነው፤ በእግዚአብሔር *መንግሥት* ኢየሱስ *የመጀመሪያ* ነው (ሮሜ 8፥29፤ ቆላ. 1፥15፤ ዕብ. 1፥6)። በእርሱ በማመናችን በመንፈሳዊ አነጋገር እኛም የበኩር ልጆች እንሆናለን። የእግዚአብሔርን *መንግሥት* የምንወርስ «የበኩር ልጆች» ነን። *በደስታ የተሰበሰቡት ጉባዔ* ማለትም የቤተክርስቲያን አባሎች ነን። *ስሞቻችን በሰማይ ተጽፈዋል* (ሉቃ. 10፥20፤ ራእ. 21፥27 ይመለከቷል)።

ፍጹምነትን ያገኙ የጻድቃን ነፍሳት የተባሉት በምዕራፍ 11 የአብዛኞቹ ስም የተጠቀሰው፣ የብሉይ ኪዳን እምነት አርበኞች ናቸው። እነርሱም *በደስታ ወደተሰበሰቡት ጉባዔ ይጨመራሉ*።

በዚህ ቁጥር የተጻፈውን መሠረት በማድረግ፣ አማኞች ሲሞቱ *መንፈሳቸው ፍጹምነትን* እንደሚያገኝና ወዲያውኑ መንግሥተ ሰማይ ማለትም «ሰማያዊት ኢየሩሳሌም» ይገባሉ በማለት ብዙዎች ያስባሉ (ሉቃ. 23፥42–43)። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ ደግሞ በአካላቸው ከሞት ይነሳሉ አዲስ የተዋጀ መንፈሳዊ አካልንም ይለብሳሉ (ሮሜ 8፥23)።

እግዚአብሔር *የሁሉም ፈራጅ* ነው። ጠላቶቹን ይበቀላል፤ ለሕዝቡ ግን ይፈርድላቸዋል። ሆኖም በራሱ ሕዝብ ላይም ይፈርዳል፤ ማንኛችንም ከእግዚአብሔር ፍርድ አናመልጥም። የምንታዘዝ ከሆነ የሚያስፈራን አይኖርም። ሆን ብለን የማንታዘዝ ከሆነ ግን ልንፈራ ይገባናል (ማቴ. 7፥21፤ ዕብ. 10፥30–31 ይመለከቷል)።

24 ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ስንገባ *የአዲስ ኪዳን መካከለኛ* የሆነውን ኢየሱስን እናገኛለን (ዕብ. 8፥6፤ 9፥15 እና ገለጻዎቹን ይመለከቷል)። ከፈሰሰው ደሙ የተነሣም፣ ኅሊናችን ነጽቶአል (ዕብ. 9፥14)። በዚህም ምክንያት ወደ ሰማያዊው መቅደስ እንገባለን፤ ወደ እግዚአብሔርም እንቀርባለን (ዕብ. 10፥19፤ 22)። ከአቤል ደም ይልቅ የኢየሱስ ደም *በተሻለ ሁኔታ ይናገራል*። *የአቤል ደም* ኃጢአተኛው ቃየልን እንዲበቀልለት ነበር የተናገረው (ዘፍ. 4፥8–10፤ ዕብ. 11፥4 ይመለከቷል)። የኢየሱስ ደም ግን እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንዲምራቸው ነው የሚናገረው። እግዚአብሔር ይቅር እንዲለንና ከእርሱ ጋር እንድንታረቅ ነው የሚናገረው። ለዚህ ነው ከአቤል ደም ይልቅ የኢየሱስ ደም *በተሻለ ሁኔታ ይናገራል* የተባለው።

25 *ያንን የሚናገረውን* ማለትም እግዚአብሔርን፣ *ችላ እንዳትሉ ተጠንቀቁ*። እግዚአብሔር ለአይሁድ *ከምድር* ተናገራቸው። ሊያናግራቸው በሲና ተራራ ላይ ወረደ (ቁ. 18–19 ይመለከቷል)። በመጨረሻ ግን አይሁድ እምቢ አሉት፤ ስለዚህም ተቀጡ።

ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሎአል። አሁን እንኳ *ከሰማይ* እያስጠነቀቀን ነው። አይሁዳውያን እግዚአብሔር ⁄ ከምድር የተናገራቸውን ባለመቀበላቸው ከተቀጡ፣ እኛ ደሞ ከሰማይ ለሚሰጠን ማስጠንቀቂያ እምቢ ብንል በፍጹም ከቅጣት ማምለጥ አንችልም (ዕብ. 3፥7–12፤10፥28–29 ይመለከቷል)።

26 እግዚአብሔር አይሁዳውያንን ከሲና ተራራ ሲናገራቸው *ተራራው* ተናውጦአል (ዘጸ. 19፥18)። በኋላም በብሉይ ኪዳን ነቢያት አማካይነት እግዚአብሔር ሲናገር «ምድርን ብቻ ሳይሆን ሰማይን ጭምር አናውጣለሁ» ብሏል (ኢሳ. 13፥13፤ ሐጌ 2፥6)። ትርጉሙም እንዲህ ነው፣ አንድ ቀን እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ያጠፋል፤ በስፍራቸውም *አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር* ይመሠርታል (ራእ. 21፥1)።

27 እግዚአብሔር *የሚናወጡ* ነገሮችን ማለትም *የተፈጠሩ ነገሮችን* ያስወግዳል። እነዚህ *የተፈጠሩ ነገሮች* ሰማይና ምድር ናቸው። እግዚአብሔር ያስወግዳቸዋል። ሰማይና ምድር ይወገዳሉ፤ ጨርሰው ይጠፋሉ (ማር. 13፥31)። የእግዚአብሔር *መንግሥት ሰማያዊት ኢየሩሳሌም* (ቁ. 22) ግን አትናወጥም፤ ለዘላለም ትኖራለች።

28–29 እኛ አማኞች *የማትናወጠው መንግሥት* (የእግዚአብሔር መንግሥት) ዜጎች ነን። ስለዚህም ስላደረገልን *ታላቅ ጸጋ* ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን እናመስግነው። ደስ *በሚሰኝበት ሁኔታም* ማለትም፤ *በአክብሮትና በፍርሃት* እናምልከው። እግዚአብሔር የሚወደን መሐሪና ሰማያዊ አባት ነው፤ ሆኖም *የሚያቃጥል እሳትም* ነው (ዘዳ. 4፥24፤ ኢሳ. 33፥14፤ 1ቆር. 3፥13–15፤ ዕብ. 10፥26–27፤ 2ጴጥ. 3፥10–13)። ሆን ብለው ችላ የሚሉት በአፍቃሪ አባትነቱ አያውቁትም፤ እነርሱ ውለው አድረው የሚያውቁት *የሚያቃጥል እሳት*፣ የፍርድና የቅጣት «እሳት» መሆኑን ነው። ስለዚህም ሰዎች ሁሉ *በአክብሮትና በፍርሃት* ወደ እግዚአብሔር መምጣት ይኖርባቸዋል፤ ለማዳን ብርቱ ነው፤ የዚያኑ ያህል ለመቅጣትም ብርቱ ነው።

ምዕራፍ 13

የማጠቃለያ ምክር (13፥1–17)

1 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «*እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ*» አላቸው (ዮሐ. 13፥34)። ይህ ፍቅር፣ ሁሉም ነገር መልካም ሲሆንና ሲስተካከል ብቻ ለሰዎች የምናቀርበው ሞቅ ያለ ሰላምታ አይደለም። *የወንድማማች ፍቅር ዋጋ* ያስከፍላል። ከላይ በተመለከትነው ትእዛዝ ኢየሱስ «*እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ*» የሚል አክሎበታል (ዮሐ. 13፥34)። ለመሆኑ እንዴት ነበር ኢየሱስ የወደደን? ሕይወቱን በመስጠት ነበር (1ዮሐ. 3፥16–17)። *የወንድማማችነት ፍቅር ይኑራችሁ*። በችግርና በመከራ ጊዜ እንኳ ቢሆን እርስ በርሳችን ያለን ፍቅር በየጊዜው ማደግ አለበት (ሮሜ 12፥10፤ 1ተሰ. 4፥9–10 ይመለከቷል)። በዚህም በችግር ውስጥ ጸንተን መቆም እንችላለን።

ዕብራውያኑ በስደት ውስጥ ነበሩ። ጸሐፊው ደግሞ በችግሩ ውስጥ ጸንተው መቆም የሚችሉት እርስ በርሳቸው ሲዋደዱ ብቻ እንደሆነ ይነግራቸዋል።

2 እዚህ ላይ ጸሐፊው፣ አብርሃም ሦስት መላእክት በእንግድነት ተቀብሎ እንዳስተናገደ የሚናገር አንድ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ያነሳል፤ ከሦስቱም አንዱ ራሱ እግዚአብሔር ነበረ (ዘፍ. 18፥1–10)። ሁለቱ መላእክት ወደ አብርሃም ወንድም ልጅ ወደ ሎጥ ሄደው ከጥፋት አዳኑት (ዘፍ. 19፥1–16)። ምናልባት መልአክ ወደ ቤታችን ባይመጣም፣ እንግዶች ግን ሊመጡ ይችላሉ፤ እኛም ልንመልሳቸው አይገባንም። ወደ ሎጥ ቤት የሄዱት መላእክት እንዳደረጉት ሁሉ፣ አንድ ቀን እነዚህ እንግዶች የታላቅ በረከት ምክንያት ሊሆኑልን ይችላሉ።

ይሁን እንጂ፣ እንግዶችን የምናስ ተናግደው በረከትን ለመቀበል ሳይሆን፣ በረከትን ለመስጠት መሆን አለበት! እንግዶችን ማስተናገድ በጣም ጠቃሚ ክርስቲያናዊ ተግባር ነው (ማቴ. 25፥34–40፤ ሮሜ 12፥13 1ጴጥ. 4፥9)።

3 በዚህ ቁጥር ላይ ጸሐፊው በጣም ጠቃሚ መመሪያ ይሰጠናል። ይኸውም፣ በችግር ውስጥ ያሉትን እንደሚገባን መውደድ እንድንችል፣ ራሳችንን እነርሱ ስፍራ ማድረግ አለብን፤ እነርሱ ላይ የደረሰው እኛም ላይ እንደ ደረሰ ማሰብ አለብን የሚል ነው። እንደዚያ ካደረግን በተሻለ ሁኔታ እንወዳቸዋለን፣ እንራራላቸዋለንም። ስለ እስረኞች ስናስብ፣ ልክ እኛ ራሳችንም አብረናቸው እንደታሰርን አድርገን እናስብ። መጉላላት ወይም ውርደት ወይም የተለያዩ ጉዳት ስለደረሰባቸው ሰዎች ስናስብ፣ እነዚህ ነገሮች የደረሱት እነርሱ ላይ ሳይሆን እኛ ላይም እንደሆነ እናስብ።

እናንተም እንደ እነርሱ መከራ የምትቀበሉ ያህል ሆናችሁ መከራ የሚቀበሉትን አስቡ[24] ይላል ጸሐፊው። እንደ እነርሱ ሁሉ እኛም አካል አለን፤ እኛን እንደሚሰማን ሁሉ

---

[24] «እናንተም እንደነርሱ መከራ የምትቀበሉ ያህል ሆናችሁ» በሚለው ምትክ አንዳንድ ትርጉሞች «እናንተም በስጋ መከራቸውን የምትካፈሉ ያህል» የሚል፤ ከግሪኩ በኩረ ቃል ጋር አቻነት ያለው ሃሳብ ይጠቀማሉ። ይሁን እንጂ የትርጉም ልዩነት የለውም።

እነርሱንም ደስታና ሀዘን ይሰማቸዋል። ነገ ደግሞ እኛ ራሳችን ችግር ላይ መውደቃችን የታወቀ ነው። በዚያ ጊዜ የእነርሱ ፍቅርና ርኅራኄ ያሻናል! (ዕብ. 10፥33–34 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

4 ጋብቻን የመሠረተው እግዚአብሔር ራሱ ነው (ዘፍ. 2፥24)። ስለዚህም ወንድና ሴት በጋብቻ መጣመራቸው የተከበረና እግዚአ ብሔርንም ደስ የሚያሰኝ ነው። ጋብቻ የተከበረና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ ደግሞ ከትዳር ጓደኛ ጋር የሚፈጸመው ወሲብ ደግሞ የተከበረ ነው፤ ምክንያቱም ወሲብ የጋብቻ አስፈላጊ ክፍል ነው።

አመንዝራ ማለት ከጋብቻ ውጪ ዝሙት የሚፈጽም ሰው ነው። እዚህ ላይ *ርኩሰት* ሲል ያገቡም ሆነ ያላገቡ የሚፈጽሙት ሕጋዊ ያልሆነ ወሲብን ማለቱ ነው።

የመጀመሪያ የትዳር ጓደኛ በሕይወት እስካለ ድረስ ሌላ ሴት ወይም ወንድ ማግባት አመንዝራነት ነው። ሌላ ማግባት የሚቻለው፥ አንደኛው ወገን አመንዝራ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። (ማቴ. 5፥32፤ ማር. 10፥11–12 እና ገለጻውን ይመለከቷል)። ባለትዳር ሰው ወደ ሴተኛ አዳሪ ሄዶ ወሲብ ከፈጸመ፥ እርሱም አመንዝራ ሆኖአል። ሴሰኞችና አመንዝሮችን ሁሉ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። በንስሐ የማይመለሱ መንግሥተ ሰማይ አይገቡም (1ቆር. 6፥9–10፤ 1ተሰ. 4፥3–6)።

5 እግዚአብሔር ምንም ጠቃሚ ነገር እንዲጎድለን አይፈልግም። የሚያስፈልገንንም ሊሰጠን ዝግጁ ነው፤ ብዙውን ጊዜ ግን ከሚያስፈልገን በላይ አይሰጠንም። ከሚያስፈልገን በላይ መመኘት ስግብግብነት ነው፤ ስግብግብ ሰው ደግሞ ሀብትና ንብረትን በእግዚአብሔር ስፍራ አስቀምጦአልና ጣዖት አምላኪ ነው (ኤፌ. 5፥5፤ ቆላ. 3፥5 ይመለከቷል)። እንዲህ ያለው ሰው የሚያመልከው እግዚአብሔርን ሳይሆን ገንዘቡን ነው።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ፥ *የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው፤ አንዳንድ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት በመመኘት ከእምነት ርቀዋል፤ ልባቸውንም በሐዘን ጦር ወግተዋል።* በማለት ጽፎለታል (1ጢሞ. 6፥10)። ገንዘብን የሚወድድ ሰው ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር እየቀነሰ፥ ለዚህ ዓለም ንብረት ያለው ፍቅር ደግሞ ይበልጥ እየጨመረ ይሄዳል። ማንም ቢሆን፥ እግዚአብሔርንና ገንዘብን እኩል መውደድ አይችልም (ማቴ. 6፥24 እና እና ገለጻውን ይመለከቷል)። ይህም ብቻ አይደለም፤ ገንዘብን የሚወዱ ሰዎች ራሳቸውን *በብዙ ሐዘን ይወጋሉ። ሐዘን የሚያመጡትም ጭንቀትና ሥጋት ናቸው።* ገንዘብ ወዳድ ሰው ሁልጊዜ ገንዘቤ ቢጠፋብኝስ? በማለት ይፈራል። ሰላም የለውም፤ ደስታም የለውም። ሁልጊዜ ለመጨመር ይፈልጋል እንጂ ባለው አይረካም። እኛ ግን እንደዚህ መሆን የለብንም። ከዚህ ይልቅ ባለን መርካት አለብን (ፊል. 4፥11–12)። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ *በእርግጥ «ያለኝ ይበቃኛል» የሚል ሰው ፍጹም መንፈሳዊነትን ስለሚያተርፍበት ሃይማኖት የሀብት ምንጭ ነው። ምክንያቱም ወደዚህ ዓለም ምንም ይዘን አልመጣንም፤ ከዚህም ዓለም ይዘነው የምንሄድ ምንም ነገር የለም። የምንበላውንና የምንለብሰውን ካገኘን ይበቃናል* (1ጢሞ. 6፥6–8)።

ይህን በተመለከተ ኢየሱስ ራሱ ጠቃሚ ትምህርት ሰጥቶአል፥ «. . . *ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? እያላችሁ አትጨነቁ . . . አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና የእግዚአብሔርን ጽድቅ ፈልጉ፤ ሌላው የቀረው ነገር ሁሉ ይጨመርላችኋል*» (ማቴ. 6፥31–33) አለ።

እዚህ ላይ ጸሐፊው ከዘዳ. 31፥6 ይጠቅሳል። እግዚአብሔር አይተወንም ከቶም አይጥለንም። ታዲያ፥ ለምን እንሰጋለን?

6 እዚህ ላይ ደግሞ ጸሐፊው ከመዝ. 118፥6 ይጠቅሳል። አማኞች ሁሉን በሚችል አምላክ ጥበቃ ውስጥ ናቸው። ስለዚህ መፍራት የለብንም።

7 በዚህ ቁጥር ላይ ጽሐፊው ስለቀድሞ መሪዎች ይናገራል። በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ካከበርናቸው፥ ከሞቱ በኋላም ልናከብራቸው ይገባል። የእግዚአብሔርን ቃል ሰጥተውናል፤ መልካም አርዓያም ሆነውልናል።

8 የድሮ መሪዎቻችን አልፈዋል፤ ኢየሱስ ግን ዛሬም ሕያው ነው (መዝ. 102፥27፤ ዕብ. 1፥12)። ኢየሱስ ዘላለማዊ ስለሆነ ክህነቱ ዘላለማዊና የማይለወጥ ነው (ዕብ. 7፥24)። ኢየሱስ *ሊማልድልን ለዘላለም ይኖራል* (ዕብ. 7፥25)።

ኢየሱስ እንዲህ አለ «*የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ፤ ሕያውም ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ ነገር ግን እነሆ ለዘላለም ሕያው ነኝ፤ በሞትና በሲኦል ላይ ሥልጣን አለኝ*» (ራእይ 1፥17–18)።

9 ልዩ መንፈሳዊ ኃይልን ለማግኘት ከተፈለገ፥ አንዳንድ *የምግብ ሥርዓቶችን* መጠበቅ ይገባል በማለት፥ አንዳንድ ሐሰተኛ መምህራን እነዚህን ዕብራውያን ያስተማሯቸው ነበር። እዚህ ላይ ግን የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የሰው ልብ የሚበረታው በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ፥ (ሮሜ 14፥17፤ 1ቆር. 8፥8) የምግብ ሥርዓቶችን በመጠበቅ እንዳልሆነ ይነግራቸዋል።

10 *መሠውያው* ላይ የተሰዋውን *ሥጋ* መብላት፥ መንፈሳዊ ጠቀሜታ እንዳለው አንዳንድ አይሁዳውያን ያስተምሩ ነበር። እኛ ክርስቲያኖች ያለን ግን የተለየ *መሠውያ* ነው። መሠዊያችን የእንስሳት *ሥጋ* የተሰዋበት ሳይሆን፥ የክርስቶስ አካል የተሠዋበት *መሠውያ* ነው። *መሠውያችን* የአዲሱ ኪዳን መንፈሳዊ *መሠዊያ* ሲሆን፥ *በድንኳኒቱ ውስጥ (አሮጌው ኪዳን) የሚያገለግሉ ካህናት በመሠውያው ላይ ካለው ምግብ ወስደው መብላት አይፈቀድላቸውም።*[25] ከክርስቶስ *መሠውያው* ላይ *መመገብ* ብቻ ነው መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያለው፤ ከክርስቶስ *መሠውያ* ስንበላ ራሱ ክርስቶስን *መካፈላችን* ነው (ዮሐ. 6፥53–56)።

11 ኢየሱስ ክርስቶስ *የኃጢአት መሥዋዕት* ነው። የኃጢአት ይቅርታን የምናገኝበት *መሥዋዕት* ነው (ሮሜ 3፥23–25)። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ ለሕዝቡ ኃጢአት *የኃጢአት መሥዋዕት* ያቀርብ ነበር። ካህናቱ የሌሎችን *መሥዋቶች ሥጋ* ሁሉ ይበላሉ፤ *የኃጢአትን መሥዋዕት ሥጋ* እንዲበሉ ግን አይፈቀድላቸውም።[26] ለኃጢአት *መሥዋት* እንዲሆን የሚሠዋው እንስሳ *ሥጋ ከሰፈሩ ውጪ ይቃጠላል* (ዘሌ. 16፥27)።

12 ኢየሱስ የሞተውም ከሰፈሩ ውጪ ማለትም ከኢየሩሳሌም *ከተማ በር ውጪ* ነበር። ኢየሱስ ስለተሰቀለበት ቦታ ዮሐንስ ሲናገር፥ *ኢየሱስ የተሰቀለበት ሥፍራ ለከተማ ቅርብ ነበር* ይላል (ዮሐ. 19፥20)። በመስቀል ላይ አካሉን *መሥዋዕት* አድርጎ በማቅረቡ ማለትም *በገዛ ራሱ ደም* ኢየሱስ አማኞችን ቀደሳቸው (ዕብ. 10፥10፤ 14 ይመለከቷል)።

13 *እኛም ከሰፈር ወጥተን ወደ እርሱ እንሂድ።* ለአይሁዳውያን ክርስቲያኖች «ከሰፈር ወጥተን እንሂድ» ማለት ከኢየሩሳሌም መውጣት፥ የድሮ ሃይማኖታቸውን፥ ንብረታቸውን፥ ቀስትናቸውንና ሁሉንም ነገር መተው ማለት ነው። በተመሳሳይ መንገድም ክርስቶስን ለመከተል የሚፈልጉ ሁሉ *ከሰፈር ወጥተው ወደ እርሱ መሄድ* ማለትም የድሮ ሃይማኖታቸውን፥ የድሮ ባሕላቸውንና ሕይወታቸውን መተው ይኖርባቸዋል። ሙሴ *የግብጽን ሀብት ተወ፤ ስለመሲሕ መዋረድን* መረጠ (ዕብ. 11፥26)። ኢየሱስም «*ሊከተለኝ የሚወድድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ*» (ማር. 8፥34)፤ «*የገዛ ራሱን መስቀል ተሸክሞ ማይከተለኝ ሰው የእኔ ሊሆን አይገባውም*» (ማቴ. 10፥37–38) ብሏል።

በድሮ ዘመን መስቀል ምን ያህል አሳፋሪ እንደ ነበር ያስታውሷል። የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ኢየሱስ ግን መስቀሉን ተሸክሞ *ከሰፈር ውጪ* ሄደ (ዮሐ. 19፥17)። ስለዚህ *እኛም ከሰፈር ወጥተን ወደ እርሱ እንሂድ* የውርደቱም ተካፋዮች እንሁን።

---

25 ለቁጥር 11 የተሰጠውን ማብራሪያና የግርጌ ማስታወሻውን ይመለከቷል።

26 የአሮጌው ኪዳን አገልጋዮች፥ በመሠውያው ላይ ካለው ምግብ መብላት የሌለባቸው በዚህ ምክንያት ነው (ቁ. 10)። ክርስቶስ የኃጢአት መሥዋዕት ነው፤ የኃጢአት መሥዋዕት ደግሞ እንዳይበላ ተከልክሎአል።

14 ማንም ቢሆን «ሰፈሩን» ተወልዶ ያደገበትን ከተማ፣ የቆየ ባሕሉንና ሕይወቱን መተው አይፈልግም። ይሁን እንጂ፣ ምንም ስለማይጠቅሙን በእነዚህ አሮጌ ነገሮች መታመን የለብንም። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ያልፋሉ፤ ጸንታ የምትኖር ከተማ በዚህ ምድር የለችንም። የዚህ አባባል እውነተኛነትን ሙሉ ሳያድር አይሁዳውያን አረጋግጠዋል። ኢየሱስ ከሞተ አርባ ዓመት በኋላ የኢየሩሳሌም ከተማ ሙሉ በሙሉ በሮም ሠራዊት ተደምስሳለች።

እኛ በክርስቶስ ለምንታመን ግን ምድራዊት ከተማ አታስፈልገንም፤ ከዚህ ይልቅ ሰማያዊት ከተማ፣ ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ማለትም የማትናወጠውን መንግሥት እንጠባበቃለን (ዕብ. 11፥10፤ 16፤ 12፥22፤ 28 ይመለከቷል)።

15 የአሮጌው ኪዳን የእንስሳት መሥዋዕት ተወግዶአል። የክርስቶስ መሥዋዕት ብቻ ነው፤ ለዘላለም ይጠቅማል። ይሁን እንጂ፣ እኛ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር የምናቀርበው አዲስ ዓይነት መሥዋዕት አለን፤ ይኸውም መንፈሳዊ መሥዋዕት ነው። ስለዚህ መሥዋዕት ጴጥሮስ፣ ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ቅዱሳን ካህናት ትሆናላችሁ አለ (1ጴጥ. 2፥5)።

እነዚህ መንፈሳዊ መሥዋዕቶች ምንድን ናቸው? ከእነዚህ አንዱ በዚሁ ቁጥር ተጠቅሶአል፤ እርሱም የምስጋና መሥዋዕት ነው። ምስጋናና ውዳሴ ሁልጊዜም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ «መሥዋዕት» ናቸው።

16 በከንፈሮቻችን መሥዋዕት ማቅረብ ብቻ ግን በቂ አይደለም። መልካም ሥራና ፍቅርን በማድረግም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ ይገባናል። እውነተኛ ሃይማኖት መልካም ሥራን በማድረግና ሌሎችንም በመርዳት ጭምር እንጂ፣ የእንስሳትን መሥዋዕት በማቅረብ አይወሰንም (ያዕ. 1፥27 ይመለከቷል)። መሥዋዕቶቻችን ፍቅር፣ ምሕረት፣ ታማኝነት ናቸው። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን እናቀርባለን (ሮሜ. 12፥1)። ይህ ነው ይበልጥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው መሥዋዕት፤ ምክንያቱም ሰውነታችንን መሥዋዕት አድርገን ካቀረብን ሁሉንም አቅርበናል ማለት ነው።

17 በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች ለመሪዎቻቸው መታዘዝ አይፈልጉም። እነዚህ ሰዎች መሪዎቻቸውን አያከብሩም። ብዙ ጊዜ ደግሞ ወጣቶች ታላላቆቻቸውን ይንቅፋሉ። እንዲህ ያለው ነገር ግን በክርስቲያኖች መካከል መታየት የለበትም። እርግጥ ነው መሪዎቻችን የግላቸው ስሕተትና ደካማ ጎን ይኖራቸዋል፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ የእኛ ጉዳይ አይደለም። የእኛ ድርሻ መታዘዝና መሪዎቻችንን ማክበር ነው (1ተሰ. 5፥12–13 እና ገለጻውን ይመለከቷል)።

በበላይነት እንዲመሩን እግዚአብሔር መሪዎችን ሾሞአል። በእረኝነታቸው እንዴት እንደተጠቀሙበት አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣሉ። የማንታዘዝና የምናምጽባቸው ከሆነ ግን ስለ እኛ ለክርስቶስ ምላሽ ይሰጣሉ። የማንታዘዝና የምናምጽባቸው ከሆነ ግን ስለእኛ ለክርስቶስ ምላሽ በሚያቀርቡበት ጊዜ ታላቅ ሀዘን ይሰማቸዋል። ባለመታዘዛችን ሀዘን የሚሰማቸው ከሆነ ደግሞ በተራችን እኛም ለክርስቶስ ምላሽ ስንሰጥ ታላቅ ሀዘንና የልብ ስብራት ይደርስብናል። በመሪዎቻቸው የሚያምጹ ሰዎች በራሳቸው ላይ ታላቅ መንፈሳዊ ጉዳት ያመጣሉ።[27]

የመጨረሻ ጸሎትና ሰላምታ (13፥18–25)

18–19 ጸልዩልን። ይበልጥ ለመሪዎቻችን በጸለይን መጠን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችንም ይበልጥ ይጠቅሙናል (ሮሜ 15፥30–32፤ 2ቆሮ. 1፥12 ይመለከቷል)።

20 በአዲስ ኪዳን የተጻፉትን ጸሎቶች በማጥናት እንዴት ለግላችንና ለሌሎች መጸለይ እንዳለብን እንማራለን። እዚህ ላይ ጸሐፊው ወደ ሰላም አምላክ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ከአማኞች ጋር ሰላምን ወዳደረገ አምላክ ይጸልያል። ይኸው አምላክ በዘላለማዊ ኪዳን ደም ክርስቶስን ከሞት አስነስቶታል። ይህም ማለት ደሙን በማፍሰስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትና ደስ የሚያሰኘውን መሥዋእት አቅርቦአል፤ ስለዚህም እግዚአብሔር በዘላለማዊው ኪዳን ማለትም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለተደረገው ኪዳን ካህን እንዲሆን ክርስቶስን ከሞት አስነሳው ማለት ነው (ሕዝ. 37፥26)።

ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ብቻ ሳይሆን፣ ታላቅ እረኛችንም ነው፤ እኛም በጎቹ ነን።

21 እዚህ ላይ ጸሐፊው ፈቃዱን ለመፈጸም እንድትበቁ በመልካም ነገር ሁሉ ያስታጥቃችሁ በማለት ይጸልይላቸዋል። «መልካም ነገር ሁሉ» የሚለው የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ የእግዚአብሔርን ኃይል፣ የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ ሁሉ ያጠቃልላል። ከዚህ በላይ የሚያስፈልገን የለም።

አንድ ነገር ግን ይቀራል። ምንም እንኳ ፈቃዱን ለመፈጸም የሚያበቃንን ሁሉ ብንቀበልም፣ እርሱም ደስ የሚያሰኘውን በእኛ ማድረግ አለበት (ፊል. 2፥13 ይመለከቷል)። ብቻችንን ምንም ማድረግ አንችልም (ዮሐ. 15፥5) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት እግዚአብሔር በውስጣችን ይሠራል። ስለዚህ በእኛ ውስጥ በሚሠራው ኃይል አማካይነት ከምንለምነውና ከምናስበው እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው አምላክ ለእርሱ በቤተክርስቲያንና በኢየሱስ ክርስቶስ በዘመናት ሁሉ ለዘላለም ክብር ይሁን (ኤፌ. 5፥20–21)።

22–25 ጢሞቴዎስ (ቁ. 23) ጳውሎስ ሁለቱን የአዲስ ኪዳን መልእክቶቹን የጻፈለት የጳውሎስ ባልደረባ ነው። ጢሞቴዎስ እስር ቤት እንደነበር የሚያመለክት የአዲስ ኪዳን ክፍል ይህ ብቻ ነው።

ከኢጣልያ የመጡት[28] በቁ. 24 ተጠቅሰዋል። እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ አልታወቁም፤ ይህ መልእክት ሲጻፍ በኢጣልያ ይሁኑ ወይም ከዚያ ውጪ አልታወቀም። የምናውቀው ቢኖር ለዕብራውያን ክርስቲያኖች ሰላምታ የላኩ ኢጣልያውያን ወንድሞች መሆናቸውን ብቻ ነው።

---

27 ሰዎች ሕጋዊ መሪዎቻቸውን ሲቃወሙ የሚደርስባቸው ቅጣት በዘኁ. 16 ተገልጾአል።

28 ኢጣልያ የሮም ዋና ከተማና በጣም ወሳኝ አውሮፓዊት አገር ናት። አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን ሮም፣ የሮማውያን ግዛት አጼ ማዕከል ነበረች።

የያዕቆብ መልእክት

መግቢያ

አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይህ መልእክት በኢየሱስ ወንድም በያዕቆብ እንደተጻፈ ያምናሉ (ገላትያ 1፥9)።

ያዕቆብ በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስቲያን መሪ ነበር። አያሌ ሊቃውንት ይህ መልእክት ከ50 ዓ.ም. በፊት እንደ ተጻፈ ያምናሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ ከቀደምት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ነው። ይህ መጽሐፍ ከ62 ዓ.ም. በኋላ ሊጻፍ አይችልም፤ ምክንያቱም በዚህ ዓመት ያዕቆብ ሰማዕት ሆኖ ነበር።

ያዕቆብ ይህን መልእክት የጻፈው ክርስቲያኖችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር ግዴታዎች ምን እንደሆኑ ለማስተማር ነው። በያዕቆብ ዘመን አያሌ ክርስቲያኖች መልካም ሥራን መሥራት አቁመው ነበር። «እኛ በሥራ ሳይሆን በእምነት ስለዳንን መልካም ሥራ መሥራት አያስፈልገንም» ይሉ ነበር። እነዚህ ክርስቲያኖች በእምነት ብቻ መዳናቸውን መናገራቸው ትክክል ነበር። ነገር ግን መልካም ሥራ መሥራት አያስፈልገንም ማለታቸው በጣም ስህተት ነበር። ያዕቆብ ይህን ስህተት ለማስተካከል ሲል ይህን መልእክት ጽፎአል።

አስተዋጽኦ

ሀ. ሁለት ዓይነት ፈተናዎች (1፥1–18)

1. የእምነት መፈተን (1፥1–11)
2. የፈተና መንስኤ (1፥12–18)

ለ. አጠቃላይ ትምህርቶች (1፥19–3፥18)

1. ቃሉን በተግባር መተርጎም (1፥19–27)
2. አድልዎ አለማድረግ (2፥1–13)
3. እምነትና ሥራ (2፥14–26)
4. አንደበትን መቆጣጠር (3፥1–12)
5. ሁለት ዐይነት ጥበብ (3፥13–18)

ሐ. ልዩ ልዩ ምክሮች (4፥1–5፥20)

1. የዓለማዊነት ዝንባሌ (4፥1–17)
2. ከፉው ሀብታም (5፥1–6)
3. ትዕግሥት (5፥7–12)
4. የእምነት ጸሎት (5፥13–20)

ምዕራፍ 1

እምነትና ጥበብ 1፥1–8

1 *ያዕቆብ ራሱን «የእግዚአብሔርና የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ»* በማለት ይጠራል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ዋና መሪዎችን ጨምሮ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው (ሮሜ 1፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቷል)። አንድ አገልጋይ በጌታው ላይ ሙሉ በሙሉ በመደገፍና በሁሉ ነገር ታዛዥ በመሆን ይኖራል። እኛም እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች መኖር ይገባናል። ምንም ያህል ሥልጣን ቢኖረን አገልጋዮች ነን። የተሰጠን ሥልጣን ሁሉ የእግዚአብሔር ነውና።

የእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን *«የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም»* አገልጋዮች ነን። ያዕቆብ የኢየሱስን ሙሉ ማዕረግ በዚህ ቦታ እንደጻፈ አስተውል። ኢየሱስ የሚለው ስሙ ሰው መሆኑን፤ በምድር ላይ መኖሩን፤ ማስተማሩንና ታምራት ማድረጉን፤ መሞቱንና ከሞት መነሣቱን የሚያሳይ ስም ነው። «ክርስቶስ» የሚለው ቃል ትርጉሙ «የተቀባ» ማለት ነው (መዝ. 2፥2፤ የሐዋ. 4፥26)። በዕብራይስጥ «የተቀባ» ለሚለው ቃል «መሲሕ» የሚለው ቃል አቻ ነው (ዮሐ 4፥25)። ክርስቶስ የእኛ አዳኝና እኛን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ መካከለኛ ለመሆን «ተቀባ»። የኢየሱስ ሦስተኛው የማዕረግ ስሙ «ጌታ» ነው። ይህም በግሪክ ቋንቋ አምላክ ማለት ነው። ይህ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስም ነው። ስለዚህ ከዚህ የምንረዳው ኢየሱስ ሰውም አምላክ መሆኑን ነው። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል እውነተኛ ሊሆን የቻለው በዚህ ምክንያት ነው።

ያዕቆብ ይህን መልእክት የፃፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች ማለትም በክርስቶስ ላመኑ አይሁዶች ነው። እነዚህ አማኞች በማያምኑ አይሁዶችና በሮማውያን በተነሣባቸው ስደት ምክንያት በየአገሩ የተበታተኑ ነበሩ።

ያዕቆብ እነዚህን አማኞች *«ዐሥራ ሁለቱ ነገዶች»* በማለት ይጠራቸዋል። የአይሁድ ሕዝብ የሆነውን የያዕቆብ *ዐሥራ ሁለቱ* ልጆች ነገዶች ማለት ነው። እነዚህ *ዐሥራ* ሁለት ነገዶች የአብርሃም የልጅ ልጅ ከሆነው ከያዕቆብ ወንዶች ልጆች የመጡ ናቸው። ሆኖም ያዕቆብ ይህን መልእክት የጻፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን በየስፍራው ላሉ አማኞች በሙሉ ነው። ስለዚህ የአይሁድ ክርስቲያኖች ብንሆን ወይም ከአሕዛብ (ከአረማዊነት) የመጡ ክርስቲያኖች ይህ መልእክት ለእኛ ተጽፎአል።

2 በዚህ ክፍል የተጠቀሰው *ፈተና* ስለ ክርስቶስ የምንቀበለው መከራና ስደትን ያመለክታል። ያዕቆብ በዚህ ስፍራ የሚናገረው መከራ በራሳችን ስህተትና ኀጢአት የሚመጣውን አይደለም።

ያዕቆብ ፈተና በራሱ ደስታ ያስገኛል አላለም። ነገር ግን እንደ ደስታ «ቍጠሩት» ይላል። ፈተናን እንደ ደስታ የምንቆጥረው ለምንድን ነው? ምክንያቱ እንዲህ ካለው ፈተና ብዙ መንፈሳዊ ጥቅሞችን እናገኛለን (ቁጥር 3–4)። የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ፈተናን መቋቋም ይችላሉ፤ ክርስቲያኖች ብቻ ግን በፈተና ደስ ሊሰኙ ይችላሉ።

3 በዚህ ቦታ ያዕቆብ ይህን ፈተና የእምነት *መፈተን* ብሎ ይጠራዋል። እነዚህ ፈተናዎች ምን ጥቅም ያስገኙልናል? እንዲህ ያሉ ፈተናዎች በውስጣችን *«መጽናትን»* ይፈጥሩልናል። እምነታችንን ለመፈተንና ለማጠንከር እግዚአብሔር ፈተናዎችን ወደ ሕይወታችን ያመጣል (1ጴጥ 1፥6–7)። መጽናት ማለት በእምነት መቆምና መጠንከር ወይም መበርታት ማለት ነው። ብርቱና ጽኑ መሆን እንጂ እንደተመታ ውሻ የሚያላዝንና የሚያለቅስ መሆን አይደለም። አንድ ሰው በፈተና ውስጥ ሲያልፍ መንፈስ ጠንካራ ሰው ይሆናል። ብርታቱ በራሱ ሳይሆን በእምነት ከክርስቶስ የሚቀበለው ነው።

«ለመጽናት» ሌላው ቃል ትዕግሥት ነው። ትዕግሥት ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አንዱ ነው (ገላ 5፥22)። እንዲህ ያለው መንፈሳዊ ትዕግሥት ወይም ጽናት ለእኛ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም መዳናችን ከዚህ ጋር የተያያዘ ነውና። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «እስከ መጨረሻ በትዕግሥት የሚጸና ግን ይድናል» (ማር 13፥13፤ ሉቃ 21፥19)።

እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን ፈተና እንዲመጣ የሚፈቅድበት ሁለተኛው ምክንያት እኛን ለመቅጣት ነው። ከእግዚአብሔር መንገድ ርቀን ወይም እንደ ፈቃዱ መሄድ ትተን ይሆናል። እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ፈተናዎች አማካይነት ወደ ትክክለኛ መንገድ እንድንመጣ ያደርጋል። እንዲህ ያለ ቅጣት በሚመጣበት ጊዜ ተስፋ መቁረጥ አይገባንም (ዕብ 12፥5–6)። ነገር ግን እነዚህ ፈተናዎች ለእኛ ጥቅም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የመጡ መሆናቸውን በማወቅ በደስታ ልንቀበል ይገባናል።

4 *የመጽናት ፍሬ ፍጹም መሆን ነው።* ፈተናዎች ወደ እኛ የሚመጡት *ፍጹምና ሙሉ* እንድንሆን ነው። ፍጹም የሆነ ክርስቲያን ትዕግሥተኛና ጽኑ ነው። ፍጹም የሆነ ክርስቲያን ባሕርይ ሙሉ ስለሆነ ምንም አይጎድለውም። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወቱ የሚታይ ነው፤ እንዲህ ያለ ሰው እንደጎመራ ፍሬ ነው። ፍሬ ሁለመናው በአንድ ጊዜ አይበስልም። ፀሐይና ዝናብን ሲያገኝ በሁሉም ጎኑ ይበስላል። የክርስቲያኖችም ሕይወት እንደዚህ ነው።

5 ሁሉም ክርስቲያኖች ወደ ፍጽምና ያለማቋረጥ ያድጋሉ። እያንዳንዳችን የሚጎድሉን ነገሮች አሉ። ብዙውን ጊዜ የሚጎድለን *ጥበብ* ነው። በዚህ ቍጥር ላይ ትልቅ ተስፋ ተገብቶልናል፤ ከእኛ ማንም ጥበብ ቢጎድለው *እግዚአብሔርን ይለምን፤ እግዚአብሔርም ይሰጠዋል*። የሚያስፈልገንን ጥበብ ሁሉ እንቀበላለን፤ እግዚአብሔር ስጦታዎቹን *በልግሥና* ይሰጣልና። ጥበብ ስለ ጎደለን እግዚአብሔር በእኛ ዘንድ ስህተትን አይፈልግም፤ ደግሞም ለዚህ ሲል አይገሥጸንም። እርሱ የሚወደን ሰማያዊ አባታችን ስለሆነ ያለ ፍርሃት ወደ እርሱ ልንቀርብ እንችላለን።

ጥበብ ከዕውቀት የተለየ ነው። ዕውቀት በራስ ጥረት ይገኛል፤ በትምህርት ቤት በመማርም ይገበያል። እውነተኛ ጥበብ ግን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው[1]። ጥበብ ከዕውቀት ይበልጣል፤ ምክንያቱም ጥበብ ዕውቀትን መጠቀም የሚያስችል ስጦታን ስለሚያጠቃልል ነው። ዕውቀት በጥበብ አማካይነት በተግባር ላይ ካልዋለ እርባና የለውም።

6–8 ከእግዚአብሔር አንድን ነገር ለመቀበል ከፈለግን፤ በእምነት እርሱን ልንጠይቀው ይገባናል። ያለ እምነት ብንጠይቀው እግዚአብሔር የጠየቅነውን አይሰጠንም። ይህ ሕግ ለጥበብ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ልመናዎቻችን የሚሠራ ነው።

የሚጠራጠር ሰው *ሁለት ሐሳብ* ያለው ሰው ነው (ቍጥር 8)። በአንድ ልብ የጠየቀውን የሚያገኝ ይመስለዋል፤ በሌላኛው ደግሞ ልመናውን የማያገኝ መስሎት ይጠራጠራል። እንዲህ ያለ ሰው *የሚያወላውል* ያልጸና ነው፤ በነፋስ እየተገፋ የሚናወጥ ባሕርን ይመስላል።

ደሃውና ሀብታሙ (1፥9–11)

9 *በኑሮው ዝቅተኛ* የተባለው ወንድም በባርነት ሥር ያለ፤ አገልጋይ፤ እስረኛ፤ የተናቀ ሰው ወይም በአንድ ችግር ውስጥ የወደቀ አማኝ ነው። እንዲህ ያለው ሰው በምድር ላይ ያለው ስፍራ ዝቅ ያለና የተዋረደ ነው። ነገር ግን በእምነቱ መንፈሳዊ ቦታው *ከፍ ስለሚያደርገው* በዚህ ደስ ሊለውና ሊመካ ይችላል[2]። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅና ከክርስቶስ ጋር ወራሽ ነው (ሮሜ 8፥14፤ 16–17)። ዓለም የእግዚአብሔር መንግሥት ተቃራኒ ነች። በዓለም ውስጥ ዝቅተኛ ስፍራ የተሰጣቸው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ይከብራሉ (ማቴ 5፥3–5፤23፥11–12፤ ማር 10፥43–44)።

10–11 *በኑሮው ከፍ ያለው* የተባለው በዚህ ስፍራ ሀብታም የሆነ ክርስቲያን ወንድምን ያመለክታል። ሀብታም ወንድም

---

[1] የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሆኑ *የጥበብና የዕውቀት* ስጦታዎች አሉ (1ቆሮ 12፥8 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ) ነገር ግን ያዕቆብ በዚህ ቁጥር ላይ የሚናገረው ስለ እነዚህ ልዩ ስጦታዎች ሳይሆን ባጠቃላይ ስለ ጥበብ ነው።

[2] በራሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ሊመካ ይገባዋል። *ከፍ ያለውን* (መንፈሳዊ) *ስፍራ* ያገኘው በራሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

በሀብቱ ሊመካ አይገባውም፤ ምክንያቱም ሀብቱ ፈጥኖ ሊጠፋ ይችላልና (ማቴ 6፥19–21)። ንግድ ለዘላለም የሚቆይ አይደለም፤ ከጊዜ በኋላ *ይጠፋል* (ቁ 11)። ሀብታም ወንድም ሀብቱን ማከማቸት *ሳይሆን ለድሆችና ለክርስቶስ* አገልግሎት ሊጠቀምበት ይገባዋል (ማር 10፥21–23 ይመልከቱ)። ሀብቱ የራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር እንደሆነ ሊቆጥር ይገባዋል። *ራሱን ዝቅ ያድርግ* (ቁ 10)፤ የዚያን ጊዜ *ትምክህቱ* በእግዚአብሔር እንጂ በሀብቱ ላይ አይሆንም (1ጢሞ 6፥17–19)።

ሀብታም ማን ነው? መሬትና ንብረት ያለው ሁሉ ራሱን ሀብታም አድርጎ ሊቆጥር ይገባዋል፤ እንዲሁም ጥቂት ሀብት ያለውን ክርስቲያን ሁሉ በዚህ ውስጥ ይመድበዋል። ጥቂት ሀብት ያላቸው ራሳቸውን «ሀብታም» አድርገው አይቆጥሩም፤ ነገር ግን ምንም ከሌላቸው ድሆች ጋር ሲነጻጸሩ በእርግጥ ሀብታሞች ናቸው።

የሰው ሀብት ይጠፋል፤ የእግዚአብሔር *ቃል* ግን ለዘላለም ይኖራል። ከእግዚአብሔር ይልቅ በሀብቱ የ*ታመነ* ሰው ከሀብቱ ጋር ይጠፋል። እንዲህ ያለው ሰው እንደሚረግፍና እንደሚጠፋ አበባ ነው (ኢሳ 40፥6–8፤ 1ጴጥ 1፥23–25 ይመልከቱ)። ማንም ሰው በሀብትና በእግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁለቱም ሊ*ታመን*ና ሊመካ አይችልም (ማቴ 6፥24 ይመልከቱ)።

ፈተናዎች 1፥12–18

12 የሚጸና አማኝ *የሕይወት አክሊል* ይቀበላል። «የሕይወት አክሊል» በኃጢአት ላይ ድል የማድረግ አክሊል ወይም በሕይወት ሩጫ ለሚገኝ ድል የሚሰጥ አክሊል ነው (1ቆሮ 9፥25፤ 2ጢሞ 4፥7–8)። ሆኖም *የሕይወት አክሊል* ዋነኛ ትርጉም ደኅንነት ወይም የዘላለም ሕይወት ነው፤ *እስከመጨረሻ በትዕግሥት የሚጸና ግን ይድናል* ማር 13፥13። መስቀላችንን ለአጭር ጊዜ ልንሸከም ይገባናል፤ ነገር ግን አክሊላችንን ለዘላለም እንደፋለን።

እግዚአብሔር የሕይወት አክሊልን እርሱን *ለሚወዱት* ሊሰጥ ቃል ገብቶአል። እርሱን የሚወዱት በእርሱ የሚያምኑና የሚታዘዙት ናቸው። ፍቅር፣ መታዘዝና እምነት የሚነጣጠሉ አይደሉም።

በዚህ ቊጥር ላይ የተጠቀሰውን ፈተና እንመልከት። ፈተና በሕይወታችን በተለያዩ ጊዜያት የሚመጡ ልዩ ልዩ መከራዎችንና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ያጠቃልላል[3]። እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ፈተና እምነታችንንና ብርታታችንን ለመመዘን በሕይወታችን እንዲመጣ ይፈቅዳል (ቊ 2)። ነገር ግን ፈተና ሲመጣ በኃጢአት ልንወድቅ እንችላለን። ለምሳሌ፡– በእምነታችን ምክንያት መከራ ቢገጥመን፣ እምነታችንን ለመተው እንፈተን ይሆናል። እምነትን መካድ ትልቅ ኃጢአት ነው። ወይም በእግዚአብሔር ጸጋ ሀብት የማግኘት ዕድል ቢገጥመን ይህን ሀብት ለራሳችን ብቻ ለመጠቀም፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሀብታችንን የመውደድ ፈተና ሊገጥመን ይችላል። ይህን ካደረግን በኃጢአት እንወድቃለን። እስቲ ሌላ ምሳሌ እንመልከት። ባለ ትዳር ብንሆንም ከሌላ ሰው ጋር በፍቅር እንጠመድ ይሆናል። እንዲህ ባለው ሁኔታ ኃጢአት የማድረግ ፈተና እጅግ ከፍተኛ ነው፤ እምነታችንም በእርግጥ ይፈተናል። እነዚህ ሁሉ ወደ ኃጢአት ሊመሩን የሚችሉ ፈተናዎች ናቸው። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ጸንተን ካልቆምን በኃጢአት እንወድቃለን። ፈተናው በራሱ ኃጢአት እንድናደርግ ምክንያት አይሆንም፤ ነገር ግን በውስጣችን ያለው ምኞትና ፍላጎት ኃጢአት እንድንሠራ ምክንያት ይሆናሉ (ቊ 14)። ኃጢአት ከኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን ይመጣል፤ ለሠራነው ኃጢአት ያለንበትን ሁኔታ ልንወቅስ አንችልም፤ ልንወቅስ የምንችለው ራሳችንን ብቻ ነው።

13–14 በእነዚህ ቊጥሮች ያዕቆብ *ፈተና* የሚል *ቃል* ተጠቅሞአል። ይህ *ቃል* በቊጥር 2 እና 12 ላይ የተጠቀሰው ፈተና ዓይነት ትርጉም የለውም። በዚህ በ*ታ* የተጠቀሰው፣ ኃጢአት ለማድረግ ያለውን ፍላጎት ለማመልከት ነው። እግዚአብሔር እንደ *ፈቃዱ* እምነታችንንና መንፈሳዊ ጥንካሬአችንን ለመመዘን ፈተና እንዲመጣብን ይፈቅዳል። ነገር ግን ኃጢአት እንድናደርግ እግዚአብሔር አይፈትንም። ኃጢአት እንድናደርግ የሚመጣ ፈተና ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከገዛ ራሳችን ኃጢአተኛ ፍላጎቶች ነው።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች በፈተና ተሸንፈው በኃጢአት ይወድ*ቃ*ሉ። ብዙውን ጊዜ «እግዚአብሔር ፈትኖኝ ወደቅሁ» በማለት ላደረጉት ኃጢአት እግዚአብሔርን ይወቅሳሉ። እንዲህ ያለውን ነገር ልናስብ ከቶ አይገባም፤ እግዚአብሔር ማንንም ሰው ኃጢአት እንዲሠራ አይፈትንም። ስለዚህ ይህን ምዕራፍ ስናነብ፣ ያዕቆብ ስለ ሁለት ነገሮች እንደሚናገር ልብ ልንል ይገባል። በ*መጀመሪያ* ከውጭ ሁኔታዎች ስለሚነሣው የእምነት መፈተን ይናገራል (ቊ 2–3፤12)። ሁለተኛው በቊጥር 13–14 በውስጣችን ካለ ክፉ ምኞት ስለሚነሣ ወደ ኃጢአት ስለሚመራ ፈተና ይናገራል። እግዚአብሔር ከውጭ የሚነሣውን ፈተና እምነታችንን ለመፈተን ሲል በሕይወታችን እንዲመጣ ይፈቅዳል። ነገር ግን ከውስጣችን የሚነሣው ፈተና ከእግዚአብሔር አይመጣም። *ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ ነገር አይፈተንም* እንዲያውም እርሱ ማንንም አይፈትንም (ቊ 13)። ከውጭ በሚመጣው ፈተና ጸንተን ልንቆም፣ ከውስጥ የሚነሣውን ፈተና ደግሞ ልናሸንፈው ይገባናል።

15 ሁሉም ክርስቲያኖች በየጊዜው ልዩ ልዩ ፈተናዎች ይገጥሟቸዋል፤ እነርሱም ክፉ ሐሳቦችና ምኞቶች ናቸው (2ቆሮ 10፥5 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ)። እነዚህን ወዲያው ካስወገድናቸው በኃጢአት አንወድቅም። ነገር ግን እነዚህ ክፉ ሐሳቦችና ምኞቶች ሥር እንዲሰዱና እንዲያድጉ ስንፈቅድ *ኃጢአት ይወለዳል*። እነዚህ ሐሳቦች ወደ ክፉ ድርጊት ባይመሩን እንኳ በራሳቸው በልባችን ስፍራ ከሰጠናቸው ኃጢአት ይሆናሉ። የኃጢአት ውጤት ደግሞ ሞት ነው። ኃጢአት ሰዎችን ወደ ዘላለም ሞት ይመራቸዋል (ሮሜ 6፥23፤ ገላ 6፥7–8)።

16–17 *አትታለሉ!* እግዚአብሔር ሰዎችን ክፉ ነገር እንዲያደርጉ አይመራም። እርሱ ወደ መልካም ነገር ብቻ ይመራል። እግዚአብሔርን ለሚወዱ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ለጥቅማቸው ነው (ሮሜ 8፥28)። እግዚአብሔር የሚሰጠው ስጦታ መልካምና ፍጹም ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ *መልካምና ፍጹም* ስጦታ ከእግዚአብሔር ነው።

ያዕቆብ እግዚአብሔርን *የብርሃን ሁሉ አባት* ይለዋል። እንዲህ ሲል እግዚአብሔር የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ፈጣሪ ነው ማለቱ ነው። ነገር ግን እርሱ እንደ እነዚህ «የሰማይ ብርሃናት» በቀንና በሌሊት የሚለዋወጥ አይደለም። የእግዚአብሔር ብርሃን ሁልጊዜ ያበራል፤ በእርሱ ዘንድ ጨለማ የለም (ዮሐ 8፥12፤1ዮሐ 1፥5)።

18 *እግዚአብሔር . . . በፈቃዱ . . . ወለደን*። ይህም እርሱ በፈቃዱ ፈጠረን፤ በፈቃዱ የእርሱ ቤተሰብ እንድንሆን መረጠን ማለት ነው (ኤፌ 1፥4–5)። በኢየሱስ በማመን ክርስቲያን መሆን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ አዲስ መወለድ ማለት ነው (ዮሐ 1፥12፤3፥3)። በሌላ አገላለጽ አዲስ ፍጥረት መሆን ማለት ነው (2ቆሮ 5፥17)።

እግዚአብሔር የፈጠረን በእውነት *ቃል* ነው። የእውነት *ቃል* ኢየሱስ ራሱ ማለት ሊሆን ይችላል (ዮሐ1፥1–3)፤ ወይም የክርስቶስ ወንጌል ሊሆን ይችላል (1ጴጥ 1፥23)። ሁለቱም ትርጓሜዎች እውነት ናቸው።

እግዚአብሔር ለምን በእርሱ ቤተሰብ ውስጥ እንድንወለድ አደረገ? ይህን ያደረገው የፍጥረቱ ሁሉ *መጀመሪያ* እንድንሆን ነው። ክርስቶስ ራሱ በአማኞች መካከል በኩር ነው (1ቆሮ 15፥20–23)። እንዲሁም አማኞች በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ የ*መጀመሪያ* ናቸው። በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት እስራኤላውያን የምርታቸውን የ*መጀመሪያ* ፍሬ በየዓመቱ ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸው ነበር (ዘኁ 18፥12)። ያ ፍሬ ከሁሉ የተሻለ እንደ ሆነ ይቆጠር ነበር። ስለዚህ አማኞች ከሰዎች ሁሉ እንደ

---

[3] ፈተናዎች በዚህ መልኩ በእኛ ላይ የመጡ መጥፎ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን መልካም ነገሮችንም ያጠቃልላሉ። እነዚህ ፈተናዎች እምነታችንንና መታዘዛችንን ልክ እንደ አስቸጋሪ ፈተናዎች ስለሚመዝኑ መልካም ናቸው። ስለዚህ በዚህ ቊጥር ፈተና ማለት «የእምነት መመዘን» ማለት ነው።

ተሻለ ለእግዚአብሔር እንደሚቀርቡ የበኵራት ምርጥ ፍሬ ናቸው። እንዲህ ያለው ስጦታ እግዚአብሔር ደስ ያሰኘዋል።

መስማትና ማድረግ (1፥19–27)

19 ሁልጊዜ እግዚአብሔርን፣ ቃሉን ለመስማትና እርስ በርስ ለመደማመጥ ፈጣንና የተዘጋጀን ልንሆን ይገባናል። አብዛኛውን ጊዜ የሚናገርና ጥቂት ጊዜ የሚሰማ ሰው ትዕቢተኛ ነው። ለሌሎች ሐሳብ ግድ የለሽ ነው።
እንዲሁም ለመናገር የዘገየን ልንሆን ይገባናል። ይህ ማለት ከመናገራችን አስቀድመን ስለምንናገረው ነገር ማሰብ አለብን። አንድ ነገር ከመናገራችን በፊት ራሳችንን ሦስት ጥያቄዎች ልንጠይቅ ይገባናል፤ የምንናገረው እውነት ነው? የምንናገረው መልካም ነገር ነው? ደግሞስ አስፈላጊ ነውን? እውነተኛ፣ መልካምና አስፈላጊ ከሆነ የዚያን ጊዜ እንናገር። ካልሆነ ግን ዝም እንበል።

ለመናገር የዘገየን ከመሆን በተጨማሪ ለቍጣም የዘገየን ልንሆን ይገባናል። መቆጣት ሁልጊዜ ኀጢአት አይደለም (ኤፌ 4፥26)። ለምሳሌ፣ ትክክል ስላልሆነ ነገር መቆጣት ኀጢአት አይደለም (ማር 11፥15–17)። ነገር ግን ራስን መግዛትና መቆጣጠር እስከሚያቅት ከደረሰ የዚያን ጊዜ ኀጢአት ይሆናል። ቶሎ ልንቆጣ አይገባም። ከመቆጣታችን በፊት ስለ ጉዳዩ ከፉነት እርግጠኞች መሆን አለብን። ቍጣችን የእግዚአብሔር እንጂ የሰው ሊሆን አይገባም፤ የግላችን ሆኖ ለበቀል የሚያነሣሣንም መሆን የለበትም። በኀጢአት ላይ እንጂ በኀጢአተኛው ላይ ልንቆጣ አይገባንም፤ አለበለዚያ እኛ ራሳችን ኀጢአትን እናደርጋለን።

20 የሰው ቍጣ ጽድቅን አይሠራም፤ ምክንያቱም ቍጣው የሚያመራው ወደ ድርጊቱ ሳይሆን ወደ ሰዎች ስለሆነ ነው። የሰው ቍጣ ራስ ወዳድ ነው። የሰው ቍጣ የሚነሣው የሰው ፍላጎት ስለተነካ እንጂ የእግዚአብሔር ፍላጎት ስለተነካ አይደለም። የሰው ቍጣ ስለ እግዚአብሔር ሲባል የሚፈጸም አይደለም፤ ስለዚህ *የሰው ቍጣ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ በሰው ሕይወት ውስጥ ፍጹም እንዲሆን አያደርግም።*

21 *ስለዚህ ርኩሰትንና የክፋትንም ብዛት ሁሉ አስወግዱ።* ጳውሎስና ጴጥሮስ በመልእክቶቻቸው ውስጥ በተደጋጋሚ የጻፉትን ምክር ያዕቆብ በዚህ ስፍራ ይናገራል (ኤፌ 4፥22፤31፤5፥3፤ 1ጴጥ 2፥1 እና ማብራሪያዎችን ይመልከቱ)።

22 በቁጥር 19 ላይ ያዕቆብ *ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ይሁን* ይላል። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቻ በቂ አይደለም፤ *መታዘዝም* ያስፈልጋል። የምንድነው ቃሉን በመስማት ሳይሆን በማመን ነው። እውነተኛ እምነት ሁልጊዜ *መታዘዝ* ያለበት ነው (ያዕ 2፥14–17)።

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው «እንዴት የሚያስደንቅ ቃል ነው!» ይላሉ። የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነቡና የሚወዱ ቢሆኑም ካልታዘዙት ምንም አያደርግላቸውም። እንዲያውም በቃሉ ይፈረድባቸዋል። የእግዚአብሔርን ቃል የማይታዘዙ ሰዎች እውነተኛ እምነት የላቸውም፤ *ራሳቸውን ያታልላሉ።*

23–24 በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቃል እንደ መስታወት በምሳሌ ቀርቧል። ራሳችንን በመስታወት ስንመለከት እውነተኛውን ፊታችንን፣ እውነተኛውን ማንነታችንን (ገጽታችንን) እናያለን፤ በቃሉም ኀጢአተኛ ተፈጥሮአችንንና ኀጢአታችንን እናያለን። ቃሉን የምንሰማ ብቻ ከሆን'ን ራሱን በመስታወት ተመልክቶ፣ ኀጢአቱንም አይቶ ወዲያው እንደሚረሳ ሰው እንሆናለን። ከ«መስታወቱ» ወዲያው አንዙር። ይልቁኑ መስታወቱ የሚያሳየንን በእርጋታ ተመልክተን ማድረግ የሚገባንን እናድርግ። ፊታችንን ልናጠራ፣ በመስታወቱ ውስጥ ያየነውን ኀጢአታችንን ልናስወግድ ያስፈልጋል።

25 በዚህ ቦታ ያዕቆብ ራሱን በመስታወት በሚገባ ስለሚመለከት ማለትም *ፍጹሙን ሕግ* ስለሚመለከት ሰው ይናገራል። ይህ ፍጹም ሕግ የክርስቶስ ቃል፣ የክርስቶስ ወንጌል ነው። ወንጌል እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያድንበት ኀይል ነው (ሮሜ 1፥16)። ስለዚህ የክርስቶስ ወንጌል የሆነው ይህ *ፍጹም ሕግ* ከኀጢአትና ፍጻሜው ሞት ከሆነው ከኀጢአት ቅጣት ነጻ ያወጣናል።
የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ፍጹሙን ሕግ በሚገባ የሚመለከት ሰው አይዘነጋውም፤ እንዲያውም ይጠብቀዋል፤ ያደርገውማል። እንዲህ ያለው ሰው በዚህ ምድር ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ሕይወት *የተባረከ* ይሆናል።

26 ብዙ ሰዎች ሃይማኖተኛ እንደሆኑ ያስባሉ፤ ሃይማኖተኛነታቸው ግን ውጪያዊ ነው። በውስጣቸው ልባቸው በክፋት የተሞላ ስለሆነ ሲናገሩ እንኳ ከአንደበታቸው ክፉ ቃላት ይወጣሉ። እንዲህ ያሉ ሰዎች እውነተኛ ሃይማኖተኞች አይደሉም።

የእውነተኛ ሃይማኖተኛ ሰው አንዱ ምልክት አንደበቱን መግታት መቻሉ ነው። እውነተኛ ሃይማኖት አንደበትን መግታት የሚያስችል ኀይል ይሰጣል። ሐሰተኛ ሃይማኖት ግን እንዲህ ያለውን ኀይል አይሰጥም፤ ይህ ሃይማኖት *ከንቱ* ነው።

በክርስቲያኖች መካከል በተደጋጋሚ የሚከሰተውና አጥፊ የሆነው ኀጢአት ከአንደበት የሚመጣው ነው፤ በተለይም አንደበታችንን ሌሎች ለመኮነንና እርስ በርስ በምንካሰስበት ጊዜ ይህ ጥፋት ይከሰታል (ያዕ 3፥6፤8)። ኢየሱስ ራሱ የምንናገረው በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጠው እንዲህ ሲል ተናግሯል፤ «*በእውነት እላችኋለሁ፥ ሰዎች በሚናገሩት ምንም ጥቅም በሌለው ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል። ምክንያቱም ከቃልህ የተነሣ ይፈረድበታል፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈርድብሃል*» (ማቴ 12፥36–37)።

27 ነውር የሌለበት ንጹሕ ሃይማኖት ማለትም እውነተኛ ሃይማኖት ይህ ነው፤ በመጀመሪያ ወላጆች ለሌላቸው ልጆችና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች እንክብካቤ በማድረግ መልካም ሥራ ማድረግ፤ ሁለተኛ ራስን ከዓለም ርኩሰት መጠበቅ ነው (ያዕ 4፥4)። በአጭሩ የእውነተኛ ሃይማኖተኛነት ማረጋገጫ ንጹሕ ሕይወት ለሌሎች ፍቅር ያለው ልብ ናቸው።

ምዕራፍ 2

አድልዎ ማሳየት አይገባም (2፥1–13)

1 *ወንድሞቼ ሆይ! . . . በሰው መካከል አድልዎ አታድርጉ።* ይህ ማለት የሰውን ሥልጣንና ሀብት በማየት አድልዎ አታድርጉ፤ የሰውን ውጪያዊ ገጽታ አትመልከቱ። ሰዎችን በሀብታቸው፣ በኅብረተሰብ ውስጥ ባላቸው ቦታና በኑሮ ደረጃቸው መከፋፈል የለብንም። የክርስቶስ የክብሩ ብርሃን የዚህን ዓለም ክብር ከንቱ ያደርገዋል። ስለዚህ የሰዎችን ምድራዊ ክብርና ሁኔታዎች ሳይሆን የክርስቶስ ብርሃን በሕይወቱ ምን ያህል እንዳበራ እንመልከት። የሰውን ውጪያዊ ሁኔታ ከማየት ይልቅ ውስጣዊውን መንፈሳዊ ሕይወት እንመልከት።

2–4 ያዕቆብ ለትምህርቱ ምሳሌ እንዲሆኑ ወደ ክርስቲያኖች ስብሰባ ስለ መጡ አንድ ሀብታምና አንድ ደሃ ሰዎች ይናገራል። አድልዎ ማሳየት የሌለብን በስብሰባዎች ጊዜ ብቻ አይደለም። ወደ ቤታችን የመጡ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ዓይን ልንመለከት ይገባናል። ሁልጊዜ ለማንኛውም ሰው ከከፍተኛ የመንግሥት ባለ ሥልጣን አንሥቶ እስከ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላለው ሰው ተመሳሳይ ፍቅር ልናሳይ ያስፈልጋል። ይህን ካላደረግን ራሳችንን በሰዎች መካከል ፈራጆች አድርገን አስቀመጥን ማለት ነው (ቍጥር 9)። እግዚአብሔር አድልዎን ስለማያደርግ እኛም አድልዎ ማድረግ የለብንም (ሮሜ 2፥11፤ ኤፌ 6፥9)።

5 ያዕቆብ በነበረበት ዘመን አብዛኛዎቹ አማኞች ድሆች እና ብዙዎቹ ባሮች ነበሩ። ከድህነታቸውና ከሥቃያቸው ብዛት የተነሣ የክርስቶስን ወንጌል እንደ ታላቅ የተስፋ ቃል፣ ከመከራቸውም ነጻ የሚያወጣ ተስፋ አድርገው ይቆጥሩ ነበር። በእኛም ዘመን እንዲሁ ነው፤ ብዙውን ጊዜ ሀብታሞች ወደ ክርስቶስ አይመጡም (ማር 10፥23–25)። በትውልድ ሁሉ እግዚአብሔር ድሆችን፣ የተናቁና ተራ ሰዎችን *የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ* መርጦአል፤ ይህም የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። በዚህ ዓለም ድሆች ናቸው፤ በሰማይ ግን

ሀብታም ይሆናሉ። በዚህ ዓለም እንኳ «ሀብታም» ናቸው፤ ይህም *በእምነት ሀብታሞች* መሆናቸው ነው። በእምነት ሀብታሞች የሚሆኑት እምነታቸውን በምድራዊ ሀብት ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ስላደረጉ ነው።

6–7 ብዙ ሰዎች ወንጌልን ማዳመጥ አይወዱም፤ ምክንያቱም ወንጌል ለድሆች ማካፈልን ስለሚያስተምር ነው (ማር 10:21–22)። አብዛኞቹ ሀብታም ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ሀብታቸውን ይወዳሉ (ማቴ 6፥24)፡ ብዙ ባለ ሥልጣናት ወንጌል ማድመጥ የማይፈልጉት ወንጌል ሥልጣን ሁሉ የክርስቶስ እንደ ሆነ ስለሚናገር ነው (ማቴ 28:18)። በዚህ ምክንያት ብዙ ሀብታሞችና ባለ ሥልጣናት ክርስቶስንና ተከታዮቹን ይቃወማሉ። የክርስቶስን *ክቡር ስም* ይሳደባሉ፡ ተከታዮቹንም ይጨቍናሉ፤ ወደ ፍርድ ቤትም ይወስዱቸዋል።

ሆኖም ያዕቆብ መልእክቱን የጻፈላቸው እነዚህ አማኞች ድሆችን በመናቅ ለሚያሳዱዷቸው ሀብታሞችና ባለ ሥልጣናት ግን ታላቅ ክብር ይሰጣሉ።

8–9 *«ሰውን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ»* የሚለው ሁለተኛው ታላቅ ትእዛዝ ነው (ዘሌ 19፥18፤ ማር 12፥31)። ይህ ሁሉንም ሰው፡ ሀብታም ይሁን ደሃ በእኩል ዓይን መውደድ እንዳለብን ይናገራል። ነገር ግን *በሰዎች መካከል ልዩነት ብናደርግ* ሁለተኛውን ትእዛዝ እንጥሳለን። እንዲህ በማድረጋችን *ሕግ ተላላፊዎች* እንሆናለን (ቍጥር 9)።

ያዕቆብ በዚህ ቦታ ሁለተኛው ትእዛዝ የነገሥታት ንጉሥ ትእዛዝ ስለሆነ የእግዚአብሔር *መንግሥት ሕግ* በማለት ይጠራዋል። በምድር ላይ የንጉሥ ሕግ ትልቁ ሕግ ነው። ሁለቱ የክርስቶስ ታላላቅ ትእዛዛትም እንዲሁ ናቸው። የትኛውም ሌላ ሕግ ከእነዚህ አይበልጥም (ማር 12፥29–31)።

10 በአንድ አገር ብዙ ሕግጋት አሉ። አንድ ሰው ከእነዚህ ሕግጋት አንዲቷን ቢተላለፍ ወንጀለኛ ይሆናል። በእግዚአብሔር ሕግም እንዲሁ ነው። ከብሉይ ኪዳን ሕግ በተጨማሪ ብዙ ደንቦችና ሥርዓቶች አሉ። አንድ ሰው ሁሉንም ጠብቆ አንዲቷን ቢተላለፍ፤ በአንዱ ምክንያት የጠበቃቸው ሌሎቹ ሁሉ ከንቱ ይሆናሉ፤ በዚህም ሕግ ተላላፊ ሆኖ ይወነጀላል (ገላ 3:10)። ስለዚህ በሰዎች መካከል አድልዎ እንዳናደርግ ያዕቆብ ይነግረናል። አለበለዚያ ግን ሁሉንም ሕግ እንደተላለፍን ይቆጠራል።

11 ከዐሥርቱ ትእዛዛት ሁለቱን ለምሳሌ በመጥቀስ (ዘፀ 20:13–14)፡ ያዕቆብ እንደገና አንድ ሰው ሕግን ሙሉ ካልጠበቀ ሕግ ተላላፊ ተደርጎ እንደሚቆጠር ያሳያል። በዚህ ቦታ ግን ያዕቆብ ለማሳየት የፈለገው ነገር ማንም ሰው ሁልጊዜ ሕግን ሙሉ በሙሉ መጠበቅ እንደማይችል ነው። ለዚህም ነው በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ማንም ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቅ የማይችለው (ገላ 2፥15–16 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ)።

12 እኛ ክርስቲያኖች *በነጻነት ሕግ መራመድ* ይገባናል ምክንያቱም እግዚአብሔር ሚፈርድብን በዚህ ሕግ ነውና። *የነጻነት ሕግ* ምንድን ነው? ይህ የክርስቶስ ሕግ ነው። ሁለቱ ታላላቅ ትእዛዛትና ዐሥርቱ ትእዛዛት በክርስቶስ ሕግ ውስጥ ተጠቅሰዋል። ነገር ግን «ነጻነት የሚሰጥ ሕግ» የተባለው ለምንድን ነው? ምክንያቱ እንደ ባሮች፤ ይህን ሕግ በግድ ስለማንከተል ነው፤ እንደ ልጆች በፈቃዳችን ሕጉን እንከተላለን። ክርስቶስ አዲስ ፍላጎት፤ አዲስ ልብስና አዲስ ሕይወት ሰጥቶናል። ሕጉንም መከተል የምንችልበትን ኀይል ሰጥቶናል። ይህ ብቻ ሳይሆን ሕጉን በየትኛውም መንገድ ብንተላለፍ ይቅር ይለናል። ከእንግዲህ ወዲህ የኀጢአት እስረኞች አይደለንም። ክርስቶስን ለመከተልና እርሱን ለመታዘዝ ነጻ ሰዎች ነን (ዮሐ 8፥31–32፤36)። ያዕቆብ የክርስቶስን ሕግ *የነጻነት ሕግ* ያለው ለዚህ ነው።

13 ያዕቆብ በቁጥር 12 ላይ *ንግግራችሁም፤ ሥራችሁም በነጻነት ሕግ የሚፈርድባችሁ መሆናችሁን በማሰብ ይሁን* ይላል፤ ይህም የክርስቶስ ሕግ ነው። የአይሁድ ሕግ የሆነው የብሉይ ኪዳን ሕግ አንድም ምሕረት የሚባል ነገር አይታይበትም (ዘዳ 17፥2–7)። ነገር ግን የክርስቶስ ሕግ ምሕረት የተሞላ ነው። ለሌሎች ምሕረት ካደረግን፤ እግዚአብሔርም ምሕረት ያደርግልናል። ለሌሎች ምሕረት ካላደረግን ግን እኛም ምሕረትን አናገኝም (ማቴ 5፥7፤ 6፥12፤14–15)። ለሌሎች ምሕረትን ካላሳየን፡ እኛም በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት ይፈረድብናል። ስለዚህ በምሕረት ሕግ ፍርድ እንድንቀበል ምሕረት በተሞላ መንገድ እንድንናገርና እንድናደርግ ያዕቆብ ይነግረናል።

ምሕረት ከፍርድ ይበልጣል። ፍርድ ከምሕረት ከበለጠ ማናችንም ከኩነኔ አናመልጥም። ፍርድ ከምሕረት የሚበልጥ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን ክርስቶስን አይልክም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ምሕረትን ከፍርድ ከፍ አድርጎ አስቀመጠ። ስለዚህ እኛም ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት እንዲህ ልናደርግ ይገባናል። ለሰው ሁሉ ያለ ምንም አድልዎ ፍቅርን ማሳየትና ምሕረትን ማድረግ ይገባናል። ለሌሎች ባሳየነው ምሕረት መጠን እግዚአብሔርም ለእኛ ምሕረት ያደርግልናል።

እምነትና ሥራ (2፥14–26)

14 «አምናለሁ» ማለት ቀላል ነገር ነው፤ ነገር ግን እንዲህ ማለቱ ብቻ ትርጉም የለውም። «እምነቴ እውነተኛ ነው ወይስ ሐሰተኛ?» ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ምክንያቱም የዳንነው በእውነተኛ እምነት እንጂ በሐሰተኛ እምነት አይደለም።[4]

እምነታችን እውነተኛ ይሁን ወይም ሐሰተኛ በምን ልናውቅ እንችላለን? ይህ የሚታወቀው *በሥራችን* ነው፤ ይህም የፍቅር ሥራችን፤ የመታዘዝ ተግባራችን የእምነታችንን ማረጋገጫ ነው። እምነታችን የሚገልጽ ሥራ ከሌለን እንዲህ ያለው «እምነት» አያድነንም (ማቴ 7፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ)። እንዲህ ያለው እምነት እውነተኛ እምነት አይደለም *የሞተ* እምነት ነው (ቍጥር 17)።

15–16 በዚህ ቦታ ያዕቆብ ስለ ሐሰተኛ እምነት ሲናገር፤ ይህ በቃላት ብቻ እንጂ በሥራ እንደማይገለጽ ፍቅር ነው። ድሃ ለሆኑ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንደምንወዳቸው እየተናገርን በችግራቸው የማንረዳቸው ከሆንን እምነታችን ሐሰተኛና ጥቅም የለሽ ነው (1ዮሐ 3፥17–18)። እንዲህ ዓይነቱ «ፍቅር» ማንንም አይጠቅምም። በተመሳሳይ መልኩ እምነታችን በሥራ ካልተገለጸ ዋጋ የለውም።

17 ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉ በጣም ጠቃሚ ከሆኑ ጥቅሶች መካከል አንዱ ነው፤ ምክንያቱም የጳውሎስን ትምህርት ያለ አግባቡ እንዳንተረጉም ይረዳናል። በኤፌሶን 2፥8–9 ጳውሎስ ሰው በሥራ ሳይሆን በእምነት እንደሚድን ጽፎአል። ብዙ ሰዎች ይህን በአግባቡ ሳይረዱ አንድም መልካም ሥራ መሥራት እንደሌለባቸው ያስባሉ። ሰው በእምነት ስለዳነ መልካም ነገር መሥራት እንደማያስፈልገው ይገምታሉ። ጳውሎስ በሌላ ስፍራ መልካም ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ያስተማረውን ዘንግተዋል። ጳውሎስ በኤፌሶን 2፥10 ላይ *እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጃቸውን መልካም ሥራዎች እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት የተፈጠርን እንድሆንን ጽፎአል። በገላትያ 5፥6 ላይ ደግሞ በፍቅር አማካይነት በሥራ ላይ የሚውል እምነት* እንደሚጠቅም ጽፎአል።

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ ክርስቲያኖች መልካም ሥራ መሥራት እንደሌለባቸው የሚያስቡት የተሳሳተ አመለካከት እንዲታረም ያሳስባል። በእምነት እንጂ በሥራ አለመዳናችን እርግጥ ነው። ማንም ምንም ያህል ብዛት ያለው መልካም ሥራን ቢያደርግ ደኅንነትን ሊያገኝ አይችልም፤ ይህ እውነት ነው። ሆኖም «እምነት ምንድን ነው?» ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። እውነተኛ እምነት በሥራ የሚገለጽ ነው። ሥራ ሁልጊዜ ከእምነት ጋር የሚሄድ ነው። ያለ ሥራ የሚገለጽ እውነተኛ እምነት የለም። እውነተኛ እምነት ሁልጊዜ ወደ መልካም ሥራ ይመራል።

መልካም ሥራ ምንድን ነው? ከመታዘዝ ጋር የሆነ ሥራ ነው። እግዚአብሔር እንድናደርገው የሚፈልገው ሥራ የኢየሱስን ትእዛዛት እንድንፈጽም ነው (ዮሐ 14፥15)።

---

[4] ስለ እምነት በሚናገረው በዚህ ማብራሪያ ውስጥ እምነት ብቻ እንዳላደነን ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ደኅንነት ያገኘነው በጸጋ ነው፤ ያዳነንም እግዚአብሔር ነው (ኤፌ 2፥8–9 እና ማብራሪያውን ይመ)።

የኢየሱስ ዋና ትእዛዝ ደግሞ እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተም እርሱ በርሳችሁ እንድትዋደዱ የሚል ነው (ዮሐ 15፥12)። ስለዚህ እውነተኛ እምነት ሁልጊዜ ራሱን የሚገልጸው በፍቅር ነው (ገላ 5፥6)። አንድ ሰው ራሱን እንደሚወድ ለሌላውም ሰው እንዲህ ያለውን ፍቅር ቢያሳይ፤ ይህ ሰው እውነተኛ እምነት እንዳለው እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

በመጀመሪያ ከሥራ በፊት እምነት ይመጣል። ካመንን በኋላ አዲስ ሰዎች እንሆናለን። በዚያን ጊዜ እውነተኛ እምነት በኑሮአችን የባሕርይ ለውጥ ያመጣል። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሕይወታችንን በፍቅሩ ይሞላል (ሮሜ 5፥5)። ባልንጀራችንን እንድንወድና የክርስቶስን ሌሎች ትእዛዛት መፈጸም እንድንችል አዲስ ኀይል እንቀበላለን። ይህ አዲስ ፍቅርና አዲስ መታዘዝ እምነታችን እውነተኛ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።

ስለዚህ በአጠቃላይ አዲስ ኪዳን ደኅንነትን በገዛ ሥራችንና ጥረታችን ሳይሆን በእውነተኛ እምነት እንደምናገኝ ያስተምራል። ነገር ግን እውነተኛ እምነት ሁልጊዜ በፍቅራችንና በመታዘዛችን ይገለጣል ፍቅርና መታዘዝ ከሌለ ግን እምነት የለም። ሥራ በፍቅርና በመታዘዝ[5] ሲገለጽ ለእምነታችን ማረጋገጫ ይሆናል። ያለ ፍቅርና ያለ መታዘዝ እምነታችን አያድነንም፤ ይህም የሞተ እምነት ነው።

ከኢየሱስ ጋር ከተሰቀሉት ከሁለቱ ወንጀለኞች አንዱ ከመሞቱ በፊት አመነ (ሉቃ 23፥39–43)። ካመነ በኋላ ግን አንድም መልካም ሥራ የመሥራት ዕድል አልነበረውም። ከዚህ የምንረዳው ይህ ሰው የዳነው በሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ እንደሆነ ነው። ነገር ግን በሥጋ ያልሞቱ ሰዎች ካመኑበት ጊዜ ጀምሮ በሕይወት እስካሉ ድረስ እምነታቸው በፍቅር ሥራና በመታዘዝ ሊገለጽ ይገባዋል።

18 ያዕቆብ በዚህ ስፍራ በሁለት ሰዎች መካከል ያለውን ንግግር በምናባዊ ምሳሌ ያቀርባል። የመጀመሪያው ሰው እምነት ብቻ እንጂ ሥራ እንደማያስፈልግ ይናገራል። ሁለተኛው ደግሞ እምነትና ሥራ ሁለቱም እንደሚያስፈልጉ ይናገራል። ሁለተኛው ሰው (ያዕቆብ) የመጀመሪያውን ሰው እንዲህ ይለዋል፤ «እምነት እንዳለህ ትናገራለህ?» *እምነትህን ከሥራ ለይተህ አሳየኝ*። እምነትህ ያለ ሥራ ስለ ሆነ ልታሳየኝ አትችልም። ነገር ግን *በሥራዬ እምነቴን አሳይሃለሁ*። ሥራዬ የእምነቴ ማረጋገጫ ነው።»

19 አሁንም የምናባዊው ንግግር በመቀጠል ሁለተኛው ሰው (ያዕቆብ) የመጀመሪያውን ሰው «*አንድ እግዚአብሔር አለ* ብለህ *ታምናለህ*።» ‘አንድ እግዚአብሔር’ አለ ብለህ በመናገርህ እውነተኛ እምነት እንዳለህ የምታሳይ ይመስልሃል። ነገር ግን ተሳስተሃል። እንዲህ ማለትህ ምንም አያሳይም። *አጋንንት* እንኳ እግዚአብሔር እንዳለ *ያምናሉ*፤ ነገር ግን ሥራቸው ክፉ ስለሆነ እምነታቸው ሐሰተኛ ነው ይለዋል።

20–21 ንግግሩ እንደ ቀጠለ ሁለተኛው ሰው (ያዕቆብ) ለመጀመሪያው ሰው ስለ አብርሃም ያስታውሰዋል። እግዚአብሔር አብርሃምን ልጁን ይስሐቅን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርበው ይነግረዋል (ዘፍ 22፥1–13፤ ዕብ 11፥17–19)። አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ እውነተኛ እምነት ስለነበረው እግዚአብሔርን ታዘዘ። አብርሃም ጻድቅ ሆኖ የተቆጠረው ለምን ነበር (ቊ. 21)? በማመኑ ነበር ወይስ በመታዘዙ? አብርሃም ጻድቅ ሆኖ የተቆጠረው በማመኑና በመታዘዙ ነበር።

22 የአብርሃም *እምነትና ሥራ* (መታዘዝ) በአንድ ላይ ይገለጹ ነበር። እምነት ያለ መታዘዝ የሞተ ነው (ቊ. 17)። ያለ እምነት መታዘዝ ዋጋ ቢስ ነው፤ እግዚአብሔርን በፍጹም ደስ አያሰኘውም፣ ምክንያቱም *ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም* (ዕብ 11፥6)።

የአብርሃም እምነት መጀመሪያ ቢሆንም እምነቱ በመታዘዙ ፍጹም ወይም ሙሉ ሆነ። ያለ መታዘዝ የሆነ እምነት እንደማይጠቅም ፍሬ አልባ ዛፍ ነው። አንድ ዛፍ ሙሉ የሚሆነው ፍሬ ሲሰጥ ነው። እንዲሁም እምነታችን ፍጹም የሚሆነው በታዘዥነት በምንሠራው ሥራ ነው። ሰዎች የሚያውቁን በፍሬአችን፤ በመታዘዛችን ነው (ማቴ 7፥20)።

23 ያዕቆብ በዚህ ቦታ ከዘፍጥረት 15፥6 አብራም በእግዚአብሔር አመነ፤ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት የሚለውን ቊጥር ይጠቅሳል (ሮሜ 4፥1–3)። ከዚህ የምንረዳው ነገር ሰው በእምነቱ ጻድቅ ሆኖ ይቆጠራል። ሆኖም ያ እምነት በፍቅርና በመታዘዝ የሚገለጽ እውነተኛ እምነት መሆን አለበት።

ቀደም ብሎ የተናገረውን መድገም ያስፈልጋል። ያለ ሥራ በሆነ እምነት መዳን እንደማንችል ሁሉ ያለ እምነት በሆነ ሥራም ልንድን አንችልም። የማንም ሰው ሥራው፤ ሃይማኖታዊ ሥራው ቢሆን እንኳ ፍጹም ሊሆን አይችልም። እያንዳንዱ ሰው ስህተት ይሠራል፤ በተለያዩ ጊዜያት ኀጢአትን ያደርጋል። ስለዚህ በሥራችን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ተብለን መቆጠር በፍጹም አንችልም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ አንድንም። በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራና ጽድቅ ላይ እምነታችንን ካላደረግን በስተቀር ጻድቃን ተብለን ልንቆጠር አንችልም (ሮሜ 3፥22–24 እና ማብራሪያውን ይመ)። ራሳችንን ጻድቃን ልናደርግ ወይም በራሳችን ጉልበትና ጥረት ደኅንነትን ማግኘት አንችልም። የክርስቶስን ጽድቅ በእምነት በመቀበል ብቻ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ተብለን ልንቆጠር እንችላለን።

24 ጳውሎስ በገላትያ 2፥15–16 እና ኤፌሶን 2፥8–9 ላይ ሰው በእምንት እንደሚጸድቅና እንደሚድን ተናግሯል። ያዕቆብም ከዚህ እውነት ጋር ይስማማል። በዚህ ስፍራ ያዕቆብ የሚናገረው ይህ እምነት እውነተኛ መሆን አለበት ማለትም በፍቅርና በመታዘዝ የሚገለጥ እምነት መሆን እንዳለበት ነው። ስለዚህ ያዕቆብ *ሰው የሚጸድቀው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራም ጭምር መሆኑን* ይናገራል። የምንጸድቀው በሥራ በሚገለጥ እምነት እንደሆነ ያዕቆብ አስረግጦ ይናገራል።

25 ያዕቆብ በዚህ ቊጥር ከብሉይ ኪዳን ሁለተኛ ምሳሌ በመጥቀስ ስለ አመንዝራይቱ ረዓብ ይናገራል (ኢያሱ 2፥1–16፤ ዕብ 11፥31 ይመ)። ረዓብ በኢያሱ የተላኩትን *ሰላዮች ረዳቻቸው*። እምነቷ እውነተኛ እንደ ነበር እንዴት እናውቃለን? ረዓብ አይሁዳውያኑ ሰላዮች እንዲያመልጡ ማድረጓ እምነቷ እውነተኛ እንደ ነበር ያረጋግጣል። የዚህም ውጤት ረዓብ ከሞት እንድታመልጥ ሆነ። ኢያሱና ሠራዊቱ ኢያሪኮን ባወደሙ ጊዜ ረዓብ እንድትተርፍ መመሪያ ሰጥቶ ነበር (ኢያሱ 6፥24–25)።

26 ያዕቆብ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው በማለት በድጋሚ ዋና ሐሳቡን ያስተላልፋል (ቊጥር 17 እና ማብራሪያውን ይመ)። ከሥራ የተለየ እምነት፤ ከነፍስ እንደተለየ ሥጋ ነው፤ ከሬሳም የተሻለ አይደለም።

ምዕራፍ 3

አንደበትን መቆጣጠር (3፥1–12)

1 *ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ*። ያዕቆብ ይህን ያለው ለምንድን ነው? ምክንያቱ በያዕቆብ ዘመን (ዛሬም በእኛ ዘመን) ብዙ ሰዎች አስተማሪዎችና መሪዎች ለመሆን ይሞክሩ ነበር። ለራሳቸው ክብርንና ከፍ ያለ ቦታን ይፈልጉ ነበር። ያዕቆብ በዚህ ቦታ የሚናገረው «ክብርንና ከፍ ያለ ቦታን ለማግኘት ስትሉ አስተማሪ ለመሆን አትፈልጉ» ነው። አስተማሪ መሆን ትልቁ ጉዳትም ሊሆን ይችላል። አስተማሪዎችና መሪዎች ከሌሎች ይልቅ ዕውቀትና ኀላፊነት ስለ ተሰጣቸው በፍርድ ቀን የባሰ ፍርድ ሊቀበሉ ይችላሉ (ሉቃስ 12፥47–48)።

ስለዚህ *ብዙዎች* አስተማሪዎች ለመሆን መፈለግ የለባቸውም። ነገር ግን አንዳንዶች አስተማሪዎች ሊሆኑ ይገባል። አስተማሪ ወይም መሪ መሆን መልካም ነው (1ጢሞ 3፥1)። በዚህ ሁኔታ አስተማሪዎች ሊሆኑ የሚገባቸው እንዴት ያሉ ሰዎች ናቸው? አስተማሪ ወይም መሪ ለመሆን ሁለት መስፈርቶች አሉ። የመጀመሪያው አስተማሪ ለመሆን አንድ ሰው ከጌታ የተቀበለው ልዩ ስጦታ ሊኖረው ይገባል፤

[5] ፍቅርና መታዘዝ የማይነጣጠሉ ሁልጊዜ አብረው የሚሄዱ ናቸው፤ መታዘዝ ማፍቀር ነው፤ ማፍከርም መታዘዝ ነው (ዮሐ 14፥15)። በተመሳሳይ ሁኔታ እምነትና ሥራ አብረው የሚገለጹ ናቸው፤ አንዱን ከሌላው ነጥሎ መያዝ አይቻልም።

ምክንያቱም አስተማሪዎች ከጌታ ለቤተክርስቲያን የተሰጡ ስጦታ ናቸው (ኤፌ 4፥7፤11–12)። ሁለተኛው አንድ ሰው ከጌታ ልዩ የሆነ ጥሪ ወይም ሹመት ሊኖረው ይገባል (1ቆሮ 9፥16)።

2 ሁላችን በብዙ ሁኔታ እንሰናከላለን፤ ኀጢአትም እንሠራለን፤ ብዙውን ጊዜ ኀጢአት የምንሠራውም በአንደበታችን ነው። ይህ ለአስተማሪዎች ልዩ አደጋ ሊፈጥር ይችላል፤ ምክንያቱም ሥራቸውን የሚሠሩት በመናገር ነውና። ነገር ግን አንደበት ለአስተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኖች በሙሉ አደገኛ ነው፤ ለአብዛኞዎቻችን አያሌ ኀጢአት የምንሠራበት መንገድ አንደበት ነው።

ያዕቆብ አንደበታችንን መቆጣጠር ከቻልን ፍጹማን ሰዎች እንደምንሆን ይናገራል። ንግግራችንን መቆጣጠር ከቻልን መላ ሰውነታችንን መቆጣጠር እንችላለን። ከሰውነታችን ብልቶች ሁሉ ለመቆጣጠር እጅግ አስቸጋሪው አንደበት (ምላስ) ነው። ምላሱን መቆጣጠር የሚችል ሰው ሌሎች ክፉ ምኞቶቹን ሁሉ መቆጣጠር ይችላል።

ሆኖም ማንም ሰው ፍጹም እንዳይደለ እናውቃለን፤ አንዱ ምክንያትም ማንም ሙሉ በሙሉ አንደበቱን መቆጣጠር አይችልምና።

3 አንድ ሰው ትልቅ የሆነውን ፈረስ በትንሿ ልጓም ሊቆጣጠር ይችላል። አንደበታችንን መቆጣጠር ከቻልን መላ ሰውነታችንን መቆጣጠር እንችላለን ማለት ነው።

4 አንደበታችን ልክ በአንድ ትልቅ መርከብ እንዳለች ትንሽ *መሪ* ነው። የመርከብ መሪ መጠኗ አነስተኛ ቢሆንም ከመረከቡ በስተኋላ ሆና የመርከቡን የጉዞ አቅጣጫ ትመራለች። እንዲሁም ምላሳችን የሰውነታችን አነስተኛዋ ክፍል ሆና ትልቅ ውጤት ታመጣለች።

5 ምላሳችን እንደ ትንሽ *እሳት* ወይም እንደ ክብሪት ናት። ትንሿ እሳት አገር የሚያህል ጫካ ታቃጥላለች። ከእነዚህ ሦስት ምሳሌዎች ማለትም ከልጓም፣ ከመሪና ከእሳት እንደምንረዳው ምላስ በሰውነታችን ዋና ብልት ናት። ትንሽ ሐሜት ቤተክርስቲያንን ትከፋፍላለች፤ ለመሪዎችም ውርደት ታመጣለች። ጥቂት የስህተት ትምህርት ብዙዎችን ወደ ስህተት ትመራለች።

6 አንደበት እንደ እሳት ነው። ሰይጣንም ከሰውነታችን ክፍሎች በይበልጥ የሚጠቀመው ምላስን ነው። ምላሳችን (አንደበታችን) በገሀነመ እሳት እንደተለኮሰ ነች፤ ማለትም ሰይጣን አንደበታችንን በእሳት ይለኩሳል ምላሳችንን ካልተቆጣጠርን ሁለንተናችንን ያረክሳል፤ የሕይወት አቅጣጫችንን ያቃጥላል፤ ወደ ጥፋትም ይመራናል። በክርስቲያኖች መካከል ምላስ እጅግ ክፉ የሆነውን ነገር ይሠራል። አንድ ክርስቲያን ለጌታ የተሰጠና *ፈሪሃ* እግዚአብሔር ባለው መንገድ እየሄደ አንደበቱን የማይቆጣጠር ከሆነ፣ ይህ አካሄዱ ሕይወቱን ያበላሸዋል። በክርስቲያኖች መካከል ያለ የተለመደ ኀጢአት በአንደበት የሚሠራ ነው።

7–8 . . . *ምላስን ሊገራ የሚችል ማንም የለም* (ቁ 8)። *ታዲያ* እንዲህ ከሆነ የሚረዳን የለንማ? በእርግጥ እግዚአብሔር አንደበታችንን እንድንቆጣጠር ይረዳናል። ነገር ግን በዚህ ሕይወት በፍጹምነት አንደበታችንን መቆጣጠር እንችላለን ብለን አናስብም።

ምላሳችን *ዕረፍት የሌላት ክፉ ነገር ናት*፤ ሁልጊዜ ክፉ የሆነውን ለመናገር ሁኔታዎችን ትፈልጋለች፤ *የሚገድል መርዝ የምላባት ነች*። አንዳንድ የመርዝ ዓይነቶች በመጀመሪያ ሲቀመሱ ምንነታቸው አይታወቅም፤ ሌሎች ደግሞ ጣፋጭ ናቸው። መርዝ የሚገድለው ከተዋጠ ወይም ከተጠጣ በኋላ ነው። ምላሳችንም እንደዚህ ነው (መዝ 140፥3)።

9–10 ብዙ ሰዎች ክርስቲያኖችንም ጨምሮ ባለ «ሁለት ምላስ» ናቸው። በጸሎት ስብሰባ ላይ የሚጣፍጡ ቃላትን በመጠቀም እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ይሰማሉ፤ ከዚያ ስፍራ ሲወጡ ግን ስለ ወንድሞቻቸው ክፉ ወሬ ያወራሉ። *ከአንድ አፍ ምስጋናና እርግማን ይወጣሉ፤ ወንድሞች ሆይ! ይህ ሊሆን አይገባም*።

11–12 በዚህ ቍጥር ላይ ያዕቆብ ከተፈጥሮ ምሳሌ በመውሰድ ባለ «ሁለት ምላስ» መሆን እንደማይቻል ያብራራል። መልካም መዓዛ ያለው የሚመስል የባለ «ሁለት ምላስ» ጸሎተኞች ጸሎት ልክ እንደሚጣፍጥ መርዝ ነው። ለእግዚአብሔር ጆሮ የሚጣፍጡ ስላይደሉ አይሰማቸውም (መዝ 66፥18)። ባለ «ሁለት ምላስ» ሰው መርዝ የተሞላ ምላስ እንዳለው ሰው ነው።

በተፈጥሮ ከአንድ ምንጭ የሚወጣ ውሃ ጣዕሙ አንድ ዓይነት ነው። ከንጹሕ ምንጭ ንጹህ ውሃ፣ ከጨዋማ ምንጭ ጨው ጨው የሚል ውሃ ይገኛል። እንዲሁም ከአንድ ዛፍ አንድ ዓይነት ፍሬ ይገኛል። ከበለስ ዛፍ የበለስ ፍሬ፣ ከወይን ተክል ደግሞ ወይን ይገኛል። የምንጭን ጣዕም በሚያመነጨው ውሃ፣ ዛፍን ደግሞ በሚያፈራው ፍሬ መለየት እንችላለን።

በተመሳሳይ መንገድ ሰዎችን በንግግራቸው ልናውቃቸው እንችላለን። የአንድ ሰው ንግግሩ ክፉና መራራ ከሆነ፣ ልቡም እንዲሁ ነው። ክፉ ሰው የሚጣፍጡ ቃላትን በመናገር ሊያታልል ቢችልም ማንነቱ ከጊዜ በኋላ በሚናገራቸው ክፉ ቃላት መታወቁ አይቀርም።

ማንም ሰው ራሱን አያታልል፤ ስለ ወንድሙ ክፉ ነገር እየተናገረ በጣፋጭ ቃላት የሚጸልየውን ሰው ጸሎት እግዚአብሔር አይቀበልም። እንዲህ ያሉ ጸሎቶች የውሸት እንደሆኑ እግዚአብሔር ያውቃል። *«እግዚአብሔርን እወዳለሁ» እያለ ወንድሙን የሚጠላ ሐሰተኛ ነው* (1ዮሐ 4፥20–21)።

ሁለት ዓይነት ጥበብ (3፥13–18)

13 ጥበበኞችና አስተዋዮች ነን ካልን ይህን እናረጋግጥ። ፍቅር ካለን ይህን ፍቅር እናሳይ። እምነት ካለንም ይህንኑ እናሳይ። *ታዲያ* እንዴት ልናሳይ እንችላለን? *በመልካም አኗኗርና* በተግባር ማሳየት ይቻላል። የምንሰብከው፣ የምናስተምረው እንዲሁም የምንሠራው ማንኛውም *ሥራ በጥበብና በማስተዋል* መሆን አለበት። ሁለት ዓይነት ጥበባት አሉ። የእግዚአብሔር ጥበብ (ሰማያዊ ጥበብና) የሰው ጥበብ (ምድራዊ ጥበብ)። የእግዚአብሔር ጥበብ ሁልጊዜ ወደ ትሕትና ሲመራ የሰው ጥበብ ግን ወደ ትዕቢት ይመራል፤ ማለትም *ወደ መራራ ቅንአትና ራስ ወዳድነት* ይመራል (ቁ 14)።

14 ምድራዊ ጥበብን የተሞላ ሰው ለእግዚአብሔር የሠራ መስሎት ሊታበይ ይችላል፤ ነገር ግን እርሱ የሠራው ለራሱ ጥቅም የሆነውን ነው። እንዲህ ያለ ሰው ለእግዚአብሔር በሠራው ሊታበይ አይገባውም። እንዲህ ካደረገ ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትንም ይክዳል።

15 የምንጭ ውሃን በመቅመስ ስለምንጩ ምንነት መናገር እንደምንችለው፣ አንድ ሰውም የትኛው ዓይነት ጥበብ እንዳለው በማየት ማወቅ እንችላለን። የሰማያዊው ጥበብ ፍሬ ትሕትና ነው። የምድራዊው ወይም ተፈጥሮአዊው ጥበብ ግን ቅንአትና ራስ ወዳድነት ነው። ምድራዊው ጥበብ *የዚህ ዓለም ገዢ* ከሆነው *ከዲያቢሎስ* ማለትም *ከሰይጣን* ነው (ዮሐ 16፥11)።

16 በቤተክርስቲያን ውስጥ መለያየትና በወንድሞች መካከል ጥል የሚፈጥረው ምክንያት ምንድን ነው? ዋናው ምክንያት *ቅንአትና ራስ ወዳድነት* ነው (ቁ 14)። ይህ ደግሞ በሰፊው ምእመናን ላይ ብቻ ሳይሆን በመሪዎችም ዘንድ የሚከሰት ነው። እያንዳንዱ አማኝ ራሱን ይመርምር!

17 ከሰማይ የሚመጣው ጥበብ የእግዚአብሔር ነው። እንዲህ ያለውን ጥበብ ለማግኘት እግዚአብሔርን እንጠይቅ (ያዕ 1፥5)።

ከእግዚአብሔር የሚገኘው ጥበብ ምን ይመስላል? እንዴትስ ልናውቀው እንችላለን? በመጀመሪያ *ንጹሕ* ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ንጹሕ ስለሆነ።

ሁለተኛ የእግዚአብሔር ጥበብ ሰላም ወዳድ ነው። ጥበበኛ ሰው ሁከት አይፈጥርም። ጥበበኛ ሰው ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገር ደግሞ የዘገየ ነው (ያዕ 1፥19)። ሁልጊዜ ወደ ሰላም የሚመራውን ለማድረግ ይጥራል (ሮሜ 14፥19)። ጥበበኛ ሰው *ደግና* ስለሌላው የሚያስብ ነው። ስለ ሌሎች ግድ ይለዋል፤ ሰዎችን የሚያሳዝንና ስሜታቸውን የሚጎዳ ንግግር አይናገርም። ጥበበኛ ያልሆኑ ሰዎች ተከራክረው መርታታቸውን እንጂ ለአነጋገራቸው ግድ የላቸውም። እነዚህ

ሰዎች በክርክሩ ሊያሸንፉ ይችላሉ፤ ነገር ግን ወደጆቻቸውን ከንግግራቸው የተነሣ ያጣሉ። ጥበበኛ ሰው እንዲህ ያለውን አያደርግም።

ጥበበኛ ሰው *ታዛዥ* ነው። ለሌሎች ታዛዥ ሆኖ ለመኖር ፈቃደኛ ነው (ኤፌ 5፥21)፤ በሌሎች ሰዎች ላይ የበላይ የመሆን ፍላጎት የለውም፤ እንዲያውም ሐሳባቸውንና ፍላጎታቸውን ያከብራል።

ጥበበኛ ሰው *ምሕረት* አድራጊ ነው። በሌሎች ላይ አይፈርድም። ሁልጊዜ ይቅርታ ለማድረግ የተዘጋጀ ልብ አለው፤ ለመበቀል በፍጹም አይሞክርም።

ጥበበኛ ሰው *ጥሩ ፍሬ የሞላበት* ነው፤ ይህም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው (ገላ 5፥22–23)። አድልዎ የሚያደርግ ልብ ስለሌለው ሁሉንም በእኩል ዓይን ይመለከታል።

በመጨረሻም ጥበበኛ ሰው *ግብዝነት የሌለበት* ነው። ሊታመን የሚችልና ለራሱ ጥቅም ሲል ሌሎችን ለማታለል የሚሞክር አይደለም። ሁልጊዜ እውነትን በፍቅር ይናገራል (ኤፌ 4፥15)።

ጥበባችንና ንግግራችን እውነተኛ ነውን? ይህ ጥያቄ ክብደት ያለው ነው። አንዳንድ ጊዜ እርስ በርሳችን በምናወራው ወሬ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ታማኝነትና ግልጽነት ያለው ንግግር አይኖረንም። ስለ አንዳንድ ጉዳዮች እውነቱን ደብቀን እናወራለን። የምንናገረው ጣፋጭ ቢመስልም በልባችን ያለው ሐሳብ ግን መራራ ነው። በእርግጥ ፊት ለፊት ውሸት ባንናገርም፣ ኀጢአት እንደ ሆነ ሁላችን እናውቃለን። ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ለማስተላለፍ ብለን እውነትን እንሸሽጋለን። ነገር ግን ጥበበኛ ሰው ሁልጊዜ እውነተኛ ነው፤ ሁልጊዜ በቅንነትና በታማኝነት ይናገራል።

18 በዚህ ቍጥር የተጠቀሱት *ሰላም ወዳድ ሰዎች* ጥበበኞች፣ ከእግዚአብሔር ጥበብን የተቀበሉ ሰዎች ናቸው። የጽድቅን ዘር ዘርተው *የጽድቅን ፍሬ ይሰበስባሉ* (ገላ 6፥7 ይመለከቷል)። ሰላም ወዳድ ሰዎች አንደበታቸውን መግታት ተምረዋል።

ምዕራፍ 4

ለእግዚአብሔር መገዛት (4፥1–10)

1 በቤተክርስቲያን ውስጥ *ጦርነትና ጠብ* የሚፈጠሩት በምን ምክንያት ነው? ለዚህ ምክንያት የእኛ *ምኞቶች* ናቸው። ክፉ ምኞቶች ኀጢአት ወደ ማድረግ የሚመሩ እንደሆኑ ይታወቃሉ። እዚህ በታ ላይ ግን ያዕቆብ ስለ እነዚህ ምኞቶች ብቻ ሳይሆን ስለ ስግብግብ ምኞቶችም ይናገራል። ስግብግብ ምኞት መልካም ነገርን መመኘት ቢሆንም ምኞቱ ለራስ ብቻ ነው። ለምሳሌ የትምህርት፣ የሥራ ዕድል ወይም የመሳሰሉ መልካም ምኞቶች ቢኖሩም እነዚህም ለራስ ፍላጎት ብቻ መመኘት ይቻላል።

ለእነዚህ ነገሮች ያለን ምኞት በአብዛኛው ለምን ወደ ጠብና ቅንአት ይመራናል? ምክንያቱ ለግላችን ወይም ለራሳችን ብቻ ስለምንመኛቸው ነው። ለእነዚህ ነገሮች ያለን ምኞት የእኛን ነገር ብቻ ለማሟላት እንጂ እግዚአብሔርን ወይም ሌሎችን ለመጥቀም አይደለም። ይህ ስግብግብነት ነው። ታዲያ ለመልካም ነገሮች ይሁን ወይም ለክፉ፣ ሥጋዊ ምኞት ኀጢአት ነው። እነዚህ ራስ ወዳድነት የሞላባቸው ምኞቶች በክርስቲያኖች መካከል ጠብና ጦርነት እንዲከሰቱ ምክንያቶች ናቸው (1ጴጥ 2፥11)።

እርስ . በርስቸው የሚጣሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን የሚያደርጉት ለእግዚአብሔር ብለው እንደሆነ ይናገራሉ። የሰው ልጆች ታሪክን ስንመለከት አያሌ ክፉ ድርጊቶች የተፈጸሙት በእግዚአብሔር ስም ነው። ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን፣ ሰዎች እግዚአብሔርን ያገለገሉ እየመሰላቸው ስደትና መከራ እንደሚያመጡባቸው አስጠንቅቋቸው ነበር (ዮሐ 16፥2)። ራሳችንን አናታልል። የምንዋጋው ከሰይጣን ጋር እንጂ ከሌሎች አማኝ ክርስቲያኖች ጋር አይደለም። በአማኞች መካከል ያለ ጠብ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አይደለም። እንዲህ ያለው ባሕርይ ለእግዚአብሔር ሲባል ሳይሆን ለራስ ጥቅም ሲባል የሚገለጥ ነው።

2 በዚህ ምድር ሕይወት ማንም ሰው የፈለገውን ሁሉ ሊያገኝ አይችልም። ስለዚህ ሰዎች ተጨማሪ ነገሮችን ለማግኘት ይስገበገባሉ። አንድ ስጦታ እንደተቀበልን ወይም አንዳንድ ምኞቶች እንደ ተሟሉ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን ለመያዝ መሯሯጥ እንጀምራለን። ስለዚህም እርካታን አናገኝም።

ሁልጊዜ የምንፈልገውን ለማግኘት ከመሯሯጥ፣ የሚያስፈልገንን እንዲሰጠን እግዚአብሔርን መጠየቅ ይሻላል። እርሱ የሚያስፈልገንን ሁሉ ያውቃል፤ ስለዚህም በወቅቱ ይሰጠናል። አንድ መልካም ነገርን ከተመኘን ያንን ለራሳችን ጥቅም በማለት ለመያዝ እንፍጨረጨር፤ ይልቁኑ ስለዚያ ነገር እግዚአብሔርን በማመን እንጠይቀው።

3 አንዳንድ ሰዎች «እግዚአብሔርን ጠይቄው ነበር፤ እርሱ ግን የጠየቅሁትን አልሰጠኝም» ይላሉ። እነዚህ ሰዎች የጠየቁትን ያላገኙት ለምንድን ነው? ምክንያቱ በተሳሳተና *በክፉ አሳብ* ስለለመኑ ነው። ማለትም በራስ ወዳድነት ለራሳቸው ደስታና ጥጋብ ስለለመኑ ነው። በሥራቸው መሳካትና መከናወን እንዲሆንላቸው እግዚአብሔርን የለመኑት ለእርሱ ክብር ወይም ለሌሎች በረከት ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም ነው።

እግዚአብሔርን ስለ ማንኛውም ነገር ስንለምነው፣ ኢየሱስ እንዳደረገው እኛም ልናደርግ ይገባናል። «ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን» (ማር 14፥36)። ይህን ልመና ለእግዚአብሔር የማቀርበው ማንን ለመጥቀም ነው? ስለ ራሴ ብዬ ነው ወይስ ስለ እርሱ? የሚል ጥያቄ በማቅረብ ራሳችንን መመርመር ይገባናል። እግዚአብሔር የሚሰጠን ማንኛውም ነገር እርሱንና ሌሎችንም ለማገልገል እንደምናውለው ከልብ መናገር ይኖርብናል። ይህ ከባድ ነገር ቢሆንም ኢየሱስ የተወልን ምሳሌ ይኸው ነው። ከእግዚአብሔር መቀበል ከፈለግን በራስ ወዳድነት በፊቱ ልንቀርብና ልንጠይቀው አይገባንም። እርሱ ልባችንን ስለሚያውቅ ልናታልለው አንችልም። የጠየቅነው ጥያቄ በራስ ወዳድነት መሆን አለመሆኑን ጠንቅቆ እንደሚያውቅ መዘንጋት የለብንም።

4 *እናንተ ከዳተኞች!* ያዕቆብ እንዲህ ብሎ የሚናገረው አማኞችን ነው። *ከዳተኞች* ብሎ የጠራቸው ለምንድን ነው? ምክንያቱ ክርስቶስን ትተው ዓለምን ስለ ወደዱ ነው። ከክርስቶስ ይልቅ የዓለምን ደስታ ወደዱ (2ቆሮ 11፥2–3፤ ኤፌ 5፥23)። በአንድ ጊዜ እግዚአብሔርንና ዓለምን መውደድ አይቻልም (ማቴ 6፥24፤ 1ዮሐ 2፥15)።

5 . . . *በውስጣችሁ ያሳደረው መንፈስ ለእርሱ ብቻ እንድንሆን በብርቱ ይመኛል።*[6] እግዚአብሔር (ክርስቶስ) እንደ ታማኝና ናፋቂ ሙሽራ፣ እኛ ደግሞ እንደ ታጩ ሙሽሪት ሆነን ቀርበናል። እኛ ግን ብዙ ጊዜ ታማኞች ሆነን አልተገኘንም። ታማኝ የሆነውን ባል ትተን እንደ ሥጋዊ ምኞትና ገንዘብን የመሳሰሉ ወደ ሌሎች ጣዖታት ሄድን። እግዚአብሔር ደግሞ በዚህ ጉዳይ ቀናተኛ ነው (ዘፀ 20፥4–5)።

6 ምንም እንኳ ከእግዚአብሔር ብንርቅም እርሱ በጸጋውና በምሕረቱ ጥሪውን ወደ እኛ ያቀርባል። ኀጢአታችን የቱንም ያህል የበዛ ቢሆንም የእርሱ ጸጋ ወሰን የለውም። ወደ እርሱ እንድንመለስና እንደገና እንድንወደው *ጸጋን አብዝቶ ይሰጠናል*።

ሆኖም እግዚአብሔር ጸጋን *ትሑት* ለሆነ እንጂ ለሁሉ አይሰጥም። ያዕቆብ በዚህ ቦታ ከመጽሐፈ ምሳሌ 3፥34 ይጠቅሳል (1ጴጥ 5፥5 ይመልከቱ)። *እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል*። ስለዚህ ትዕቢተኞች ሊጠነቀቁ

---

[6] ይህ ክፍል በተለያዩ ትርጉሞች የተለያዩ ሐሳቦች ስላሉ ትክክለኛው ፍቺ አይታወቅም። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው *መንፈስ*፣ መንፈስ ቅዱስን ለማመልከት ይሁን ወይም የሰውን መንፈስ በትክክል አይታወቅም። ምንም ይሁን ምን አጠቃላይ ሐሳቡን ስንመለከት እግዚአብሔርን ትተን ዓለምን መውደድ ስንጀምር እግዚአብሔር በእኛ እንደሚቀናና እንደሚቆጣ የሚናገር ክፍል ነው።

ይገባቸዋል። ኀይለኛ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት እጅግ የሚያስፈራ ነገር ነው።

7 ከዓለምና በዓለም ካለው ተድላ ተመልሰን ለእግዚአብሔር መገዛት፤ ከዚህም ጋር ሰይጣንን መቃወም አለብን። ሰይጣን ሁልጊዜ የዓለምን ተድላ በማሳየትና በማታለል ከእግዚአብሔር እንድንርቅ ይጥራል። ስለዚህ እርሱን እንዲሁም ወደ እኛ የሚልካቸውን ፈተናዎች መቋቋምና መቃወም ይገባናል (1ጴጥ 5፡8–9)።

ብዙ ሰዎች፤ «ሰይጣንን እንዴት ልቋቋመው እችላለሁ? እንዴትስ ማሸነፍ እችላለሁ? ፈተና ወደ እኔ ሲመጣ የቱንም ያህል ልቋቋመው ብሞክር ወዲያው እውድቃለሁ» ይላሉ (ሮሜ 7፡15፤18–19)።

ዲያቢሎስን እንዴት መቃወም እንችላለን? እርሱን የምንቃወመው በክርስቶስ ኀይል ነው። ልናስተውለው የሚገባን የመጀመሪያ ነገር የዲያቢሎስን ፍላጎት ስንከተል ጌታችንን ኢየሱስን እንከደዋለን። ሁለተኛው ነገር በክርስቶስ ኀይል መበርታት ነው (ኤፌ 6፡10–11፤13)። የክርስቶስ ኀይል ሁልጊዜ በአጠገባችን ነው። ዋናው ነገር ግን በዚህ ኀይል ለመጠቀም ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል።

ስለዚህ ሰይጣን ሲፈትነን «ወዲያ ሂድ አንተ ሰይጣን» ማለት ነው (ማቴ 4፡10)።

8 እግዚአብሔር ወደ እኛ እንዲቀርብ እንፈልጋለን? ከፈለግን እኛ ወደ እርሱ መቅረብ አለብን። እግዚአብሔር ከእኛ የራቀ ከመሰለን፤ ምክንያቱ ሁልጊዜ መጀመሪያ እኛ ከእርሱ መራቃችን ነው። ከእግዚአብሔር ለምን እንርቃለን? ለዚህ ምክንያቱ መተው ያልፈለግነው ኀጢአት በእኛ ውስጥ ስላለ ነው።

ወደ እግዚአብሔር እንዴት መቅረብ እንችላለን? ለዚህ ያዕቆብ የሚሰጠው መልስ፤ እናንተ ኀጢአተኞች እጃችሁን አጽዱ በማለት ነው። ይህ ማለት ራሳችንን ከየትኛውም የኀጢአት ሥራና ባሕርይ ማንጻት ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ያዕቆብ እናንተ ወላዋዮች ልባችሁን አጥሩ ይላል። ውጪያዊ ከሆኑ ኀጢአቶች ብቻ ሳይሆን ስውር ከሆነው ለሰው ከማይታየው የልብ ኀጢአት ራሳችንን ማንጻት አለብን። እግዚአብሔር በልባችንና በሐሳባችን ያለውን ሁሉ ይመረምራል (1ዜና 28፡9)። ወላዋይ መሆን አለመሆናችንን ያውቃል። ወላዋይ ሰው እግዚአብሔርና ዓለምን በአንድ ላይ ለመውደድ ይሞክራል። ስለዚህ እንዲህ ያለ ሰው ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ንጹሕ አይደለም፤ ልቡም ቅዱስ አይደለም፤ በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም። በንጹሕ እጅና ልብ ብቻ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይቻላል (መዝ 24፡3–4፤ ማቴ 5፡8፤ ዕብ 12፡14)።

ልባችን እንዴት ሊጸዳ ይችላል? ኀጢአታችንን መናዘዝና ኀጢአትን ከመሥራት በመመለስ በንስሐም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለብን። ራሳችንን በትሕትና ዝቅ ስናደርግ እርሱ ጸጋን ይሰጠናል (ቊ 6)፤ ወደ እኛም ይቀርባል። እንደ እኛ ላሉ ኀጢአተኞች ምሕረቱን ስለሚያደርግ እናመስግነው።

9 ጳውሎስ ደስ ይበላችሁ! (ፊል 4፡4)፤ ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ! ይላል (1ተሰ 5፡16) ይላል። ያዕቆብ ግን በዚህ ቁጥር ተጨነቁ፤ እዘኑ፤ አልቅሱ ይላል። ለምን እንጨነቃለን፤ እናዝናለን፤ እናለቅሳለን? እንዲህ የምንሆነው በኀጢአታችን ምክንያት ነው። እዚህ ሁለት እውነቶች አሉ፤ ጳውሎስ እግዚአብሔር በጣም ስለሚወደን «ደስ ይበላችሁ» ይላል። ያዕቆብ ደግሞ እኛ እግዚአብሔርን በጣም በጥቂቱ ስለምንወደው «ተጨነቁ» ይላል። በእግዚአብሔር በጎነትና ጸጋ ደስ ሊለን ይገባል። በኀጢአታችንና ባለ መቀደሳችን ልናዝን ይገባናል። የሚያዝኑ ቡሩካን ናቸው ይላል ኢየሱስ። በኀጢአታቸው ተጸጽተው የሚያዝኑ የተባረኩ ናቸው (ማቴ 5፡4)።

10 ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን በትሕትና እናቅርብ። . . . አምላክ ሆይ! ትሑት የሆነውንና ለንስሐ የተዘጋጀውን ልብ አትንቅም (መዝ 51፡17)። ትሑት ስንሆን እግዚአብሔር ወደ እኛ ይቀርባል። እርሱ ጸጋን ይሰጠናል (ቊጥር 6)፤ ከፍ ያደርገናል (ማቴ 5፡3፤ ሉቃ 18፡9–14፤ 1ጴጥ 5፡6)።

ስለ ሐሜት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (4፡11–17)

11 ያዕቆብ ስለ ክፉው አንደበታችን (ያዕ 3፡8)፤ በወንድሞች መካከል ስላለው ጠብና ጦርነት ሲናገር ቆይቷል (ቊ 1)። አሁን ደግሞ ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማሙ ይላል። ሐሜት ምንድን ነው? ሐሜት የወንድማችንን ስህተትና ድካም ለሌላ ሰው መግለጥ ነው። እያንዳንዱ ሰው ከስህተትና ድካም የራቀ ስላልሆነ ሐሜትን ከሞላ ጎደል ወይም በከፊል እውነትነት ያለው ነገር በመጨመር ይቀርባል። ሐሜት ውሸት ከሆነ ሐሰተኛ ምስክርነት ይሆናል። ነገር ግን እውነትም ሆነ ሐሰት ስለ ወንድማችን ስህተትና ድካም ለሌሎች ካወራን ሐሜት ነው፤ ሐሜት ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ኀጢአት ነው።

ወንድማችንን ማማትና በእርሱ ላይ መፍረድ ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው። በልባችን በወንድማችን ላይ እንፈርዳለን፤ በአንደበታችን ደግሞ ወንድማችንን እናማለን (ማቴ 7፡1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ)።

በወንድማችን ላይ ስንፈርድ የክርስቶስ ሕግ በሆነው ላይ እንፈርዳለን። በሕግ ላይ «መፍረድ» ማለት ሕግን አለመታዘዝ ነው። ይህ ካደረግን ራሳችንን ከሕግ በላይ አስቀመጥን ማለት ነው። ሕግን ስናማ አንዳንድ ትእዛዛት ትክክል ሌሎች ደግሞ የተሳሳቱ ናቸው ማለታችን ነው። ስለዚህ «ይህን ሕግ እፈጽማለሁ፤ ሌላውን ግን አልፈጽምም» ማለት ነው። «ወንድሜን ማማት ወይም በእርሱ ላይ መፍረድ ከፈለግሁ አደርገዋለሁ» ማለታችን ነው። በዚህን ጊዜ ራሳችንን በሕግ ላይ ፈራጆች አድርገን እናስቀምጣለን።

12 ነገር ግን ሕግ የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በሕግ ላይ ስንፈርድ ራሳችንን በእግዚአብሔር ስፍራ እናስቀምጣለን። ይህ ደግሞ እጅግ የከፋ ኀጢአት ነው። እንደ እግዚአብሔር ለመሆን መፈለግ፤ የትዕቢት ከፍተኛው ደረጃ ነው። አዳምና ሔዋን ከኤደን የተባረሩበት ኀጢአት ይህ ነበር (ዘፍ 3፡5–6)። ራሳችንን በትሕትና ዝቅ ማድረግ ሲገባን (ቊጥር 10)፤ አንድ ጌታና አንድ ፈራጅ እያለ ራሳችንን ጌታና ፈራጅ እናደርጋለን። ይህ እንዴት ያለ ትልቅ ስህተት ነው! እንዴትስ የከፋ ኀጢአት ነው! ሊያጠፋና ሊያድን የሚችል አንድ ብቻ አለ፤ እርሱም እግዚአብሔር ራሱ ነው። ለሰዎች ደኅንነትን ሊሰጥ ወይም ወደ ሲኦል እንዲወርዱ ሊፈርድ የሚችል እርሱ ብቻ ነው። የቱንም ያህል ራሳችንን ከፍ ብናደርግ ራሳችንን ልናድን አንችልም። ምንም ያህል በወንድማችን ላይ ብንፈርድ ልናጠፋው ወይም ልንኮንነው አንችልም። ሊያድንና ሊኮንን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ በክርስቲያን ወንድማችን ላይ ለመፍረድ መሞከር የለብንም። እንዲያውም ክርስቲያን ባልሆነ ሰው ላይ እንኳ ለመፍረድ መሞከር የለብንም።

13–15 ያዕቆብ ንግግሩን ሌላ ርእስ ጉዳይ በማንሣት ወደፊት ስላለው ሁኔታ ይናገራል። ያዕቆብ በዚህ ቦታ ስለ ወደፊት ነገር ማቀድ አያስፈልግም ብሏልን? በፍጹም አላለም። ወደፊት ልናደርጋቸው ስላሉት ነገሮች በጥንቃቄ እቅድ ማውጣት ይኖርብናል። ገበሬው ዘሩን ሲዘራ ወደፊት ስለሚሰበስበው መከር መመልከት ይኖርበታል። ጳውሎስና ሌሎቹ ሐዋርያት ወዴት እንደሚሄዱና በሄዱበት ስፍራ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ ያቅዱ ነበር። ነገር ግን እቅድ በምናወጣበት ጊዜ በልባችን «የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ እንዲህና እንዲያ እናደርጋለን» እንበል (የሐዋ 18፡21፤ 1ቆሮ 4፡19)። ሕይወታችን በሙሉ ያለችው በእግዚአብሔር እጅ ነው። ነገ ምን እንደሚሆን አናውቅም። በእርግጠኝነት ወደፊት ስለሚሆነው ማወቅ አንችልም። ሕይወታችን እንደ ጤዛ ነው፤ ዛሬ እዚህ በሕይወት አለን፤ ነገ ግን የለንም። ስለዚህ በእቅዳችን ሳይሆን በማይለወጠው በእግዚአብሔር ላይ እምነታችንን መጣል ይኖርብናል። አዎን፤ እቅድ ልናወጣና ዘር ልንዘራ ይገባናል፤ የሚያሳድግና ለፍሬ የሚያበቃው ግን እግዚአብሔር ነው (1ቆሮ 3፡7)። እቅድ ማውጣትና መሥራት አለብን፤ እንደ ፈቃዱ መከናወንን የሚሰጠን ግን እግዚአብሔር ነው። ልንታመነው የሚገባን እርሱን ብቻ ነው።

16 ስለዚህ በራሳችን ሥራና ስኬት አንታበይ። ትምክህታችን በእግዚአብሔር ብቻ ሊሆን ይገባዋል።

ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋና ለራሳችን ካደረግን፣ በእግዚአብሔር ላይ ኀጢአትን እናደርጋለን። እግዚአብሔር ላደረገው ነገር እኛ ምስጋናውን የምንወስድ ከሆንን እጅግ የከፋ ነገርን አድርገናል!

17 በዚህ ቍጥር ሁለት በጣም አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶች ቀርበዋል። *የመጀመሪያው* እግዚአብሔር የሚፈርድብን በምናውቀው ነገር ላይ ነው። ሕፃን ልጅ ባለማወቅ ሕግ ቢተላለፍ ባለማወቁ አይቀጣም፤ ኀጢአትም አይሆንበትም። ጎልማሳ የሆነው ዐውቆ ሕግን ቢተላለፍ ለእርሱ ትልቅ ኀጢአት ነው። አንድ ሰው ብዙ እያወቀ እግዚአብሔርን ካልታዘዘ ቅጣቱ ትልቅ ይሆናል (ሉቃ 12፥47–48፤ ያዕ 3፥ እና ማብራሪያዎቻቸውን ይመልከቱ)።

ሁለተኛው ትምህርት ኀጢአትን በተመለከተ ነው። ብዙ ሰዎች ኀጢአት ክፉ የሆነ ነገርን *መሥራት* ብቻ እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ያዕቆብ በዚህ ቦታ ማድረግ የሚገባንን አለማድረጋችን ኀጢአት እንደ ሆነ ያስተምረናል። ማድረግ የሚገባንን አለማድረጋችን፣ ማድረግ የማይገባንን ከማድረጋችን ጋር እኩል ኀጢአት ነው። ወንድማችን እርዳታ እየፈለገ ካልረዳን በእርሱ ላይ ኀጢአትን እንሠራለን። እንዲሁ በኢየሱስ ካላመንን በአለማመናችን ኀጢአትን እንሠራለን።

ምዕራፍ 5

ለሀብታሞች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (5፥1–6)

1–3 በዚህ ክፍል ያዕቆብ መልእክቱን በተለይ የሚያስተላልፈው ድሆችን ለሚበድሉ ሀብታሞች ነው። ሀብታም ክርስቲያኖች እነዚህን ቍጥሮች በአንክሮ ሊመለከቷቸው ይገባል።

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ እንደ ነቢይ ይናገራል። ድሆችን በሚጨቁኑ ሀብታሞች ላይ *አሰቃቂ መከራ* ይመጣባቸዋል ይላል። ከዚያም የሀብታሞች ባለጠግነትና ልብስ ተበላሽቷል። በሀብታሞች ላይ የሚመጣው ጥፋት እርግጠኛ በመሆን እንዲያውም እንደ ተፈጸመ አድርጎ ይናገራል[7] በመጨረሻው ቀን ይህ የተበላሸው ሀብት *ይመሰክርባቸዋል*። በሀብታቸው ክርስቶስንና ሌሎችን ማገልገል ሲኖርባቸው እነዚህ ሀብታሞች ባለ ጠግነታቸውን ለራሳቸው አከማችተዋል። ያዕቆብ ይህንን ለመጨረሻ ቀኖች አድርገዋል ይላል። የመጨረሻዎቹ ቀኖች፣ ክርስቶስ በመጀመሪያ ወደ ምድር በሥጋ በመምጣቱና በዳግም መምጣቱ መካከል ያሉት ቀኖች ናቸው። ይህች ምድር የምታልፍበት ጊዜ ቅርብ ነው፤ ሀብታሞችም ያከማቹትን ሀብት አይጠቀሙበትም። የሚያጡት ሀብታቸውን ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውንም ጭምር ነው (ማቴ 6፥19–21፤ ማር 8፥36–37፤ ሉቃ 6፥24፤ 16፥19–31)።

በ70 ዓ.ም. ይህ መልእክት ከተጻፈ ጥቂት ጊዜ በኋላ የሮም ጦር ኀይል የኢየሩሳሌምን ከተማ ደመሰሰ። በዚያ ከተማ የነበሩ አይሁዶች በሙሉ ከሀብታቸው ጋር ጠፍተዋል። በዚህ የያዕቆብ «ትንቢት» ከታሰበው ጊዜ በፊት እውን ሆነ።

4 ያዕቆብ ሀብታም ክርስቲያኖች ከሠራተኞቻቸው ላይ ስለሚሠርቁ ይወቅሳቸዋል። እንዲህ ባለው ኢፍትሐዊነት የተበዳዩ ጩኸት ወደ ሰማይ ይደርሳል። *የመከር ሰብሳቢዎቻችሁንም ጩኸት ጌታ እግዚአብሔር ሰምቶአል*።[8] እግዚአብሔር ይሰማል፤ ኢፍትሐዊነትንም ይበቀላል።

5 ሀብታዎች በምቾትና በደስታ ይኖራሉ። ሰዎች አንድ ከብት ለእርድ ከማቅረባቸው በፊት እንደሚያደልቡ፣ እነዚህ ሀብታሞችም ሰውነታቸውን *ለዕርድ ቀን እንደ ተዘጋጀ* ሰንጋ አወፍረዋል። ይህ «የዕርድ ቀን» በቅርብ ጊዜ የሚመጣው የፍርድ ቀን ነው (ሉቃ 12፥15–21)።

6 ሀብታምና ኀይለኛ የሆኑት ከስግብግብነታቸው የተነሣ ጻድቃንን ገድለዋል። ነቢያትንና ሐዋርያትን ገድለዋል (ማቴ 23፥37)። ያዕቆብ ራሱ በ62 ዓ.ም. ተገድሏል። የሀብታሞች የከፋው ኀጢአታቸው ግን ኢየሱስ ክርስቶስን መግደላቸው ነው (የሐዋ 7፥52)። ያዕቆብ በዚህ ስፍራ የጠቀሳቸው ጻድቃን ሀብታምን የማይቃወሙ ድሆችን፣ ነቢያትን፣ ወ.ዘ.ተ. ወይም ኢየሱስንና አያሌ ጻድቃንን ሊያመለክቱ ይችላሉ። ሀብታሞች ኢየሱስን ለመግደል በሚማከሩበት ጊዜ እንኳ አይቃወማቸውም ነበር (1ጴጥ 2፥23)። በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ራሱ ጨቋኝ የሆኑ ሀብታሞችን ይቃወማቸዋል።

በመከራ ውስጥ መታገሥ (5፥7–12)

7–8 በዚህም ክፍል ውስጥ ያዕቆብ ለአማኞች ይናገራል። *በትዕግሥት ጠብቁ . . . በተስፋ ጽኑ* በማለት ይጽፋል። ታላቅ መከራ በሀብታም አይሁዶች ላይ ብቻ ሳይሆን ያዕቆብ በነበረበት ዘመን ባሉ ክርስቲያኖችም ላይ ይመጣል። የኢየሩሳሌም በቅርብ ጊዜ ውስጥ መፍረስ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊት በኢየሩሳሌም ያሉ አማኞች መከራ ይገጥማቸዋል። በተጨማሪም የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሩቅ አይደለም። ስለዚህ እምነታቸውን እንዳይተውና ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ያበረታታቸዋል (ማር 13፥13፤ ዕብ 3፥6፤14፤10፥36 ይመልከቱ)።

እኛ በራሳችን ኃይል በተስፋ መጽናትና በትዕግሥት መጠበቅ አንችልም። እግዚአብሔር ግን በቅዱስ መንፈሱ ሊረዳን ዝግጁ ነው። ትዕግሥት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው (ገላ 5፥22)። እግዚአብሔር ራሱ *ፍጹሞች ያደርገናል፤ ያጸናናል፤ ያበረታናል* (1ጴጥ 5፥10)።

ገበሬ ዝናብ እስኪዘንብለት ይጠብቃል። በእስራኤል አገር ዝናብ የምዘንብባቸው ወቅቶች መፀውና ጸደይ ናቸው። የመፀው ዝናብ «የመጀመሪያው ዝናብ» ሲባል የጸደዩ ደግሞ «ኋለኛው ዝናብ» ይባላል። ከመጀመሪያው ዝናብ በኋላ ገብሬው መሬቱን ያርሳል፤ ከኋለኛው ዝናብ በኋላ መከር ለመሰብሰብ ይዘጋጃል። ገበሬው ዝናብ እስኪመጣ በትዕግሥት እንደሚጠብቅ፣ አማኞችም የኢየሱስን ዳግም ምጽአት በትዕግሥት መጠበቅ አለባቸው። ገበሬው ምድራዊና ኀላፊ የሆነ መከር ለመሰብሰብ በትዕግሥት ከጠበቀ፣ እኛማ በሰማይ የተጠበቀልንን ውርስ ለማግኘት በትዕግሥት መጠበቅ እንዴት ያቅተናል?

9 በዚህ ቍጥር ላይም እንደገና ያዕቆብ ክርስቲያኖች እርስ በርስ እንዳይፈራረዱ ያስጠንቅቃል። እርስ በርሳችሁ አትጨቃጨቁ ሲል ጽፎአል።

ፈተኞዎችና ልዩ ልዩ መከራ ሲመጣብን እርስ በርስ ለመካሰስ እንዴት እንቸኩላለን! በምድረ በዳ የነበሩት እስራኤላውያን በሙሴና አሮን ላይ እንደጉረመረሙ እኛም እርስ በርስ እንዲያውም በመሪዎቻችን ላይ እናጉረመርማለን (ዘፀ 16፥1–3፤17፥1–4)። ይህ ሊሆን አይገባም!

እምነታችንን ለመፈተን ወደ ሕይወታችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ፈተና ይመጣል (ያዕ 1፥2–3)። በእነዚህ የፈተና ወቅቶች እንዴት እንደምንቆም እግዚአብሔር ያሳየናል። በፈተና ጊዜ በሌሎች ላይ የምናጉረመርም ከሆነ፣ በእርግጥ በእግዚአብሔር ላይ እያጉረመረምን ነው (ዘፀ 16፥8)። እርሱም ይፈርድብናል። ልንጠነቀቅ ይገባናል! ያለበለዚያ እስራኤላውያንን በምድረ በዳ እንደቀጣ እኛንም ይቀጣናል (ዘኍ 11፥1፤ 14፥1–4፤26–29)። ፈራጅ (ክርስቶስ) በደጅ ቆሞአል (ራዕ 3፥20)። እርሱ ስናጉረመርም ይሰማል። ኢየሱስ ለፍርድ ወደ ምድር ለመምጣት ተዘጋጅቶአል፤ የሚፈርደውም በማያምኑት ላይ ብቻ ሳይሆን በሚያምኑትም ላይ ነው (1ጴጥ 4፥17)።

10–11 እስከ *መጨረሻ* የጸኑት *የተባረኩ* ተብለው ተቆጥረዋል (ያዕ 1፥4)። ያዕቆብ ከብሉይ ኪዳን ታሪክ በዘመኑ የታወቀውን ኢዮብን በምሳሌነት ያቀርባል። እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ከባድ ፈተና እንዲደርስበት በመፍቀዱ ፈተነው። ኢዮብ ያለውን ሀብት አጣ፤ በኋላም ጤንነቱ ተወሰደበት። በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ

---

[7] ጳውሎስም ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን አሁን እንደተፈጸሙ አድርጎ ጽፎአል (ሮሜ 8፥30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ)።

[8] አንዳንድ ትርጉሞች *ጌታ እግዚአብሔር* በሚለው ሐረግ ምትክ «የሰራዊት ጌታ» በሚለው ቀይረዋል፤ የሁለቱም ትርጉም ተመሳሳይ ነው። «ሰራዊት» የሚለው ቃል አያሌ መላእክትን ያመለክታል።

አላጉረመረመም። በመጨረሻም እግዚአብሔር ኢዮብን ባረከው፤ በፊት ከነበረው ሀብት ይልቅ የሚበልጥ የበለጠ ሆነለት። ይህ ሁሉ የሆነው ከመጀመሪያ አንስቶ የእግዚአብሔር እቅድ ነበር (ኢዮብ 1፥1–22፤ 2፥1–10፤ 42፥12–17)።

እግዚአብሔር በሕይወታችን መከራና ችግር እንዲመጣ የሚፈቅደው ለእኛ ጥቅም ነው። በመጨረሻ ከምሕረቱና ከፍቅሩ የተነሣ ስቃያችንንና ሕመማችንን ወደ ደስታና በረከት ይለውጠዋል (መዝ 103፥8፤ ኢሳ 61፥1–3፤7) ኑ! ወደ እግዚአብሔር እንመለስ! እርሱ እንደ ሰበረን እርሱ ይፈውሰናል፤ እርሱ እንደቆሰለን እርሱ ቁስላችንን ይጠግናል፤ . . . ያስነሣናል፤ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን (ሆሴዕ 6፥1–3)።

12 . . . *ኦትማሉ።* ያዕቆብ በዚህ ቦታ የሚናገረው በማንኛውም ተራ ንግግር ስለ መማል ነው። በግልጽ እውነተኛ የሆነውን ነገር መናገር አለብን። *ንግግራችሁ አዎ ከሆነ በእውነት አዎ ይሁን፤ አይደለም ከሆነም በእውነት አይደለም ይሁን።* የምንናገረው እውነት ሊሆን ይገባዋል። እውነትን የሚናገር ሰው የተናገረው ነገር እውነት ስለ መሆኑ መማል አያስፈልገውም። እንዲህ ያለው መሐላ ዋጋ የለውም። ከዚህም የባሰው ነገር ስንምል የጌታን ስም በከንቱ መጥራታችን ነው (ማቴ 5፥34–37)። ማስተዋል የሚገባን ለምንናገረው ማንኛው ተራና ከንቱ ንግግር ጌታ ይፈርድብናል (ማቴ 12፥36)።

ያዕቆብ በየትኛውም ሁኔታ መማል አያስፈልግም አላለም። በአንዳንድ አገር ፍርድ ቤት ምስክርነት ከመስጠት በፊት መሐላ ይገባሉ፤ ይህ ኀጢአት አይደለም። እጅግ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች መማል ተገቢ ይሆናል (ዕብ 6፥16–17)። ሐዋርያው ጳውሎስ በሚናገረው ነገር አብዛኛውን ጊዜ ጌታን ምስክሩ አድርጎ ይጠራል (2ቆሮ 1፥23፤ ገላ 1፥20፤ ፊል 1፥8)። ያዕቆብ በሚናገረው እንዲህ ስላለው ሁኔታ ሳይሆን ተራ በሆነው ንግግር ውስጥ ስለሚደረገው ተገቢ ያልሆነ መሐላ ነው።

የእምነት ጸሎት (5፥13–20)

13 በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ መጸለይ አለብን (ፊል 4፥6)። በዚህ ቍጥር ያዕቆብ ደስ ቢለን የምስጋና መዝሙር እንዲዘምር ይናገራል። ይህ እውነት ነው፤ ሆኖም በመከራ ውስጥ እያለንም የምስጋና መዝሙር መዘመር አለብን (ሐዋ 16፥23–25 ይመልከቱ)።

14 *የታመሙ አማኞች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን* ወደ እነርሱ ጠርተው ለፈውስ እንዲጸልዩላቸው ያድርጉ። ሽማግሌዎች የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መሪዎች ናቸው (1ጢሞ 5፥17፤ ቲቶ 1፥5–6 እና ማብራሪያዎቻቸውን ይመልከቱ)። የታመመውን ሰው *ዘይት ቀብተው*[9] *ይጸልዩለት።* በአዲስ ኪዳን ዘመን ዘይት ለህክምና አገልግሎት የሚውል ነው[10]። ስለዚህ ከዚህ እንደምንመለከተው የታመመ ሰው መድኃኒትም ጸሎትም ያስፈልገዋል። በመድኃኒት የሚደረጉ ህክምናም ሆነ ጸሎት *በጌታ ስም* ሊደረጉ ይገባቸዋል። «በጌታ ስም» ማለት የድግምት ቃል አይደለም። ነገር ግን የምንጸልየውና መድኃኒቱን የምንሰጠው እንደ ክርስቶስ ተወካዮች፣ እንደ እርሱ ፈቃድና ለእርሱ ክብር፣ በእርሱ የፈውስ ኀይል በማመን ነው።

15 እንዲህ ዓይነቱ በእምነት የተመሠረተ ጸሎት በሽተኛውን ያድነዋል። የእምነት ጸሎት የሰውየውን አካላዊ በሽታ ያድነዋል። የፈውስ ኀይል የሚመጣው ከክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ሕመምተኞችን በተሰጣቸው በመድኃኒት ወይም በጸሎት ብቻ ይፈውሳል፤ ወይም በሁለቱም ይፈውሳል። ገበሬው አትክልቱን ውሃ ያጠጣል፤ የሚያሳድገው ግን እግዚአብሔር ነው (1ቆሮ 3፥7)። በተመሳሳይ መልኩ ሐኪም ለበሽተኛው መድኃኒትን ይሰጣል፤ የሚፈውሰው ግን ክርስቶስ ነው። ያዕቆብ በዚህ ቦታ የሚናገረው ልዩ ስለሆነው የመንፈስ ቅዱስ የፈውስ ስጦታ አይደለም (1ቆሮ 12፥9)። ይህ ስጦታ ለጥቂት የቤተክርስቲያን አባላት የተሰጠ ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን የእምነት ጸሎት ሊያደርግ ይችላል። ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ የታመመው ሰው፣ ከቤተሰቡ ጋር ሆኖ ለፈውሱ መጸለይ አለበት (ቍጥር 13)። ሽማግሌዎች በአንድነት ተስማምተው የእምነት ጸሎት ቢያደርጉ ኢየሱስ ጸሎታቸውን ይመልሳል (ማቴ 18፥19–20፤21፥23)።

ይህ ሰው (በሽተኛው) *የሠራው ኀጢአት ቢኖር ይቅር ይባልለታል።* ብዙ በሽታዎች በቀጥታ በኀጢአት ምክንያት የመጡ አይደሉም (ዮሐ 9፥1–3)። ሆኖም አንዳንድ በሽታዎች በቀጥታ በኀጢአት ምክንያት ይመጣሉ፤ ያዕቆብ የሚናገረው እንዲህ ስላሉት በሽታዎች ነው። እንዲህ ባለው መንገድ በመጣ በሽታ የተያዘው ሰው ለሰውነቱ አካላዊ ፈውስ የሚያስፈልገው ብቻ ሳይሆን ለነፍሱም መንፈሳዊ ፈውስ ያስፈልገዋል። *በእምነት በተደረገው ጸሎት አማካይነት* የታመመው ሰው ኀጢአት ይቅር ይባልለታል፤ ነፍሱም ትድናለች። ክርስቶስ በሥጋ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን የአካል ፈውስንና የኀጢአት ይቅርታን ያደርግ ነበር (መዝ 103፥2–3፤ ማር 2፥3–12)።

ያዕቆብ በዚህ ቍጥር ጸሎት የተደረገለት ማንኛውም በሽተኛ አካላዊ ፈውስ ያገኛል ማለቱ አይደለም። ማንኛውም ሰው አንድ ቀን መሞቱ ስለማይቀር፣ የተጸለየለት ሁሉ ይፈወሳል ማለት አይደለም። የታመመ ሰው አካላዊ ፈውስ ባያገኝም ኀጢአቱን ከተናዘዘና በኢየሱስ ካመነ፣ ለኀጢአቱ ይቅርታ ያገኛል፤ ነፍሱም ትድናለች። ደኅንነት ከሁሉ በጣም አስፈላጊ የሆነ «ፈውስ» ነው፤ ሙሉና ዘላለማዊ ነው።

16 ኅብረት እንደሚያስፈልግ ሁሉም ክርስቲያን ይስማማል። የቤተሰብ ኅብረት፣ የጸሎት ኅብረት፣ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ፕሮግራሞችና የቤተክርስቲያን አምልኮ ጊዜያት አሉን። እነዚህ ሁሉ አስፈላጊና መሠረታዊ ናቸው። ። ነገር ግን እውነተኛ ኅብረት በእነዚህ ስብሰባዎች ከመገኘት የበለጠ ነው። እውነተኛ ኅብረት ማለት *ኀጢአታችንን እርስ በርስ መናዘዝ ነው፤* እርስ በርስ መተዋወቅና መዋደድ ነው፤ እርስ በርስ መተማመንና አንዱ ለሌላው መጸለይ ማለት ነው። ሁላችንም ኀጢአት ስለምንሠራ የምንናዘዘው ኀጢአት አለን። ከማንም የምንደብቀው ነገር የለም።

ስለዚህ እርስ በርሳችን ኀጢአታችንን እንናዘዝ፤ ከዚያም አንዱ ለሌላው ይጸልይ። ይህን ስናደርግ ሁላችንም መንፈሳዊ ፈውስ እናገኛለን። ኅብረታችንም ይጠነክራል፤ ደስታ የሞላበት ይሆናል።

የጻድቅ ሰው ጸሎት ብዙ ውጤት የሚያስገኝ ታላቅ ኀይል አለው። ጻድቅ ሰው ግን ነው? እኛ ነን። በክርስቶስ በማመናችን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ተብለን ተቆጥረናል። ጸሎታችንም *ውጤት የሚያስገኝ ኀይል* ያለው ነው። ስለዚህ *ባለማቋረጥ እንጸልይ* (1ተሰ 5፥17)።

17–18 የብሉይ ኪዳን ነቢይ ኤልያስ እንደ እኛው ሰው ነበር። ጸሎቱ በእርግጥ ውጤት የሚያስገኝና ብዙ ኀይል ያለው ነበር። በጸሎቱ በእስራኤል ምድር ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል ዝናብ እንዳይዘንብ አደረገ። ከዚያ በኋላ ጸለየ ዝናብ ዘነበ። ኤልያስ ምሳሌአችን ነው (1ነገ 17፥1፤18፥1፤41–45)።

19–20 ያዕቆብ በዚህ ስፍራ ለክርስቲያን *ወንድሞቹ* ይናገራል። አንድ ወንድም *ከእውነት መንገድ ቢወጣ፣ ለሞት* የተጋለጠ ነው (ቍጥር 20)። ስለዚህ ከተሳሳተበት መንገድ ለመመለስ ሁልጊዜ መሞከር አለብን። የሚያድን እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ሆኖም የተሳሳተውን ወንድማችንን ከሳተበት ለመመለስ እኛን ይጠቀማል። ኀጢአት የሠራው ወንድም ከስህተቱ ከተመለሰ ማለትም ንስሐ ከገባ፣ ኀጢአቱ ሁሉ ይቅር ይባልለታል። የኀጢአት ይቅርታ የምናገኘው በንስሐ ብቻ ነው፤ ሌላ ምንም መንገድ የለም።

---

[9] በግሪኩ በዚህ ቁጥር *መቀባት* የሚለው ቃል ትርጓሜ መድኃኒት ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ መቀባት ትብዐ ቅዱስን አያመለክትም።

[10] ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ለዘይት የተሰጡት ሁለቱም ትርጓሜዎች ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም መድኃኒትን ለህክምና ስንጠቀም የፈውስ ሥራውን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው።